3628

# የእግዚአብሔር መንግሥት

## ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ቆይታው በምሳሌ የተናገራቸውን በጥልቀት የተብራራ

ከጌታነህ ቸርነት -ኢ/ር

# የእግዚአብሔር መንግሥት

የመጀመሪያው እትም
ኅዳር 2005 ዓ.ም

E-mail: getanehcher@gmail.com

ፖስታ 55214 አ.አ

## የመጽሐፉ አዘጋጅ

በሆለታ ገነት ከተማ በቀድሞው ገነት ጦር ትምህርት ቤት በሚባል ስፍራ ተወልጄ አደግሁ። በ1982 ዓ.ም. ጌታን አዳኝ አድርጌ ተቀብዬ አገልግሎት ጀመርኩኝ። እግዚአብሔር በሰጠኝ ጸጋ የጌታን ቃል አነባለሁ ደግሞም አስተምራለሁ። ላለፉት 20 ዓመታት በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት በተለይም በነቀምት፣ በፍቼ፣ በጊንቢ፣ በአሰላ፣ በሆለታገነት፣ በግንደበረት (ጋጎ)፣ በቡሬ፣ በፍኖተ ሰላምና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የአዲስ አበባን ከተማ ጨምሮ ሳስተምር ኖሪያለሁ። የጌታን ቃል ሳስተምር በተሰጠኝ ሰዓት ውስጥ አሳቦቼን መጠቅለል ስለማልችል የማስተምረውን ቃል በጽሑፍ ብቀይረው የተሻለ ሆኖ አገኘሁት።

በመሆኑም አስቀድሜ

- የእግዚአብሔር ነፋስ
- የእስራኤል ደናግል
- የኢየሱስ ክርስቶስ የምድር መልክ
- መለኮታዊ ጠጉር የሚሉ

መጽሐፍት አሳትሜ በገበያ ውለዋል። አሁን ደግሞ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚል መጽሐፍ በተለይም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ቆይታው በምሳሌ የተናገራቸውን ቃል ይዤ ለማስተማር ሞክሬያለሁ። ይህንን ሃሳብ ወይንም የመጽሐፍ ርዕስ እንዳዘጋጅ ትኩረት የሰጠኝ የሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረውን ቃል ተመርኩዤ ነው። "አሁንም፥ እነሆ፥ እኔ የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበክሁ በመካከላችሁ የዞርሁ ሁላችሁ . . ." (የሐዋ. 20፥25) በሌላ ስፍራም "ቀንም ቀጥረውለት ብዙ ሆነው ወደ መኖሪያው (የቅዱስ ጳውሎስ) ወደ እርሱ መጡ ስለ እግዚአብሔር መንግሥትም እየመሰከረ ስለ ኢየሱስም ከሙሴ ሕግና ከነቢያት ጠቅሶ

እያስረዳቸው ከጥዋት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ ይገልጥላቸው ነበር። አኩሌቶቹም የተናገረውን አመኑ እኩሌቶቹም የተናገረውን አላመኑም . . .' (የሐዋ. 28፥23-24)

ከጠዋት እስከ ማታ መማርና መስማት የሚኖርብን ጉዳይ ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህን ስናስተምር እኩሌቶቹ ያምናሉ እኩሌቶቹ ደግሞ አያምኑም። አሁንም እግዚአብሔር እስከ ፈቀደልኝ ዘመን ድረስ ይህን 'የእግዚአብሔርን መንግሥት' አስተምራለሁ።

ጌታነህ ቸርነት

## ምስጋና

ይህን መጽሐፍ ወደ ህትመት ከመምጣቱ 10 ዓመት በፊት የተቀመጠ ሲሆን የተወሰኑ ማስተካከያና እርማት ተደርጎ በመጽሐፍ ታትሟል። ብዙዎች በጸሎት፣ በሀሳብ፣ ጽሑፉን በማረም ተባብረውኛል የያንዳንዱን ስም መጥቀስ አስቸጋሪ ይሆናል።

ጽሑፉን ዋነኛ አካል በኮምፒውተር በመገልበጥ የጻፈችልኝን እኅት አሰለፈችን አመሰግናለሁ። በተጨማሪም ጥቅሶችን በማረምና የታከሉ ሀሳቦችንም በመጻፍ የተባበረችኝ እኅት መሠረት ገ/ኢየሱስን አመሰግናለሁ።

የመጽሐፉን የውጭ ሽፋን በማዘጋጀት የተባበረኝ አቶ አሸናፊ መንገሻን አመሰግናለሁ።



# ማ ው ጫ


መግቢያ ........ i

የመጽሐፉ አዘጋጅ ........ iii

1. የዓለም መንግሥታት ........ 1
2. የሰናፍጭ ቅንጣት ........ 7
3. የመንግሥተ ሰማያት ዕድገት ........ 15
4. በእርሻ የተሰወረ መዝገብ ........ 21
5. የተሸሸገ እርሾ ........ 30
6. በባሕር የተጣለ መረብ ........ 33
7. የወይኑ አትክልት ባለቤት ........ 37
8. የወይን አትክልት ተከራዮች ........ 54
9. ለልጁ ሰርግ ያደረገ ንጉሥ ........ 68
10. ባሮቹን ሊቆጣጠር የወደደ ንጉሥ ........ 76
11. ሩቅ አገር የሄደ መኩንን ........ 83
12. መልካም ዕንቁ የሚሻ ነጋዴ ........ 98
13. አሥሩ ቆነጃጅት ........ 106
14. የእርሻው እንክርዳድ ........ 114
15. በመንግሥትህ አስበኝ ........ 124
16. የሐዋርያት ጸሎት ........ 134
17. ሕፃናትና የእግዚአብሔር መንግሥት ........ 158
18. የመንግሥተ ሰማያተ ዋጋ ........ 166
19. መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም ........ 173
20. ዘመኑ ተፈፀመ ........ 179
21. ለታናሽ መንጋ የተሰጠ መንግሥት ........ 184

እንግዳ አይሆንበትም። በሌሎች ምሳሌዎች ደግሞ ከዚህ በተለየ መልኩ ትገለጣለች።

"ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።" (ማቴ. 28፥20) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊያርግ ሲቃረብ በማቴዎስ ወንጌል የመጨረሻው ቃል ይህ ነበር። እኔ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ በማለት ተናገረ። በትንቢት ነቢያት የተናገሩት፣ መዝሙራት፣ ሕግጋት፣ መላእክት የተናገሩት እንዳለ ሆኖ እርሱ በምድር ሲመላለስ ያስተማረውና ያዘዘው ጉዳይ ልዩ ትኩረት (Special emphasis) ተሰጥቶት በቅድሚያ አምኖ የተጠመቀ ደቀ መዝሙር ክርስቶስ ያዘዘውን እንዲማሩና እንዲጠብቁ ታዟል። በወንጌላት ውስጥ ብዙ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ተገልጦ የተናገረውና የመከረው ደግሞም የመሠከረው ከሌላው በተለየ ልዩ ትኩረት እንደሰጠው ተናግሯል።

"እኔ መጥቼ ባልነገርኋቸውስ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን ለኃጢአታቸው ምክንያት የላቸውም።" (ዮሐ. 15፥22) ... በእርግጥም በቅርንጫፎች የተነገረ ብድራትን ከተቀበለ ግንዱ በሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ሲመላለስ ያስተማረውን በትምህርት መንፈስ አብራርቶ አምነው ለጻኑ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ብዙ የተለያዩ ሰዎች በተረዱት ሁኔታ እንደጻፉ የታወቀ ነው። እግዚአብሔር ለአንዱ እንዲህ ለአንዱ እንዲያ ሲያስተምረው መሠረታዊ አቅጣጫን ሳይለቅ ሁሉ አንዱን ክርስቶስን ያምኑትና ይድኑ ዘንድ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ሲመላለስ ትኩረት ከሰጠባቸው የትምህርት አርእስት መካከል የእግዚአብሔር መንግሥት፣ ዳግም ምፅአት፣ ሁሉን ትቶ መከተል፣ እንደ ሕፃናት ልብ ይኖረን ዘንድ የመከረበት ብዙ ገጾችን የያዘ ነው። በብዛት ግን በየመድረኩ ስንሰማ የሚተላለፍልን



መልእክቶች በአንዱ ወንጌል ለዚያውም በአደባባይ ሳይሆን እንዲሁ በንግግር መካከል ጣል ያደረጋቸውን ነው። ለምሳሌ "ዳግም መወለድ" የሚል ቃል ለኒቆዲሞስ አንድ ጊዜ ተናግሯል ነገር ግን በተደጋጋሚ እንሰማዋለን። እኔ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት ነኝ ያለውም በዮሐንስ ወንጌል አንድ ጊዜ ቶማስ ለተባለው ሐዋርያ ጌታን ወዴት እንደምትሄድ አናውቅም ባለው ጊዜ የጠቀሰው ቃል ነው። ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ትርጉም ግን ማንም ሳይጠይቀው በግልጥ ሁሉ በተሰበሰቡበት እንደ ቋሚ ርዕስ ያስተማረበትና በቤት ሲቀመጡ ደግሞ ያብራራበት በመሆኑ እኛም እርሱ ትኩረት የሰጠበትን ወደ ነፍሳችን እንዲዋሃድ በተለያየ ምሳሌዎች ትርጉም በመፍታት ብንኖር በእርግጥም ደቀ መዝሙር ያደርገናል ብዬ አምናለሁ። እስተምሩ የሚለውን ቃል ከተናገረ በኋላ እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ከእናንተ ጋር ነኝ በማለቱ የመንግሥትን ሚስጥር ተምሮ ለመጠበቅ ነፍሱን ላዘጋጀ ሰው ጌታ ሁልጊዜ ከዚህ ሰው ጋር እስከ ዓለም ፍፃሜ ይቆያል።

# 1. የዓለም መንግሥታት

የእግዚአብሔር ቃል ስለ ዓለም መንግሥታት የተለያየ ትምህርት አለው:: የነዚህ መንግሥታት አመጣጥ፣ ቆይታና ፍፃሜያቸውን አስቀድሞ በትንቢት ይገልፃል:: አብዛኛዎቹ ግን ከእስራኤል መንግሥት አቋም ጋር የተቆራኙ ናቸው:: ከእስራኤል መንግሥት ርቀው ያሉትን በአብዛኛው አይጠቀልልም::

የአንድ አገር መንግሥት የራሱ የርስት ግዛት ያለው፣ መተዳደሪያ ሕግና ሕግ አውጪ አካላት ያሉት ሲሆን ይህን ሕግ ደግሞ ተግባራዊ እንዲሆን ዜጎችን የሚዳኝበት የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል:: በዳኝነት የተወሰነውን ደግሞ ውሳኔ አስፈጻሚ አካል አለው:: በመሆኑም የአንድ መንግሥት ዜጎች በሰላምና በመፈቃቀር እንዲኖሩ ይሆናል:: በተጨማሪም ንጉሡና የመንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት የሚቀመጡበት የንጉሥ ከተማ አለ:: የአንድ አገር መንግሥት ተጠሪነቱ ለዜጎቹ ለአገሩና ለሕጉ ነው::

እስራኤልን ስንመለከት በዓለም መንግሥታት መካከል (Center) እንደሆነች መመልከት ይቻላል:: በሰሜንና በደቡብ ያሉትን ወይንም በምስራቅና በምዕራብ ያሉትን ብንመለከት ሚዛኑ የተስተካከለ ነው::

በዓለም መንግሥታት ፈር መሠረት ዋናዎቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሰዋል:: የባቢሎን፣ የፋርስና ሜዶን፣ የግሪክና የሮማን መንግሥታት (Impire) ዋነኞቹ ናቸው:: በዚህ በተጠቀሰው መሠረት የእያንዳንዱ መንግሥት ወሰንና ኃይል በቅደም ተከተላቸው እየጠበበና እየላላ መጥቷል::

- የባቢሎን መንግሥት
- የፋርስና የሜዶን
- የግሪክ መንግሥት
- የሮም መንግሥት

(ዳን. 2፥ 31-49)

ልጆችንና የምድር አራዊትን የሰማይ ወፎችንም በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶሃል፥ ለሁሉም ገዥ አድርጎሃል፤ አንተ የወርቁ ራስ ነህ።" (ዳን. 2፥38)

የዚህ የወርቁ መንግሥት ችሎታው ከሰው ልጆች አልፎ አራዊትን፣ ወፎችንና ፍጥረታትን በሙሉ ያካተተ ነው። ጥንካሬውም የተፈተነ ነው። የመንግሥቱም ንጉሥ ስሙ የነገሥታት ንጉሥ ነው። "ብርታትንና ክብርን የሰጠህ የነገሥታት ንጉሥ አንተ ነህ።" (ዳን. 2፥37)

የቀድሞው የዓለም መንግሥታት አሁን እንደምናያቸው ዓይነት መንግሥታት አይደሉም። (Authocrasy) ፍፁም ባለሙሉ ማዕረግ ከመሆናቸውም በላይ ነፍሳቸው የወደደውን በሙሉ በተገዢው ሕዝብ ላይ መጫን ይችላሉ። ለምሳሌ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር ምስል በማቆም በሜዳ ላይ አገር ሁሉ እንዲሰግዱ አድርጓል። "ንጉሡ ናቡከደነጾር ላቆመው ለወርቁ ምስል እንድትሰግዱ ታዛችኋል፤ ተደፍቶም የማይሰግድ በዚያን ጊዜ በሚነድድ እሳት እቶን ውስጥ ይጣላል። ... ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የተናገሩ ሁሉ ተደፉ፥ ንጉሡም ናቡከደነጾር ላቆመው ለወርቅ ምስል ሰገዱ።" (ዳን. 3፥7)

ነቢዩ ዳንኤል እጅግ የተወደደ የእግዚአብሔር ሰው ነው ሥራውም የዓለምን ነገሥታት ታሪክ ማጥናት ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት በመሆን መጸለይ ነበር። ዳንኤል በጠላቶቹ ፊት የተገኘበት ነገር ቢኖር በእግዚአብሔር ፊት መጸለይ ነበር። ያለ ጸሎት መኖር እንደማይችል የታወቀለት ሰው ነበር። "የዚያን ጊዜም አለቆቹና መሳፍንቱ ስለ መንግሥቱ በዳንኤል ላይ ሰበብ ይፈልጉ ነበር፤ ነገር ግን የታመነ ነበርና፥ ስሕተትና በደልም አልተገኘበትምና በእርሱ ላይ ሰበብና በደል ያገኙበት ዘንድ አልቻሉም። ... ንጉሥ ሆይ፥ ከአንተ በቀር ማንም እስከ ሠላሳ ቀን ድረስ ልመና ከአምላክ ወይንም ከሰው ቢለምን፥ በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ ይጣል የሚል የንጉሥ ሕግና ብርቱ ትእዛዝ ይወጣ ዘንድ ተማከሩ።" (ዳን.



6፥4-7) ዳንኤል ሠላሳ ቀን ጸሎት አቁም ቢባል እሺ እንደማይል መሳፍንቱና አለቆች ያውቃሉ። ዳንኤል የጸሎት ጉዳይ ስለማይሆንለት ጸሎት ከሚያቆም ነፍሱን በአንበሳ ጉድጓድ ቢተው እንደሚቀለው አወቀ። ዳንኤል ግን ሠላሣ ቀን ከራሱና ከሌሎች ጋር አልተማከረም። አንድ ቀንም ያለ ጸሎት አልዋለም። "ዳንኤልም ጽሕፈቱ እንደተጻፈ ባወቀ ጊዜ ወደ ቤቱ ገባ፤ የእልፍኙም መስኮቶች ወደ ኢየሩሳሌም አንጻር ተከፍተው ነበር፤ ቀድሞም ያደርግ እንደ ነበረ በየዕለቱ ሦስት ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ በአምላኩ ፊት ጸለየ <u>አመሰገነም</u>። እነዚያም ሰዎች ተሰብስበው ዳንኤል በአምላኩ ፊት ሲጸልይና ሲለምን አገኙት።" (ዳን. 6፥10-11) ዳንኤል ጸለየ፤ በጽሑፉ ሳይደነግጥ እግዚአብሔርን አመሰገነ። ዳንኤል ወደ አንበሳ ጉድጓድ ሕዝቡ ወደ ደስታ ገባ። ነገር ግን የዳንኤል አንበሳ ጉድጓድ መጣል የዳንኤል ክብረ በዓል ቀን ሆነ። "ንጉሡም አዘዘ፥ ዳንኤልንም የከሰሱ እነዚያን ሰዎች አመጡአቸው፥ እነርሱንና ልጆቻቸውንም ሚስቶቻቸውንም በአንበሶቹ ጉድጓድ ጣሏቸው፤ ወደ ጉድጓዱም መጨረሻ ሳይደርሱ አንበሶቹ ያዙአቸው አጥንታቸውንም ሁሉ ሰባበሩ።" (ዳን. 6፥24) እነዚህ ሰዎች ከዳንኤልና ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመሆን የንጉሡን ዳርዮስን መንግሥት ተጠቃሚ ይሆኑ ነበር። ነገር ግን በምቀኝነታቸው የአንበሳው ጉድጓድ የእነርሱ ሀልፈት ሆነ። ከነልጆቻቸው ተሰባበሩ። ዳንኤል በብዙ ክብር ከበረ። ልዩ ልዩ ፈተና ልዩ ልዩ ክብር ሆነለት።

ዳንኤል እግዚአብሔር ፊት በጸሎት የሚቀርብ የእግዚአብሔር ሰው ነው። በመሆኑም ምሥጢርን እንዲያውቅ የተደረገው ለዚህ ሰው ነው። የዓለም መንግሥታትን ምሥጢር በጥበብ አወቀ። የዓለም መንግሥታት ገና በሙሉ ኃይላቸው ሳይዘረጉ እርሱ ከወዲሁ ገለጻቸው። ዛሬ ሰዎች በተለያየ መልክ የዓለምን መንግሥት ለማወቅ ብዙ መጽሐፍን ያነባሉ በመጽሐፍትም መጪውን ዘመን ለመተንበይ ይጥራሉ። ዳንኤል ግን ከአምላኩ ስር በመገኘት ዓለምንና መንግሥታቸውን አወቀ። ወደ እግዚአብሔር በጸሎት፣

ሥርዓት ውስጥ የተለያዩ ክፍሎች እንደሚኖሩ የደህንነት ሕይወት አንዱና ዋነኛው ነው::

የሰው ልጅ በጌታ የተወለደ ቀን የሰናፍጭ ቅንጣት በእርሻ እንደወደቀች ያክል ነው:: ትንሽ ነገር በሰው ልብ የሚበቅል ዕይታን ታካትታለች:: በልብ ዙሪያ የክርስቶስ ፍቅር እንደዚችው ዘር ትገባለች ትንቀሳቀሣለች:: ይህች ዘር ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ወልድ እንደ ሆነ ማስረጃን ትተዋለች:: የእግዚአብሔር መንግሥት የሰላም መንግሥት እንደሆነች ለተቀበለው ሰው ብልጭታን ታኖራለች::

ጌታ ኢየሱስ በምድር ሥጋን ለብሶ የዓለም መድኃኒት ሆኖ ሲገለጥ በዓለም በሙሉ በአንድ ጊዜ አልታየም ይልቅም በአንድ በከብት ግርግም በጨርቅ በቤተልሄም ተኛ ዛሬ ደግሞ ከሰሜን ጫፍ እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ ጫፍ በዓለም እየታወቀ መጣ:: ዓለም በሙሉ ስለ ክርስቶስ ከሰማ በኋላ የምድር ቆይታው ያበቃል:: የሰናፍጭ ቅንጣት የምታክለው ዓለምን ሞላ ፍሬው በሁሉ ቦታ ተንገርግሳ ተገለጠ ከሁሉ ዘሮች በለጠ:: ከግሪኮች በለጠ፣ ከሮማውያን በለጠ፣ ከባቢሎናውያን በለጠ፣ ከፋርስና ሜዶን መንግሥታት በለጠ፣ ዘር ነኝ ብሎ ከሚናገር በሙሉ በለጠ:: ትንሽ የምትመስል ዘር ሁሉን በለጠ:: በሥርዓት ኖረ:: የእግዚአብሔርን ሥርዓት ያቀፈ ዘር በመሆኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን በለጠ:: ሰው ሆኖ የመጣ ጌታ ሁሉን በለጠ:: "ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፤ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል::" (ማቴ. 24፥14)

ትንሽ የሚመስለንን የያዝነውን ዘር አንናቀው:: የሌሎችን ዘሮች ተመልክተን የኛን አናጥላላ:: ይልቅም በእግዚአብሔር ውኃ (በመንፈስ ቅዱስ) እያጠጣነው በመለኮታዊው ሙቀት እያሞቅነው እየኮተኮትነው በጥንቃቄ እንያዘው:: እግዚአብሔር ይህችን ዘር ያሳድጋል፣ ያበረታል ሁሉን ይበልጣል:: ሰዎች ይህን የእድገት አቅጣጫ ማየትን አይፈልጉም::



በእነርሱ ያለውን ዘር ይንቁታል ትንሽ ስለሚመስላቸው ከሌላው በማመዛዘን ይሰነካከላሉ:: የያዕቆብ ወንድም ኤሳው የብኩርና ጸጋ ነበረው:: ይህን ጸጋ ሲያቃልል አንድ የተናገረው ቃል ይደንቃል:: "ኤሳውም፦ እነሆ እኔ ልሞት ነኝ፤ ይህች ብኩርና ለምኔ ናት? አለ::" (ዘፍጥ. 25፥32) ከዚያ በኋላ ሐዋርያው በአዲስ ኪዳን ስለ ኤሳው ሲጽፍ በእንባ ተግቶ ቢሻትም መልሶ አላገኛትም ይለናል:: እኛም የመንግሥቱን ምሥጢር በሰናፍጭ ቅንጣት በውስጣችን ያለውን ይህች ለምኔ ናት የምንል ከሆነ ሌሎች አድፍጠው ይጠብቁታል::

አገልግሎትም ቢሆን ከእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት ውጭ አይሆንም:: አገልግሎት የሰናፍጭ ቅንጣት ሕግን መዝለል አይችልም:: አገልግሎት እየሰፋ ይሄዳል እንጂ ከሰፊ ወደ በለጠው ሰፊ አይሄድም መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አይመክርም:: ሰው በመጀመሪያ ራሱን ያገለግላል በራሱ የተዘራውን ቅንጣት ያገለግላል ራሱ ለራሱ ይሰብካል:: መንፈሱ ነፍሱን ይሰብካል ነፍሱ ሥጋውን ያስተምራል በውስጡ ድምጹን ለራሱ ይሰማል::

እግዚአብሔር መጀመሪያ ለአዳም አስተማረ:: ይህን አትብላ ሌሎችን ተመገብ በማለት አስተማረው:: ከአዳም ደግሞ ዓለምን ለመሙላት ነበር:: አዳም በመበደሉ የሰናፍጭ ቅንጣት ውጤታማ አልሆነችም:: እግዚአብሔር አዳምን "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት" የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል:: አዳም ግን ይኖርበት የነበረው ከዓለም ክፍል ውስጥ በዔደን ከዚህም በዔደን ምሥራቅ ነው:: ይህች የሰናፍጭ ቅንጣት የምታክል "ገነት" አዳም ሲበዛ እየሰፋች ምድርን ትሞላለች::

አንድ የጌታ መንፈስ ተሸክሞ የሚሄድ ሰው የቤተ ክርስቲያን መሠረት ወደ ሌለበት መንደር ሲገባ አስቀድሞ ማሰብ የሚገባው የሰናፍጭ ቅንጣት ሕግን ነው:: ሰላም ለዚህ ቤት በማለት የሰላምን ዘር ይዘራል:: ያች ቤት የእርሱ መሠረት መጣያ ትሆንለታለች::

"በማናቸውም ስፍራ ወደ ቤት ብትገቡ ከዚያ እስክትወጡ ድረስ በዚያው ተቀመጡ።" (ማር.6፥10) ከቤት ወደ ቤት መተላለፍ አደጋ አለው። በመጀመሪያ በተገባበት ቤት ያሉትን ወደ ጌታ ዘወር ካሉ በኋላ ወደሚቀጥለው ቤት ያሉትን እዚህ መቀላቀል በዚህ ሁሉ ይተዋወቃል ደግሞም ይጠባበቃል። ከዚያም ይህ የመንግሥት ቃል ሥር እየሠደደ ከምድር ብቅ እያለ ፀሐይ እየሞቀው ይመጣል። ይህ ቅንጣት ያድግና ከሁሉ ዛፎች በመብለጥ ቅርንጫፍ ያወጣል።

የሰማይ ወፎች በአንድ ዛፍ ላይ ጎጆ ሠርተው ለመኖር የቅርንጫፉን ታላቅነትና ማንነት አይተው ማንም ሳይመራቸው ራሳቸው ወጥተው ያርፉበታል። እነዚህ ርግቦችን እንደበረከት፣ መስፋፋት፣ ልዩ ልዩ ጸጋ ብለን ብናስባቸው ሁሉ ወደዚህ ብርቱና ታላቅ ዛፍ ይመጣሉ።

ለብዙ አብያተ ክርስቲያን አደጋ እየሆነ የመጣው ገና የቤተ ክርስቲያኑ መከፈት በይፋ ሳይታወቅ ብዙ ሺህ ሕዝብ ተጥለቅልቆ ይገኛል። የሰናፍጭ ቅንጣት ሕግን በመጣስ ከብዙ ዘር ይጀመራል እንደ ገና መቀጨጭ ይከተላል።

እግዚአብሔር አብርሃምን ካለበት ቀዬ አወጣውና እምነትን አስተማረው በዚህ ቅንጣት ግን እንደ ሰማይ ከዋክብትና እንደ ባህር አሸዋ የሰፋ ወገንን ለራሱ ለየ። የአብርሃም ውጤታማነት ሁሉን ሞላ የተስፋውም ዘር ከዚህ ተገኘ።

ጌታ ኢየሱስ በምድር ሲኖር እግዚአብሔር ኢየሱስን በጥበብ፣ በሞገስና፣ በቁመት አሳደገው። ለ30 ዓመት ሙሉ ይህን ጌታና ሰው እግዚአብሔር አስተማረ። ለ3 ዓመት አካባቢ ብቻ በማገልገል የእግዚአብሔርን ሥራ ጨረሰ። "እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ፤" (ዮሐ. 17፥4)

ጌታ በምድር አገልግሎቱ ጥቂት ተከታዮችን አስተማረ። በተለይም ለአሥራ ሁለቱ አስተማረ፤ በነዚህም ምድርን ሞላ።



ይህ በመሆኑ የእግዚአብሔር ባሕርያት በሙሉ የሰናፍጭ ቅንጣት ዕድገትን ይከተላሉ። ጥበብ፣ ማስተዋል፣ እውቀት፣ ፍቅር፣ ተስፋ በሙሉ የሚበዙ የእግዚአብሔርን ውኃና ሙቀትን የሚጠይቁ ናቸው። የእግዚአብሔር መንግሥትና በመንግሥቱ ሥር ያሉ ሁሉ የሰናፍጭ ቅንጣት ሕይወትን ይከተላሉ ቀስ ብላ የተጠራቀመች ንብረት እንደማትጎድል መጽሐፍ ይነግረናል። መሆኑም እየሰፋ በመሄድ የሚቆየውን መንግሥት ሥርዓት እንከተል።

## 2.3. የሰማይ ወፎች መታየት

የሰናፍጭዋ ቅንጣት እድገት ከፍተኛ ሲሆን የሚገለጡ የሰማይ ወፎች አሉ። ቅንጣትዋ ስትጠነክር ቅርንጫፎችዋም ይበዛሉ ይጠነክራሉ። የሰማይ ወፎች መሸከም ስትጀምር ወፎቹ ማንም ሳይጠራቸው ይመጣሉ ያርፉባትማል። ወፎቹ የራሳቸውን ክብደትና የቅንጣቷን ቅርንጫፍ ችሎታ ስለሚገምቱ ይመጣሉ። ከሁሉ ዘር ስለምትበልጥ በሩቅ መመልከት ይጀምራሉ። የቅንጣትዋ እድገት እስከ ዛፍ ስለሆነ ብዙ ወፎች ማከማቻ ትሆናለች። "የሰማይም ወፎች መጥተው በቅርንጫፎችዋ እስኪሰፍሩ ድረስ ዛፍ ትሆናለች።" (ማቴ. 13፥32)

እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥትን ወደ ልቡ ያስገባ ሰው ሁልጊዜ እድገት ይጠበቅበታል። ይህ ሰው በመንፈሳዊው ዓለም እያደገ ከመጣ ሌሎችን ሊሸከም የሚችልበት አቅም ይኖረዋል። ሌሎች የሚመጡት እንዲሸከማቸውና ከፍሬው እንዲበሉ ነው። እኔ ላይ ይህ ሁሉ ሸክም ለምን በዛብኝ ማለት አይቻልም። በሌሎች ቅጠሎች ላይ ማረፍ ባይችሉ በዚህ ሰው ላይ ግን ያርፋሉ። ጌታ ኢየሱስ በምድር ቆይታው ወቅት በመጨረሻው ዕድሜ ሲደርስ ማስተማር ጀመረ። ለ30 ዓመታት ሲያድግ ቆይቶ በመጨረሻ ሌሎችን መሸከም ጀመረ። "ዕለት ዕለትም በመቅደስ ያስተምር ነበር፤ ነገር ግን የካህናት አለቆችና ጻፎች የሕዝቡ ታላላቆችም

ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር፥ የሚያደርጉበትንም አጡ፤ ሕዝቡ ሁሉ ሲሰሙት ተንጠልጥለውበት ነበርና።" (ሉቃ. 19፥47-48) እንግዲህ በካህናት፣ በአለቆችና በታላላቆች ላይ ሕዝቡ ማረፍን አልፈለጉም ማሳረፍም ሆነ ፍሬ ማብላት አልቻሉም። የእግዚአብሔር መንግሥት እድገት በክርስቶስ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ በመሆኑ ሕዝቡ ሁሉ ከጌታ አንደበት የሚፈስሰውን ለመስማት ተንጠለጠሉበት። በማር ዘለላ ላይ እንደሚንጠለጠሉ ሕዝቡም ከጌታ አፍ በሚወጣው ቃል ላይ ቲንጠለጠሉበት። "ከንፈሮቹ እንደ አበቦች ናቸው፥ የሚፈስስ ከርቤንም ያንጠበጥባሉ።" (መኃ. 5፥13)

የሰማይ ወፎች በመንፈሳዊ በጳበሩ ሰዎች ላይ ማረፍ እንደሚገባቸው ሐዋርያው ጳውሎስም አስተምሮአል። "እኛም ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንንም ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል።" (ሮሜ. 15፥1) እንግዲህ የመንግሥተ ሰማይ የተመሰለችበት ዘር እያደገች ስትመጣ ሸክም ይበዛባታል ራሰዋን ደስ ከማሰኘት ለሌሎች ትኖራለች።

ኢሳይያስም ይህን በትንቢቱ ገልጦልናል። "ርግቦች ወደ ቤታቸው እንደሚበርሩ፥ እነዚህ እንደ ደመና የሚበርሩ እነማን ናቸው? እርሱ አከብሮሻልና ለአምላክሽ ለእግዚአብሔር ስምና ለእስራኤል ቅዱስ ልጆችሽን ከሩቅ ከእነርሱ ጋርም ብራቸውንና ወርቃቸውን ያመጡ ዘንድ ...።" (ኢሳ. 60፥8-9) እግዚአብሔር ባከበረው ሰው ላይ የሰማይ ርግቦች እንደ ቤታቸው ይመጣሉ። ርግቦች ወዴት እንደሚሄዱና ቤታቸውን የት ማድረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ። እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥትን ምስጢር በዚህ መልክ የተረዳ ወደ እኔ ሕይወት፣ አገልግሎት፣ ባሕርይ ወዘተ ሰዎች ለምን አልመጡም ማለት አይችልም። የእግዚአብሔር መንፈስ በጌታ ላይ እንደ ርግብ አምሳል እንደ ወረደ የጌታ በረከቶችም በዚሁ አካል ላይ ይመጣሉ።



## 3. የመንግሥተ ሰማያት እድገት

"እርሱም አለ፦ በምድር ዘርን እንደሚዘራ ሰው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደዚህ ናት ሌሊትና ቀን ይተኛልም ይነሣልም፤ እርሱም እንዴት እንደሚሆን ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል ያድግማል። ምድሪቱም አውቃ በመጀመሪያ ቡቃያ ኋላም ዛላ ኋላም በዛላው ፍጹም ሰብል ታፈራለች። ፍሬ ግን ሲበስል መከር ደርሶአልና ወዲያው ማጭድ ይልካል።" (ማር. 4፥26-29)

### 3.1. ሳይታወቅ የሚያድግ መንግሥት

ይህ መንግሥት በዓይን እየታየ የሚያድግ መንግሥት አይደለም። ለውጡ በአንድ ቀን የሚታይ ሳይሆን እንዴት እንደሚሆን ሳይታወቅ ያድጋል። ዘር የዘራ ሰው ዘሩ እንዴት እንደሚያድግ መመልከት አይችልም። ለዘሩ ማድረግ የሚገባውን ያደርጋል። ይኮተኩታል፣ ያርማል፣ ይጠብቃል በዚህ ምክንያት ዘሩ በምድር ይበሰብሳል ከዚያም ወደ ሰብል ደረጃ ያድጋል።

እድገቱ ማታም ቀንም ነው። ዘሪው የራሱን ሕይወት ሲኖር ዘሩም የራሱን ዕድገት ይቀጥላል። ልዩ ለውጥ የሚያደርግበት ማታም ቀንም አይኖርም። ሁል ጊዜ ዕድገት ስለሚጠብቀው ለዕድገቱ የሚሆኑትን ንጥረ ነገሮች በሙሉ ሁል ጊዜ ማግኘት ይገባዋል። የዘሩ የዕድገት ሁኔታ እንዴት እንደሚሆን አይታወቅም። ከምድር ብቅ ያለበት ቀን ይኼ ነው ብሎ መወሰን አይቻልም። ምን ዓይነት ቅጠል በምን ዓይነት ጊዜ እንደሚያበቅል መወሰን ያስቸግራል። የእግዚአብሔርን መንግሥት በአንድ ሌሊት ለማጥለቅለቅ የተሞከረ ነገር የተመካበት ስፍራ እንብዛም አይታይም። በተለይም ለመንግሥተ ሰማያት እድገት ሌሊትና ቀን ያለመታከት የሚሠሩ ሰዎች ዘሩን ያበቅሉታል።

ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔር መንግሥት ምሥጢር ፈጽሞ የገባው የእግዚአብሔር የክብር ሰው ነው። በሚሰጠን ስፍራ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አስጠርቶ ይናገር የነበረው ሕይወቱ እጅግ አስደናቂ ነው። ይህም በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 20 ቁጥር 17 ጀምሮ የሚገኝ ክፍል ነው። "ስለዚህ ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሠጽ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ"

የጳውሎስ እንባና ለቅሶ ለእግዚአብሔር መንግሥት ክብር ነው። ቀን ያለቅሳል ሌሊት ያለቅሳል። ይህንንም ሲናገራቸው ሁሉም እጅግ አለቀሱ። እንደ ጳውሎስ ያለ የእግዚአብሔር መንግሥት ጉዳይ ግድ የሚለው ጠፋ። ለሚበቅለው መንግሥት ቀንና ሌሊት ውኃ የሚያጠጣ ጠፋ የጳውሎስ እንባ ከፍተኛ ነበር።

የእግዚአብሔር ዘር ስንት ጊዜ በቡቃያነት ጠፋ? ሁሉ የራሱን ጉዳይ ሲመለከት የመንግሥተ ሰማያት ዘር በቡቃያነት፣ በዛላነት ያለፍሬ ቀረ። ለመንግሥቱ የሚጨነቅ የሚለፋና የሚያለቅስ ጠፋ። ዘሩ እንዴት ይብቀል? ይህ ዘር ታላላቅ ገበሬዎችን ጠየቀ። የገበሬዎችም ችሎታ አንድ ነው። ለዘሩ ሁለመናቸውን መስጠት ነው። ዘሩ በአንድ ጊዜ አይበቅልም። የሚጥለቀለቅ ነገር የለም። በዘመቻና በደቦ ሳይሆን በትዕግስት፣ በቀጥታ፣ በልዩ ልዩ ክብካቤ የሚበቅል ጠንቃቃ ዘር ነው። በመሆኑም የሌሊትና የቀን ዕንባ ናፈቀ። የሐዋርያት፣ የነቢያትን ዕንባ የሚጠይቅ ትግል ሆነ። ጳውሎስ ለእግዚአብሔር መንግሥት ክብር ራሱን አሳልፎ ሰጠ። "ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ። አሁንም፥ እነሆ፥ እኔ የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበክሁ በመካከላችሁ እየዞርሁ ሁላችሁ ከእንግዲህ ወዲህ ፊቴን እንዳታዩ አውቃለሁ።" (የሐዋ. 20፥24-25)



እግዚአብሔር የዝናብ አባት ነው። "በውኑ ለዝናብ አባት አለውን? ወይስ የጠልን ነጠብጣብ የወለደ ማን ነው?" (ኢዮብ 38፥28) እግዚአብሔር የሁሉ አባት ከሆነ ለዘሩ ውኃን እንዲያፈስ ከጠየቅነውና ካመሰገንነው ሁሉን ይሰጣል። ዘሩ ግን በቀስታ ስለሚያድግ አስቸጋሪና አሰልቺ ነው። የዕንባ ጉዞ ነው። ሌሊትና ቀን ለዓመታት የሚያስለቅስ ትግል ነው። እግዚአብሔር አዳምን በ6ኛ ቀን በመልኩና በአምሳሉ ለመፍጠር ሰማይንና ምድርን በሙሉ ጻሰሰ። የሰው ጉዳይ ሲያልቅለት ብቻ ወደ እረፍት ገባ። የሰው መፈጠር ሲያበቃ በዚሁ ቀን "እጅግ መልካም ነው" በማለት ዘጋው። ሳምንቱን አንድ ቀን ሲቀረው የፈጀ የመለኮት ጥበብ ነው። ጳውሎስም ፍጹምን ሰው ለማውጣት የሚያደርገው ትግል ይህ ነው የሚባል አይደለም።

## 3.2. የምድሪቱ እውቀት

የምድሪቱ እውቀት የሰብሉ ዕድገት አቅጣጫ ነው። የመጀመሪያ የምድሪቱ ዕውቀት ለዘሩ ቡቃያ መስጠት ነው። ዘሩ መዕደቁን ለመግለጥ ቡቃያን ትሰጣለች። ይህ ቡቃያ ዘሩ ከምድሪቱ ጋር ውኅደትን መፍጠሩን ሲያሳይ ዘሩ ስር መጣሉንና ትክክለኛ አቅጣጫ መያዙን ያሳያል። የዘረው ተስፋ የቡቃያው መታየት ነው። ዘርዘር ያለ ወይንም ችምችም ብሎ መብቀሉን ምልክት ይሰጣል። ጠጣር የነበረው ዘር ለስላሳ አካልን መያዝ ከተቀበረበት ይገለጣል። ቡቃያ ሊሆን የመጀመሪያው ዘር ፊፅሞ መልኩን ይቀይራል። ዘሩና ቡቃያውን የሚያዛምዳቸው ነገር የለም። ዘሩ ቡቃያው ጋር የሚገናኝበት መንገድ አይታወቅም። የተዘራው ስንዴ ቢሆን ቡቃያው አንድ ሦስትና አራት ትንንሽ ቅጠሎች ብቅ ይላሉ። እነዚህ ቅጠሎች የስንዴ ይሆን የገብስ ወይንም የሌላ ለመለየት ያስቸግራል። ምናልባትም የእንክርዳድ ቅጠል ሊሆን ይችላል። ምድሪቱ ግን ሁለት አቅጣጫ የእድገት

የነበረውን ገንዘብና ማንነት ሁሉ ሸጦ በዚህ መዝገብ ብቻ መኖርን ፈቀደ። የተበታተኑ እሳቤ ሳይሆን የትኩረት አቅጣጫው በሙሉ አንድ ሆነ።

ሰው ያለውን ነገር ሁሉ ሲሸጥ በአብዛኛው ቅሬታ ይኖረዋል ምክንያቱም የኑሮን አቅጣጫ መቀየር ያስፈራል። በተለይም የዚህ መዝገብ ምን ያህል እንደሚያዋጣ አስቀድሞ ካልታመነ አሳዛኝ ፍፃሜ ይሆናል። በአጋጣሚ መዝገቡ ውጤትን ቢያጣ ሰውዬው አብሮ ይጠፋል። ሁሉን ንብረት ሸጦ በዚህ መዝገብ ለመተዳደር ስለወሰነ የዚህ መዝገብ ፍፃሜ የሰውየውም ፍፃሜ ነው። ይህ ሰው ግን የዚህ መዝገብ ምሥጢር ጠንቅቆ ስለተረዳ ያለውን በሙሉ ሸጦ ገንዘቡን አሰባስቦ ይህን እርሻ ሲገዛ በሙሉ ደስታ ነበር።

ሰውም አግኝቶ ሰወረው ከደስታውም የተነሣ ያለውን ሸጦ ያን እርሻ ገዛ። ይህ ሰው በደስታ ብቻ አይደለም የገዛው። ይልቅም ሌላ ተጫራች ያገኘዋል በማለት ከማንም ደብቆ ገዛው። የሰውየው ነፍስ፣ መንፈሱና ሕይወቱ ፈፅሞ በዚህ መዝገብ ፍቅር ተነደፈ። ይህ መዝገብ ከእጁ እንዳይወጣ ያለውን ሁሉ አሸጠው የደበቀውን ምሥጢር ሁሉ ገንዘቡን በማፍሰስ ገዛው።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል እንዴት እንደሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ በግልፅ አስቀመጠ። "ብዙም ሕዝብ ከእርሱ ጋር ይሄዱ ነበር፥ ዘወር ብሎም እንዲህ አላቸው፦ ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የራሱን ሕይወት ስንኳ ሳየቀር ባይጠላ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።" (ሉቃ. 14፥25-26) "ኢየሱስም፦ ፍጹም ልትሆን ብትወድ፥ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ መዝገብም በሰማይ ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ አለው። ጐበዙም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ብዙ ንብረት ነበረውና እያዘነ ሄደ።" (ማቴ. 19፥21-22) "በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መልሶ፦ እነሆ፥ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ እንኪያስ ምን እናገኝ ይሆን? አለው።" ...እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ፥



የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ። ...የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል። (ማቴ. 19፥27-30)

ጌታን የሚከተሉ ብዙ ሕዝብ አሉት። አንዱን ከአንዱ የለየው "መተው" በሚለው ቃል ነው። ሁሉ ይከተሉታል ሁሉ ግን ሁለት ነገር ይከተላል። ኢየሱስንና ንብረቱን ወይም በእርሻ ያለውን መዝገብና ንብረቱን ይወድዳል በመሆኑም በመሃል መንገድ ከሚቀሩ አንዱን ይመርጡ ዘንድ ኢየሱስ ሕዝቡን አስተማረ በተለይም ከዚያ ሀብታም ጐበዝ ጋር በመዝገብ ምርጫ ተለያዩ። ሀብታሙ ከመዝገቡ ይልቅ ንብረቱን መረጠ።

እግዚአብሔር አንድ እርሻን እንድንገዛ ሲያዘን በእርሻ የሚታየውን ሰብል አይደለም። የእርሻውን ውጤታማነት የሚለኩ እንደ ወራጅ ውኃ፣ እንደ አፈሩ ባሕሪይ ማለትም ለም፣ ውጤታማ በማለት አይደለም ይልቅም በእርሻ የተሰወረውን መዝገብ ነው። በእርሻ የተሰወረውንም መዝገብ አገር ሁሉ አያውቀውም ይልቅም አንድ ሰው ያገኘዋል፤ በእርሻው ያለውን መዝገብ ለማንም ሳይነግር ያለውን ሁሉ ሸጦ ገዛ።

እግዚአብሔርም ክርስቶስን በምድር ሲልከው እንዲሁ ነበር። "መልክና ውበት የለውም፥ ባየነውም ጊዜ እንወድደው ዘንድ ደም ግባት የለውም። የተናቀ ከሰውም የተጠላ፥ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው፤ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፥ እኛም አላከበርነውም።" (ኢሳ. 53፥1-3) በመጨረሻም በሁለት ወንበዴዎች መካከል ራቁቱን ተሰቀለ። እንግዲህ ይህንን የእግዚአብሔርን ታላቅ እርሻ ማን ይገዛው? በኢየሱስ ክርስቶስ የነበረውን ታላቅ የእግዚአብሔር ቃል መዝገብ ማን ይገዛው? በሰው መስፈርት የሚገለፅ ውበት የለውም። ደም ግባት የለውም። የተናቀ ከሰውም የተጠላ ነበር። የእስራኤል መምህራን፣ ጸፍት፣ ፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያን፣ ጠቢባን፣ የዚህ ዓለም መርማሪዎች፣ ፈላስፎች አላወቁትም። በእነርሱ መስፈርት ቦታ አላገኘም። አንዳንድ ሰዎች ግን አወቁት እዚህ ግባ

የማይባሉ ሰዎች አወቁት፣ እረኞች አወቁት፣ እነ መግደላዊት ማርያም አወቁት።

መግደላዊት ማርያም ከሌሎች ይልቅ አወቀችው፤ ሰባት አጋንንት የነበረባት ሴት አወቀችው። አጋንንት የለብንም ፍፁም ሰዎች ነን በማለት ራሳቸውን የከበረ ስፍራ የሰጡት ሰዎች ይህን የክብር መዝገብ ሳያገኙ ይህች ሴት ግን አገኘችው። ሰው የራሱ ጥበብና አእምሮውን አፍኖ ከሚይዘው ይልቅ ለዘመናት በአጋንንት የታሰሩ የነበሩ የዋህ ሰዎች የጌታን ልብ አገኙ። ጌታ አጋንንትን ለማውጣት ብዙም ጉልበት አላወጣም ብዙዎቹን በጥቂት ደቂቃ ነፃ እያወጣ ዞረ በራሳቸው ማንነት ለተያዙ ሰዎች ግን ጉልበት አላወጣም። በራሳቸው ማንነት የተያዙ ሰዎች ግን ጌታንና መንግሥቱን እስከ ሞት ድረስ አሳደዱት። አጋንንት ያደሩበት ሰው ኢየሱስን አሳሳደደም ይልቅም ለክርስቶስ ታላቅ ክብር እየሰጠ ነፃ ወጣ። መግደላዊት ማርያም በሦስት መቶ ዲናር የተገዛ ሽቱ ገዝታ ጌታን ለመቃብሩ ቀባች ያላትን ሽጣ የጌታን የፍቅር መዝገብ ገዛች። ይህም የክብር መዝገብ ይህችን ሴት ለዘላለም አከበራት። "እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በማናቸውም ስፍራ በሚሰበክበት እርስዋ ያደረገችው ደግሞ ለእርስዋ መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል።" (ማቴ. 26፥13)

ማርያም ይህን ያደረገችው ተርፏት አልነበረም ይልቅም ያላትን ሽጣ አደረገች። የገዛ ደቀ መዛሙርቱ በዚህ ጉዳይ በጣም ሲያዝኑ ኢየሱስ ደስ አለው። በኢየሱስና በደቀ መዛሙርቱ መካከል ያለውን ርቀት ገለፀችው በራሴ ገንዘብ የራሳቸውን ጌታ ብቀባ እንደዚህ ለምን ይጮኻሉ? ለጌታ የሦስት መቶ ዲናር ዋጋ አይደለም ነፍሴም፣ ደሜም በእግሩ ቢፈስ አይበቃውም፤ ትልቅ ጌታ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ነው ከጌታ ክብር ይልቅ የድሆች ችግር ቢፈታ እነርሱ ደስ ያላቸው ይመስላል።



ብዙ ሰዎች በእርሻ ያለውን መዝገብ አግኝቶ ማንበብን ከዚያም የራሳቸው እንዲሆን ይመኛሉ የጌታ ቃል እውቀትን ይፈልጋሉ። ከጌታ መዝገብ በልባቸው መዝገብም እንዲጻፍላቸው ይሻሉ። የጌታን መዝገብ ይወዳሉ ሁሉ ቀርቶብኝ የእግዚአብሔር ቃል በነፍሴ ፅላቶች ቢጻፉ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ ሲሉ ይደመጣሉ። ትክክለኛ ምርጫ ነው ቃሉም የሚለው "በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል።" (ዮሐ. 15፥7) የእግዚአብሔር ቃል በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በልቡ የተመዘገበለት አንድ ሰው ቢኖር ይህ ሰው የሚወድደውን ሁሉ ቢለምን ይሆንለታል። የእግዚአብሔር ቃል በልቡ ያልተፃፈለት ሰው ሲለምን ቢውል አንድ ነገር ተስፋ ማድረግ የለበትም።

እንግዲህ ሰዎች ይህን እርሻ መሰወር፣ ከደስታም የተነሣ ያለውን ሁሉ መሸጥ ይህንንም እርሻ መግዛት ከዚያም መዝገቡን ማግኘት ቀጥሎም ከመዝገቡ የሚገኘውን በረከት መቀበል። መዝገቡ ወደ ልብ መዝገብ ሲለወጥ ይህ ሰው የሚወድደውን ሁሉ ያገኛል። መቶ እጥፍ ይቀበላል። አንድ ነገር ሽጦ ይህን መዝገብ ቢገዛ መዝገቡ ተመሳሳይ ነገር መቶ እጥፍ ይሰጠዋል ሕይወትንም ያገኛል ይኸውም የተትረፈረፈ ማለት ነው።

ይህን መዝገብ ሳይገዙ የእግዚአብሔርን ቃል በአእምሮአቸው የያዙ አያሌዎች ናቸው። መጠቀም አለመጠቀማቸው ብዙም አይገድም ይልቅስ የእግዚአብሔር ቃል በአእምሮአቸው አውቀውት የእግዚአብሔርን ልጅ ለማስገደል መምከራቸው ግን ከሁሉ የከፋ ነው። ንጉሥ ሄሮድስ ጌታ ኢየሱስ ሲወለድ የተወለደበትን ዘመንና ቦታ ለመጠየቅ የሄደው የእስራኤል ሽማግሌዎች ዘንድ ነበር። "የካህናትንም አለቆች የሕዝቡንም ጻፎች ሁሉ ሰብስቦ ክርስቶስ ወዴት እንዲወለድ ጠየቃቸው። ... በነቢይ እንዲህ ተጽፎአልና በይሁዳ ቤተልሔም ነው አሉት።" (ማቴ. 2፥4-6) ይህ ማለት የእነርሱ እውቀት የጠቀመው ንጉሡን ነበር። በእግዚአብሔር ቃል ንጉሡን

አገለገሉት:: በእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔርን ቃል (ኢየሱስን) ሊያስገድሉ ፈለጉ::

በዚህም ዘመን የከበረው የእግዚአብሔርን መዝገብ የያዙ የእግዚአብሔር እርሻዎች አሉ:: እርሻው ደካማ ቢመስልም መዝገቡ ግን ጠንካራ ነው:: "ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን፤ " (2ኛ ቆሮ. 4፥7) ይህ መዝገብ በማይረባ ዕቃ ውስጥ በመኖሩ በሁሉ ይገፋሉ፣ ይሰደዳሉ፣ ያመነታሉ፣ ይወድቃሉ ነገር ግን ከመዝገቡ ክብር የተነሣ አይጨነቁም፣ አይጠፉም፣ አይጣሉም:: መዝገቡ በመኖሩ የጠላት ከበባና ግፊያ ያዘወትርባቸዋል:: ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ በመኖሩ ብዙ ሰዎች ይህን መዝገብ ወደ ያዙ ይመጣሉ:: ይህ መዝገብ ለሁሉ መልስ ነው ጌታ የከበረ ነገር በሸክላ ዕቃ ያስቀምጣል ምክንያቱም መዝገቡ ሸክላው ሳይሆን የጠባቂው ጉልበት ይጠብቀዋል:: በተኩላ መካከል ያለፍርሃት እንደሚሄድ ጠቦት መዝገቡም በጠባቂው ብርታት በሸክላ ዕቃ ይኖራል:: በመሆኑም በእርሻ የተሰወረውን መዝገብ ለማግኘት ያለንን ሁሉ እንሽጥ አሳባችን አንድ ይሁን::

4.3. ከእርሻ ግዢ በኋላ

እርሻው የተገዛው የገዢው ንብረት በሙሉ ተጠቃሎ ከተሸጠ በኋላ ነው:: ይህ የገዛው ሰው ይህን እርሻ ሲገዛ ከሰው አልተማከረም:: እርሻውን ሰውሮ በመግዛቱ ማንም ምክር ሊሰጠው አልቻለም ማንም ደግሞ ግዛው በማለት ሊመክር አይችልም:: እርሻው በእርሻነቱ ሳይሆን በመዝገቡ ውበት ክብርን በማግኘቱ የገዢውን ንብረት በሙሉ አሸጧል::

ይህ የገዛው ሰው ከአሁን በኋላ ምንም ዓይነት ወጪ በእርሻው ላይ (Investment) ማድረግ አይችልም:: ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት ቢፈልግ የሚያስይዘው ዋስትና (Colateral) ሊኖረው አይችልም:: ሁሉን በመሸጡ የእርሻው ባለቤት ንብረት ይህ እርሻ ከነመዝገቡ ብቻ ይቀረዋል:: በዚህ



እርሻ ላይ የሚያደርገው ወጪ የሚገኘው ከመዝገቡ የሚገኝ ትርፍ ብቻ ነው:: የሰውየው ቀሪ ንብረት ይህ በመሆኑ ሁሉን ኃላፊነት የሚጥለው በዚሁ መዝገብ ነው:: መኖሪያው መዝገቡ ይሆናል::

ክርስቲያንም በእግዚአብሔር መንግሥት ሲገባ መነሻ የሚያደርገው ያለውን ሁሉ በመሸጥ ነው:: ዓላማው፣ ራእዩ፣ ትዳሩ፣ ኑሮው፣ አገልግሎቱ፣ ሕይወቱ በሙሉ ከመዝገቡ ጋር የተቆራኘ ነው በመሆኑም በዚህ መንግሥት መግባት ማለት በደስታ ያለውን ሁሉ ሸጦ ከሥጋና ደም ጋር ሳይማከር መዝገቡ የሚለውን በሙሉ ማድረግ ነው::

ዘንዶዎች አንባሪዎችና ብዙ ዓይነት ፍጥረታት በባሕር ይኖራሉ። ባሕሩ ለክፉዎችም ለመልካሞቹም የምትሆን መኖሪያ ነች።

በቤተ ክርስቲያን ሕይወትም ይህን ማየት የየዕለት ተግባራችን ነው ሁሉ በአንድነት ይኖራሉ መልካሙና ክፉው እንዳይለይ መረቡ ሁሉን አቅፏል። ሁሉ በባሕሩ (በዓለም) ስለሚኖር ማንን ከማን መለየት አስቸጋሪ ነው። ሁሉ ማወቅ ያለበት ግን ምንም በዚህ ባሕር ቢኖርም ከሥሩ መረብ የተዘረጋው ውስጥ እንዳለ ሊገባው ይገባል አንድ ቀን ይህ መረብ ተጎትቶ ሲወጣ የሁሉ ድርሻ ይገለጣል።

ለክፉዎችም ለመልካሞችም የሚሆን ባሕር በመሆኑ ሁሉ አኗኗራቸው አንድ ዓይነት ነው። አመጋገባቸው፣ አተነፋፈሳቸው፣ የዋና ስልታቸው፣ በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው። ልዩነታቸው ግን ባሕሪያቸውና የውስጥ ማንነታቸው ነው። ድብልቅልቅ በማለት ቢኖሩም ይህ መደባለቅ ባሕሪያቸውን አይነካም።

## 6.2. የመረቡ መሙላት

ይህ መረብ ሕይወት የሌለው ቁሳቁስ ነው። ቀዳዳዎች አሉት ከዚህ መረብ ቀዳዳዎች መጠን በታች የሆኑ ፍጥረታት በሙሉ ሾልከው ይወርዳሉ። ለምሳሌ እንደ ትንንሽ ዓሶች፣ ተንሳፋፊ ነፍሳትና ውኃ ከመረቢቱ ቁጥጥር ውጭ ናቸው። መረቡ እነዚህን አትይዝም በተረፈ ከመረቡ ቀዳዳ መጠን ከፍታ ያሉ በሙሉ በዚህ መረብ ውስጥ ይከማቻሉ። ይህች መረብ አድሎ አታውቅም። የሁሉ ፍጥረታት አመጋገብ፣ አኗኗር ሁሉ አንድ ነው ውኃው ለሁሉ መኖሪያ ነው።

የዚህች መረብ አገልግሎት ዘመን የመረቢቱ መሙላት ብቻ ነው። ከሞላች በኋላ ባሕር ውስጥ አትቆይም ብትቆይም አገልግሎት አይኖራትም። አገልግሎት አይኖራትም እንጂ አትቀደድም።



መንግሥተ ሰማይም በዚህ ባሕር በሆነው ዓለም የምትቆይበት ዘመን እስክትሞላ ድረስ ነው ወንጌል ለፍጥረት ተሰብኮ እስክትሞላ ድረስ ነው። የዚች የተጣለች መረብ መሙላት የሁሉ ፍፃሜ ይሆናል። በንፁህ ዓሶችና ንፁህ ባልሆኑ የባሕር ፍጥረታት እስክትሞላ ትቆያለች። ይህች መረብ ስትሞላ ምልክቱ መነተት ነው። መረቢቱ ካለችበት ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ የተሸጋገረችበት ቀን የመጨረሻው ዘመን መጣ ማለት ነው። አስተዋይ የሆነ በሙሉ ዘመንን ማወቅ የሚችለው የዚህችን መረብ መሙላትና ከስፍራዋ መንቀሣቀስ መጀመሯን ነው።

ለምሳሌ በየቦታው የክርስቶስን ወንጌል በመስማት በየቤተ ክርስቲያኑ ደጃፍ የሚጥለቀለቀውን ሰዎች መመልከት አንዱ ማስረጃ ነው። የሰዎቹ በቅድስና የመሄድና ያለመሄድ አይወስነውም። የሰዎች በዚህ መረብ ውስጥ መብዛት ግን ትልቁ ማስረጃ ነው። የፈለገው ዓይነት ሰው ይሁን የክርስቶስን ወንጌል ሰምቶ ወደ እግዚአብሔር ቤት ይምጣ ከመጣ በኋላ አኗኗሩ የፈለገ ዓይነት ይሁን ቢፈልግ የቀድሞውን ዓይነት ኑሮ ይግፋበት። ይህች መረብ ግን እየሞላች ነው። በመረብ ውስጥ መግባት ከጽድቅ ኑሮ ጋር የሚያዛምደው ነገር የለም ዓሦች አንድ ዓይነት የሚመስል አኗኗር እንዳላቸው ሁሉ በቤተ ክርስቲያንም የቅዱሳኑና የማያምነው አኗኗር ተመሳሳይነት አለው። ሁለቱም በእኩል መልኩ ቃሉን ይሰማሉ፣ ቃሉን ይመገባሉ ወዘተ ነገር ግን ክፉዎች ሁልጊዜ ባሕሪያቸውን ሳይቀይሩ ይኖራሉ። አስራት ያወጣሉ፣ ጌታ ሆይ ይላሉ፣ ይመሠክራሉ፣ ይዘምራሉ፣ ይጸልያሉ፣ ይሰብካሉ፣ የእርዳታ ድርጅቶች ያቋቁማሉ።

## 6.3. ወደ ወደብ መውጣት

ይህች መረብ ስትንቀሳቀስ የነገር መጨረሻ ነው። በተቀመጠችበት ስፍራ ፍርድ የለም። ክፉና መልካም ተያይዘው የኖሩበት ዘመን የሚለየው ከእንቅስቃሴ በኋላ ነው።

አንድ ወደብ አለ በዚህ ወደብ ላይ የተቀመጡት ወደ ወደብ የሚመጡት ለመላእክት አገልግሎት ነው። አድሎ የሌለው በመሆኑ መላእክት ይህን ሥራ ይሠራሉ።

ወደብ ላይ የሚደረገው ሥራ አንድ ነው መለየት ነው። መኖሪያን መለያየት ነው። አብረው የኖሩባትን መረብ አገልግሎት እንድታቆም ማድረግ ነው። ከመረቡ ወደ ዕቃዎች ይከማቻሉ። መልካሞቹ ወደ ዕቃ ሳይሆን ዕቃዎች ውስጥ ተከማቹ። ከመረብ ወደ ዕቃዎች መሸጋገሪያው ድልድይ የመጨረሻው ቀን ነው። የእግዚአብሔር ዕቃዎች ብዙ ናቸው። ልዩ ልዩ የክብር ዕቃዎች አሉት የወርቅ፣ የብር፣ የናስ ፣ የከበረ ድንጋይ። በሌላ መልኩም የሸክላ፣ የእንጨትና የተለያዩ ዕቃዎች አሉት። እግዚአብሔር ከባሕር የወጡትን መልካሙን ዓሦች በዚህ መልኩ ሲያስቀምጥ ክፉዎች ግን ወደ ውጭ ይጣላሉ። ክፉዎች ከውኃ ወደ እሳት ይሸጋገራሉ። በእውነት የጌታ ክርስቶስን ሥጋና ደም እየተመገቡና እየታዘዙ የኖሩ ቅዱሳን ደግሞ በተራቸው ለክርስቶስ ክብር መብል ይሆኑ ዘንድ እንደተከበሩ ዓሦች በንፁህ ዕቃዎች ተደርገው በጌታ መንፈስ ተጠብሰው ይቀርቡለታል።



# 7. የወይኑ አትክልት ባለቤት

## 7.1. የእግዚአብሔር መንግሥት ባለቤት

የእግዚአብሔር መንግሥት የእግዚአብሔርና የክርስቶስ መንግሥትም በመባል ይታወቃል። "ይህን እወቁ አመንዝራም ቢሆን ወይም ርኩስ ወይም የሚመኝ እርሱም ጣዖትን የሚያመልክ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም።" (ኤፌ. 5፥5) የአብ የሆነው ሁሉ የወልድ የወልድም የሆነው ሁሉ የአብ እንደሆነ ክርስቶስ በወንጌላት አስተምሮአል በመሆኑም እግዚአብሔር ወልድን ስለወደደው መንግሥቱ ሁሉ የአብም የወልድም ነው።

በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የተለያዩ የርስት ግዛት አለ። አንዳንዱ ከባሕር ዳር ማዶ እስከ ባሕር ማዶ ርስት ሲኖረው አንዳንዱ ደግሞ የጫማ መርገጫ የምታህል ርስት የለውም። በተለይም የምንዝር ሕይወትና ጣዖትን ማምለክ የርስት ክብር ባለጠግነትን መብት ይገፍፋል። የከተማ ቦታ በሊዝ ወይንም በውርስ ሲወሰድ የእግዚአብሔር መንግሥት ግን በጽድቅ በመኖር የሚገኝ የርስት ክብር ባለጠግነት ነው።

የእግዚአብሔርንና የክርስቶስን መንግሥት ማንነትና ማወቅ ፈጽሞ ተገቢ ሲሆን የማይገባቸውና የማይመለከታቸውም አሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በ5ኛ ምዕራፍ ሲገልጥ አመንዝራ፣ ርኩስ፣ የሚመኝ፣ ጣዖትን የሚያመልክ በዚህ መንግሥት ውስጥ ርስት የለውም። ደግሞ የማይወርስ ባሪያ ነው። "ባሪያ ለዘላለም በቤት አይኖርም።" (ዮሐ. 8፥35) "የአብርሃም ሚስት ሣራም የተናገረችው ይህንኑ ነበር ይህችን ባሪያ ከነልጅዋ አሳድድ፤ የዚህች ባሪያ ልጅ ከልጄ ከይስሐቅ ጋር አይወርስም።" (ዘፍጥ. 21፥10)

ለገላትያ ሰዎች ደግሞ የእግዚአብሔር መንግሥትን የማይወርሱ ወይንም ርስት ስለሌላቸው ገልጦላቸዋል። እርሱም "ዝሙት፣ ርኩሰት፣

መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው።" (ገላ. 5፥19-21)

ለቆሮንቶስ ሰዎችም ሐዋርያው ጳውሎስ በመጀመሪያ መልእክቱ የእግዚአብሔር መንግሥት የማይካፈሉትን በግልጽ አስቀምጧል። ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።" (1ቆሮ. 6፥9-10)

## 7.2. ማለዳ የተነሳ ባለቤት

"መንግሥተ ሰማያት ለወይኑ አትክልት ሠራተኞችን ሊቀጥር ማልዶ የወጣ ባለቤት ሰውን ትመስላለችና። ሠራተኞችንም በቀን አንድ ዲናር ተስማምቶ ወደ ወይን አትክልት ሰደዳቸው።" (ማቴ. 20፥1)

የዚህ ባለቤት ፍላጎት ሠራተኞች በወይኑ እርሻ ለመቅጠር ሲሆን የሚያሳስበው ጉዳይ ሠራተኞቹ በጊዜ ተገኝተው በወይኑ አትክልት እንዲሠሩለት ነው። ማንኛውም መሥራት የሚችል በሙሉ ከባለቤቱ ጋር በመስማማት መሥራት ይችላል። ባለቤቱ የወይኑ ጉዳይ ስላስጨነቀው የተነሣው በማለዳ ነው ሌሊቱን በሙሉ ሲያስብበት ያደረበት ጉዳይ የወይኑ አትክልትን ነው።

ሠራተኞች ወደ ባለቤቱ አልሄዱም ቅጠረንም ብለው አልጠየቁትም። ባለቤቱ ግን ማልዶ ወደ ሠራተኞች ዘንድ ሄደ። ባለቤቱ ከቤት ወጣ ሠራተኞችንም ወደ ማሳው አገባ። የባለቤቱ ጭንቀት እንጂ የሠራተኞች አልነበረም ባለቤቱ ጉዳዩ በጣም ስላሳሰበው መልክተኞችን ልኮ ሠራተኞችን አልፈለገም። ሠራተኞችም ከባለቤቱ ውጭ ከማንም ጋር አልተዋዋሉም



መካከድም የለም። በማይሆን ዋጋ ሳይሆን ሁለቱም አካል በተስማሙበት ጉዳይ ሥራው ተጀመረ።

የሠራተኞች የሥራ መደብ (Job Description) ዓይነት አልተገለጠም ነገር ግን የአከፋፈሉ ሁኔታ አንድ ዲናር ነበር በመሆኑም በጅምላ ቀጠራቸው። ደመወዛቸውም በጅምላ በነፍስ ወከፍ አንድ ዲናር ነው። ክህሎት አለው፣ ጉልበት አለው፣ ቁመና አለው፣ ወጣት ነው፣ ወንድ ነው፣ የዚህ አገር ሰው ነው፣ ይህን ቋንቋ ይናገራል፣ የሚባል መስፈርት አልተቀመጠም። ብቻ ሰው ይሁን፣ ለመሥራት ፈቃደኛ ይሁን፣ በአንዱም ዲናር ይስማማ፣ ለአንድ ቀን ለመሥራት ፈቃደኛ ይሁን ይህ ብቻ በቂ ነው። በመሆኑም የወይኑን አትክልት ሥራ ማንም ጤናማ ሰው ሊሠራው ይችላል።

መንግሥተ ሰማያት የምትመስለው ሠራተኞቹን አይደለም። ወይን አትክልቱንም አይደለም። አንዱንም ዲናር አይደለም ነገር ግን የወይን አትክልት ባለቤትን ትመስላለች። ይህም ባለቤት ማለዳ የተነሣ ሰው ነው ለሌላ ሰው ሳይሆን ለራሱ ወይን ቦታ ሠራተኞችን ለመቅጠር የወጣ ባለቤትን ትመስላለች።

እግዚአብሔር የወይን አትክልት አለው ይህ የወይን አትክልት ሕዝቡ (እስራኤል) ነው። እግዚአብሔር ሠራተኞችን ፍለጋ ማልዶ ይወጣል። በወይን አትክልት ለመሥራት ፈቃደኛ የሆኑትንና ሰው የሆነ ሁሉ እንዲሠራ ይፈቅዳል። እግዚአብሔር ለራሱ ወይን ቦታ ሠራተኞችን ለመቅጠር ሲፈልግ በመልእክተኛ ወይንም በሌሎች አይቀጥርም። ቀጣሪው ራሱ እግዚአብሔር ነው፤ ቀጣሪ ባለቤቱ ነው።

ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ለወይን አትክልት ሠራተኛ መቅጠር ኃላፊነት የለኝም በማለት አባቱን አመልክቷል። "መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት አላቸው።" (ማቴ. 9፥37-38 ፤ ሉቃ. 10፥2)

ይህ የእግዚአብሔር አምላካችን ብቸኛ መብት ነው። የመከሩ ጌታ እግዚአብሔር ነው ሠራተኛ ሊቀጥርም ማለዳ ከቤት የወጣው ባለቤቱ ነው በመሆኑም ጌታ ኢየሱስ ይህ ኃላፊነት የአባቱ እንደሆነ ተናግሯል።

በአንድ ወቅት ሁለቱ የዘብዴዎስ ልጆች ጥያቄን አቀረቡለት፡- በክርስቶስ ቀኝና ግራ መቀመጥን ነበር። የጌታ መልስ ግን የምትለምኑትን አታውቁም በማለት ነገራቸው። ይህን ጉዳይ እኔን መለመን የለባችሁም። "በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም አላቸው።" (ማቴ. 20፥23) ወደ እግዚአብሔር ወይን ስፍራ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ መግባት አይቻልም የአምላካችን ፈቃድና ስምምነትን ይጠይቃል።

ሠራተኞቹ ባልጠበቁበት ጊዜ መጥቶ እንደቀጠራቸው እንጂ ሥራ ፈልገው ሥራ እንዳላገኙ ምሳሌው ይነግረናል። እግዚአብሔርም ሠራተኞቹ ዘንድ ሄዶ ይቀጥራል እንጂ ቅጠረኝ ተብሎ አይጠየቅም። ነገር ግን ወደ ወይን አትክልት ሠራተኞችን እንዲልክ መለመን ይቻላል። እኔን ቅጠረኝ በማለት ግን ሲለምኑት አንመለከትም።

አንዳንድ የምንሰማው ቃላት አሉ። እገሌ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ሙሉ ጊዜውን ለእግዚአብሔር ሰጠ። እግዚአብሔር ይቀጥራል እንጂ ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ አይቀጠርም። እግዚአብሔር ወደ ሠራተኛ ሲሄድ ሠራተኞቹ ይመጣል ብለው አይጠብቁም። ባለቤቱ ድንገት ይደርስባቸውና በዋጋ ተስማምተው ሥራውን ይጀምራሉ። ጌታ ኢየሱስ በአገልግሎት ዘመኑ ሐዋርያትን ሲመርጥ አመራረጡን ልብ ማለት ይገባል። በመጀመሪያ ማንም ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ አልተቀጠረም። ሌሊት አባቱን ይጠይቃል አብም በወልድ ውስጥ ሆኖ ሠራተኞችን ይቀጥራል። ይልቅም እንዲህ ቢባል መልካም ይመስለኛል። እኔ ከምሠራበት ከጠፊው ዓለም ሥራ ላይ አፈናቅሎ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ሥራ እንድሠራ በጌታ ዘንድ ጥሪ ቀረበልኝ እኔም በጌታ ምሕረት ተደንቄ ሥራውን ጀመርኩኝ በማለት በምሥጋና መንፈስ መናገር ይቻላል።

ጌታ ሰዎችን ለወይን አትክልት ሥራ ሲቀጥርና ወደ ጌታ ሥራ የገቡ ሰዎችን አይቻለሁ። አንዳንዱ ደግሞ ዝም ብሎ ሲንቀዋለል በየሰው ቤት ሲዞር፣ ጊዜውን ያለ ወይን መግረዣ መሣሪያና መኮትኮቻ ሲያሳልፍ ተመልክተናል። የምበላው፣ የምለብሰው፣ የምሠራው፣ የማገለግልበት መድረክ አልተሰጠኝም የሚሉ በየስፍራው ተበራክተዋል። ይህ የወይን አትክልት ባለቤት በማለዳ ወጥቶ ሠራተኞችን ለመቅጠር ያንቀሣቀሰው ጉዳይ ምንድነው? ሥራ ወደሌለበት ማሳ ለማሸጋገር የሰውን ልጅ ከሥራው ማፈናቀል ምን ይባላል? በአጭር ቃል እኔ እንደሚገባኝ አንድ ሰው ከሥራው ተነሥቶ የእግዚአብሔርን ሥራ በመሥራት መለኮታዊነትና የመገልገያ መሣሪያ፣ በላዩም የክብር ማዕረግ ሲደረግለት ሰዎች ሁሉ በዚህ ሰው ክብር የመንፈስ ቅናት ማደር ይገባቸዋል። እኔም እንደዚህ ሠው ሞቼ ነው ጌታ የሚቀጥረኝና የምከብረው በማለት በመሪር ለቅሶ ጌታን ይለምኑታል። የዚያን ጊዜ ያ ሰው የጌታ ጥሪ የቀረበለት ፈውስ፣ ትንቢት፣ ትምህርት፣ ጸጋ፣ ፍቅር፣ ሰላም፣ በጎነት፣ ስደት፣ ወሀኒ መጣል አብረው ተዋቅረው ይሰጡታል። በሁሉ ነገር የተወጠረ ከመሆኑም በላይ መጽሐፍ እንደሚል "ስምዖንና ከእርሱ ጋር የነበሩትም ገሥግሠው ተከተሉት፥ ባገኙትም ጊዜ፦ ሁሉ ይፈልጉሃል አሉት።" (ማር. 1፥ 36-37) ሁሉ ገሥግሠው ይመጡበታል እንጂ ማንንም አይለምንም። ሁሉ ይፈልጉታል እንጂ ሁሉን አይፈልግም።

የጴጥሮስና የወንድሙ እንድርያስ አጠራርን እንመልከት። "መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ፥ ዓሣ አጥማጆች ነበሩና። ኢየሱስም፦ በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው። ወዲያውም መረባቸውን ትተው ተከተሉት።" (ማር. 1፥16-18)

ግን እንደነዚህ ዓይነቱን ለመፈለግ ማለጻ ተነስቷል:: አለመገናኘት ማለት ይህ ነው::

በዚህ ዘመን በእግዚአብሔር የወይን ቦታ ለመሥራት ብቃቱ እያላቸው የሚቀጥራቸው በማጣት የጺጋ ፀሐይ እስክትጠልቅ የቆሙ አያሌዎች ናቸው:: ሌሎቹ ተቀጥረዋል፤ እነዚህ ግን በቀጣሪ መጥፋት በአደባባይ ቆመዋል:: እግዚአብሔር ይደርስላቸዋል:: ሠራተኛ ፍለጋ የተንከራተተው ጌታ በ 11ኛ ሰዓት ያገኛቸዋል ወደ ወይኑ አትክልትም ይልካቸዋል:: በሁሉ ተስፋ ቢቆረጥም በአምላካችን ተስፋ አይቆረጥም:: የዚህ ወይን አትክልት ጌታ የ11ኛ ሰዓቶችን ከሥራ ላይ አያነሳቸውም ነገር ግን ሥራ ያጡትንና የቆሙትን ይቀጥራል:: በተመሳሳይም የመለከት እውቀትና ችሎታ እያላቸው በወይን አትክልት መሣተፍ የሚችሉትን ያለቀጣሪ የተበተኑ አያሌዎች ናቸው::

ሐዋርያት የሆኑትን ስንመለከት ከቤተ መቅደስ ውጭ የራሳቸውን ሥራ እየሠሩ የወይኑን ሥራ ግን አይሠሩም ነበር:: በራሳቸው ሥራ እንጂ በመለኮት ጉዳይ ሥራ ፊት ሆነው ቆመዋል በመሆኑም ከቤተ መቅደስ ውጭ ሆነው በዓሣ አስጋሪነት፣ በግ ጠባቂነት፣ በቀራጭነት የተሰለፉትን በሙሉ ጌታ ወስዶ በወይኑ እንዲሠሩ አደረጋቸው:: የወይን አትክልት ጌቶችና ሠራተኞች ነን የሚሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ሲቀጠሩ አልታዩም:: እነዚህ ዓይነቶች እኛ የሙሴ፣ የኤልያስ በማለት የራሳቸው ጌታ እንዳላቸው ገለፁለት::

እኔ ከሁሉ ነገር ነፃ በመሆን ያለሁትን ሰው የሚቀጥረኝ አጥቼ የምንከራተተውን ማን ይፈልገኛል ማለት አይቻልም:: እግዚአብሔር ይፈልጋል ተገቢውን ዋጋ በመክፈል ያሰማራል:: በጌታ ቤት ለብዙ ዘመን በወይን አትክልት ውስጥ የሠሩ ሰዎች ትልቁ ፈተና የሚሆነው በመንገድ ላይ በመንከራተት የሚያውቋቸውን ሰዎች ጌታ ወደ ወይኑ አምጥቶ በክብር ሲጠቀምባቸው በጉዳዩ ያልተስማሙ ቀን ነው:: እኛ የተሰጠንን



የድርውን ሥራ በታማኝነት ከመሥራት ባሻገር በተቻለ መጠን ዝም ብንል መልካም ይሆናል ከተቻለ አሠራርንና ቅልጥፍናን ማሳየት ይጠበቅብናል::

## 7.6. የሠራተኛ ደመወዝ

"በመሸም ጊዜ የወይኑ አትክልት ጌታ አዛዡን፦ ሠራተኞችን ጥራና ከኋለኞች ጀምረህ እስከ ፊተኞች ድረስ ደመወዝ ስጣቸው አለው:: በአሥራ አንደኛው ሰዓትም የገቡ መጥተው እያንዳንዳቸው አንድ ዲናር ተቀበሉ::" (ማቴ. 20፥8-9)

ቀን ለሥራ ሲመደብ ምሽት ደግሞ ለእረፍት ነው:: ቀን ሳለ ብቻ በወይን አትክልት ይሠራል በመሸ ጊዜ ግን ደመወዝ መቀበል ይከተላል:: የወይን አትክልቱ ጌታ የሠራተኞችን ደመወዝ አያሳድርም:: በዚያኑ ቀን ለሁሉ ክፍሉ ያሰናብታል:: ሲቀጥራቸው ራሱ ወጥቶ ተነጋግሮ አመጣቸው:: ደመወዝ ሲከፍል ግን የቤቱን አዛዥ እንዲከፍል አዘዘው ::

እግዚአብሔር የሠራተኛ ደመወዝ ሳያድር እንዲከፈል ይፈቅዳል:: እንዲያውም ሠራተኛን ነገ ተነገ በስቲያ ማለት ኃጢአት ነው::

"ድሀ ነውና፥ ነፍሱም ጠንክራ ትፈልገዋለችና ወደ እግዚአብሔር እንዳይጮህብህ ኃጢአትም እንዳይሆንብህ ደመወዙን ፀሐይ ሳይገባ በቀኑ ስጠው::" (ዘዳግ. 22፥15)

"እነሆ፥ እርሻችሁን ያጨዱት የሠራተኞች ደመወዝ በእናንተ ተቀምቶ ይጮኻል፥ የአጫጆችም ድምፅ ወደ ጌታ ፀባዖት ጆሮ ገብቶአል::" (ያዕ. 5፥4)

## 7.7. የደመወዝ አከፋፈል

ለአምስቱም ጊዜያት የተቀጠሩት አንድ ዓይነት ክፍያ ሆነ:: ከሁሉም ብዙ ሥራና ተመጣጣኝ ክፍያ የተከፈላቸው የማለዳዎቹ ነበር ሌሎቹ ግን በባለቤቱ ፈቃድ ከሠሩት ሥራ በላይ ከፈላቸው:: አስቀድሞ የአስራ

## 7.10. ታማኝነት

ማልዶ የወጣ የወይን ባለቤት ቤቱ እርፎ የተቀመጠው የ11ኛ ሰዓቱን ቀጥሮ ከተመለሰ በኋላ ነበር:: ሁሉ ጊዜውን፣ አእምሮውንና ልቡን የጣለው ሠራተኛ ለማግኘት ነው:: ይህ ሰው ቀኑን በሙሉ ውጭ ነው:: የተገኙትን ይዞ ለመምጣት ብቻ ይገባል:: የሚወጣው እደባባይ ነው በዚህ ምክንያት በወይኑ ያሉት ሠራተኞች የቀጣሪ ዓይን በእነርሱ ላይ አይደለም በመሆኑም መለገም፣ ወሬ በማውራት ጊዜን መፍጀት ይችላሉ:: ቀጣሪው ሩቅ በመሆኑ ተቆጣጣሪያቸው የራሳቸው ሕሊና፣ ለወይኑ ያላቸው ፍቅርና የባለቤቱ ጭንቀት ነው ስለዚህ እነዚህ የወይን ሠራተኞች የሚጠበቅባቸው በራሳቸው ሕሊና፣ በንፁህ ልብና በታማኝነት ወይኑን ማገልገል ይሆናል::

አሁንም ልብ ልንል የሚገባን አምስቱም ጊዜ የተቀጠሩት ሠራተኞች ተስፋ የሚያደርጉት የራሳቸውን ደመወዝ እንጂ የወይኑን ባለቤት ጭንቀት ማሳረፍ አይደለም:: የምጸልየው፣ መንፈሳዊ ግልጋሎት የማደርገው፣ የምዘምረው በሙሉ በዚህ ጥቅስ መሠረት ከጌታ ዋጋ ለማግኘት እንጂ የወይኑን ባለቤት ንብረት ለመጠበቅ ይሆንን? በማለት ራስን መመርመር ተገቢ ነው:: ጌታ ሕይወቱን፣ ሥጋውን፣ ደሙን፣ መንፈሱን ሰጥቶን ለእርሱና ለወይኑ መሥራትና ማርካት ሲገባን የደመወዝ ጭቅጭቅ ውስጥ የሰው ልጅ መግባቱ ለሠማይ መላእክት ሳይደንቃቸው አይቀርም:: ለጌታ ውለታ ምላሽ የምንሰጠው በማንጉራጉርና በደመወዝ መከፈል ከሆነ በውኑ የሰው ልጆች ምንኛ ምስኪኖች ነን?



አንድ ክርስቲያን ሲጸልይና ሲናገር የሰማሁት እስከ አሁን ነፍሴን ያስደስታታል:: ጌታ ሆይ እኔ ኃጢአተኛውን ከተዘፈቅሁበት ማጥ አውጥተህ ይህን ሁሉ ክብርና መንፈስ ሰጠኸኝ:: ከዚህ በኋላ የዘላለም ሕይወት የሚባል ባይኖር እንኳ ሕይወቴ ከዚህ ላይ ቢቆም ይበቃኛል ብሎ እንባ ባረዘዘ ቃል ጌታን ሲባርክና ሲናገር ሰምቻለሁ:: በእውነት የጌታን ፍቅርና ማንነት የገባው ነበር::

# 8. የወይን አትክልት ተከራዮች

(ማር. 12፥1-9)

"አንድ ሰው የወይን አትክልት ተከለ፥ ቅጥርም ቀጠረለት፥ መጥመቂያም ማሰለት ግንብም ሠራና ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ። በጊዜውም ከወይን አትክልት ፍሬ ከገበሬዎቹ እንዲቀበል አንድ ባሪያ ወደ ገበሬዎቹ ላከ ይዘውም ደበደቡት ባዶውንም ሰደዱት። ዳግመኛም ሌላውን ባሪያ ወደ እነርሱ ላከ እርሱንም ወግረው ራሱን አቆሰሉት አዋርደውም ሰደዱት። ሌላውንም ላከ እርሱንም ገደሉት ከሌሎችም ከብዙዎች አንዳንዱን ደበደቡ አንዳንዱንም ገደሉ። የሚወደው አንድ ልጅ ገና ነበረው ልጄንስ ያፍሩታል ብሎ እርሱን ከሁሉ በኋላ ወደ እነርሱ ላከ። እነዚያ ገበሬዎች ግን እርስ በርሳቸው፦ ወራሹ ይህ ነው ኑ፥ እንግደለው ርስቱም ለኛ ይሆናል ተባባሉ። ይዘውም ገደሉት ከወይኑም አትክልት ወደ ውጭ ጣሉት። እንግዲህ የወይኑ አትክልት ጌታ ምን ያደርጋል? ይመጣል ገበሬዎቹንም ያጠፋል፥ የወይኑንም አትክልት ለሌሎች ይሰጣል።"

በዚህ የወይን አትክልት ላይ አንድ ባለቤትና ከባለቤቱ የተከራዩ ሰዎችን እንመለከታለን። ዘርዘር አርገን ብንመለከት ለዚህ ርዕስ የተለያዩ ገፀ ባህርያት እናስተውላለን ፡፡

- የወይኑ አትክልት ጌታ
- የወይኑ አትክልት ጌታ አንድያ ልጅ /ወራሹ/
- ተከራይ ገበሬዎች
- የአትክልቱ ጌታ ባሪያዎች
- ከተከራዮቹ ተባረው የተተኩ ሰዎች
- የወይን አትክልት ሕዝቦች
- ከወይኑ አትክልት ውጭ ያሉ ሕዝቦች



## 8.1. የወይኑ አትክልት ጌታ

ይህ ጌታ እጅግ ባለጠጋ በመሆኑ የወይን አትክልት ማሳ ሲኖረው ይህንን ማሳ አዘጋጅቶ ራሱ ከሚያስተዳድር ይልቅ ችሎታና እውቀት ላላቸው የወይን እርሻ ተከራዮች አከራያቸውና እርሱ ራሱ ወደ ሩቅ አገር ሄደ ፡፡

በዚህ ምዕራፍ እንደምንመለከተው የወይን አትክልቱ ጌታ ለተከራዮች ሙሉ ስልጣን ከመስጠቱ ባሻገር ወደ እርሻው ዘንድ ብቅ የሚለው ወይኑ አፍርቶ ከተሸጠ በኋላ በውሉ መሠረት የሚገባውን ድርሻና ኪራይ ለመሰብሰብ ወኪሎቹን ይልካል። ይህን ያደረገው ለወይኑ አትክልት፣ ለእርሻውና ለተከራዮቹ የማይገደው ሆኖ ሳይሆን ተከራዮቹ ይህን እርሻ የማስተዳደር ሙሉ ብቃት እንዳላቸው አምኖና በሙሉ ነጻነት ያለ ጌታው ጣልቃ ገብነት ይሠሩ ዘንድ ነው።

ነቢዩ ኢሳይያስ በ5ኛ ምዕራፍ የወይን አትክልት እርሻ የነበረውን ጌታ የእርሻውን ዝግጅት ሲናገር፦

- አረሰ
- ኈለኈለ
- መልካም ሐረግ ተከለ
- አጠጣ
- ቅጥር ቀጠረ
- ድንጋይ ለቅሞ አወጣ

ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ መልካም ፍሬን ጠበቀ። በማቴዎስ ወንጌል የተገለፀው የወይኑ አትክልትም ጌታ ተከራዮች ሌላ ወጪ እንዳያወጡ ሁሉን አዘጋጀ የእነርሱ ድርሻ ይጠብቁ፣ ያበጃጁ፣ ያስተዳድሩ፣ ፍሬውንም ይሸጡና ይጠቀሙበት ከዛም በላይ ለባለርስቱ የሚገባውን ድርሻ በክብርና በደስታ ከእጅ መንሻ ጋር ያቀርቡ ዘንድ ነው። አንዳንድ ጊዜ አንድን ቤት እርሻ ወይንም ንብረት ከባለንብረቱ ተከራይተን ብዙ ጊዜ ከተጠቀምን

በኋላ ዘመን እየጨመረ ሲመጣ የራሳችን ንብረት ስለሚመስለን ለባለቤቱ የማይታወቅ ጥላቻ በነፍሳችን እንደአረም በቅሎ እናገኛለን::

የዚህ መጽሐፍ ቃል የተነገረው ለእስራኤል ማኅበረሰብ በመሆኑ እነርሱ ደግሞ የወይን አትክልት እርሻ ንብረትነትና ኪራይ በደንብ ይገባቸዋል "ርስትህን አትሸጥ ..." የሚል ቃል በመኖሩ በተጨማሪም የነገድ ስም ማስጠሪያ በመሆኑ ርስታቸውን ከሕይወታቸውና ከነገሥታት ዛቻ በላይ ይጠብቃሉ ::

ንጉሡ አክዓብ በቤተ መንግሥቱ አጠገብ የናቡቴ እርሻ እንደነበረ የብሉይ መጽሐፍ ይጠቁማል:: አክዓብ ናቡቴን እርሻ በግዢ ወይንም በለውጥ የአክዓብን ቤተ መንግሥት ለማስፋፋት ተጠየቀ:: ናቡቴ አሻፈረኝ በማለት መለሰ:: ንጉሥ አክዓብም በጉዳዩ አዝኖ ቤቱ ተሸፋፍኖ ተኛ::

ንጉሥ አክዓብን ጌታ እግዚአብሔር ለምን እንደቀሰፈው በዚህ ዘመን በአፍሪካ ለምንኖር ሰዎች እንግዳ ነገር ነው:: የትኛው መሪ ነው በዚህ ዘመን ያን ያህል ትህትና አሳይቶ እርሻህን በግዢ ከፈለክ በለውጥ ስጠኝ የሚል:: አይሰጥህም ሲባልም አዝኖ ተሸፋፍኖ የሚተኛ ባለቤቱ ኤልዛቤልም ብትሆን ናቡቴን ያስገደለችበት ጠመዝማዛ መንገድ ይገርመኛል:: ጾም፣ ሽማግሌዎችን ጾም አስይዛ፣ አገር ሰብስባ እግዚአብሔርንና ንጉሡን ናቡቴ ሰድቧል በማለት የሐሰት ማስረጃ አቅርባ አስገደለች:: በሰለጠነው ዓለም የሚኖሩ የነገሥታት ሚስቶች እንኳ ይህን ዓይነት መንገድ የተከተሉ እንደሆነ በጨዋነት መንገድ ሄደዋል የሚያስብል ይመስለኛል::

እግዚአብሔር የወይኑ አትክልት ጌታ እንደሆነ መረዳት እንችላለን:: የአብርሃም ዘር የሆነው እስራኤል ደግሞ የወይኑ አትክልት እንደሆነ በምሳሌው እንመለከታለን::

እግዚአብሔር ሁሉን ካዘጋጀና ካስተካከለ በኋላ ደግሞ ለእስራኤል የመንግሥትን ቁልፍ ወይንም የእርሻውን መግቢያ ደጅ ቁልፍ ሰጥቶ አከራይቶ በሩቅ አገር ይኖራል:: (ወዮላችሁ የመንግሥትን ቁልፍ የያዛችሁ)



"እናንተ ሕግ አዋቂዎች፥ የእውቀትን መክፈቻ ስለ ወሰዳችሁ፥ ወዮላችሁ ራሳችሁ አልገባችሁም የሚገቡትንም ከለከላችሁ::" (ሉቃ. 11፥52)

እግዚአብሔር አዳምን ከሔዋን ጋር በኤደን ምስራቅ ከተከለው ገነት እንዳኖራቸውና እንዲጠብቁና እንዲያበጃጁት ካዘዘ በኋላ የማትበላውንም ፍሬ አሳየ፣ ይህን በበሉ ጊዜ ሞትን እንደሚሞቱ ነግሮ ሄደ:: ቀን ሙሉ ሩቅ አገር ይሄዳል ሲመሽ (ዘመን ሲያልቅ) ብቅ ብሎ ይጣራል:: ሊሠሩና ሊያበጁ የሚችለው በቀን ነው በማታ ወይንም በጨለማ ምንም ሥራ እንደማይሠራ ጌታ በዮሐንስ ወንጌል ተናገረ:: አዳምና ሔዋንም ሊሠሩ፣ ሊያበጃጁ በሚችሉበት ቀን አልመጣም:: እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን መጠነኛ ትዕዛዝና ሥራ አሳይቶ ሄደ:: ለምን ጌታ ትዕዛዝ አዘዘ የሚል ሰው ካለ እኔ እንደሚገባኝ አንተ ሰው እንጂ ተራ እንስሳ አይደለህም ለማለት ነው:: እንስሳ ወይንም አራዊት ሕግና ሕገ ልቡና የላቸውም:: እኛ የሰው ልጆችን አክብሮ ይህን አትብሉ ይህን ትበላላችሁ አለን:: ዛሬ አንድ መሥሪያ ቤት ተቀጥረን የምንሠራውን ዝርዝርና አንድ ነገር ካበላሸን ለዚያ ዋጋ እንደምንከፍል ካልተነገረን በአጭሩ አልተቀጠርንም ወይንም የኛን ሙያና ክህሎት መሥሪያ ቤቱ አላመነበትም:: እግዚአብሔር ይህን በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ ብሎ ለአዳም ሲነግረው አዳም ሕፃንና ማስተዋል የሌለው አልነበረም:: ይልቅም በሥላሴ አምሳል የተፈጠረ፣ ለእንስሳ ስም ማውጣት የሚችል የአእምሮ ስፋትና ጥልቀት የእውቀትም መክፈቻ የያዘ ሰው ነበር:: እንደኔ እምነት ለአዳም ይህ ብቻ ሣይሆን ብዙ የፍትሃብሔር፣ የወንጀልና የተለያዩ የሕግ ዘርፎች ሊነገረው ይገባ ነበር እላለሁ:: ምናልባት የመነሻ ሕግ ነው እያደር ይጨመርለት ነበር እላለሁ:: ምክንያቱም ብዙ ተባዙ ከተባለና ጦርና ጠብ ስለሚበዛ በገነትም ቢሆን ብዙ ሕግ ይጠይቅ ነበር:: እንዴ እንዴት በምድረ ገነት ጦርና ጠብ ጠበቅህ በማለት የሚሞግተኝ ካለ ከምድር ገነትና ክርስቶስ ደሙን

## 9. ለልጁ ሰርግ ያደረገ ንጉሥ

"ኢየሱስም መልሶ ደግሞም በምሳሌ ነገራቸው እንዲህም አለ፦ <u>መንግሥተ ሰማያት ለልጁ ሠርግ ያደረገ ንጉሥን ትመስላለች</u>፡፡ የታደሙትንም ወደ ሰርጉ ይጠሩ ዘንድ ባሮቹን ላከ ሊመጡም አልወደዱም፡፡ ደግሞ ሌሎችን ባሮች ልኮ፦ የታደሙትን፦ እነሆ ድግሴን አዘጋጀሁ፥ ኮርማዎቼና የሰቡት ከብቶቼ ታርደዋል፥ ሁሉም ተዘጋጅቶአል፤ ወደ ሰርጉ ኑ በሉአቸው አለ፡፡ እነርሱ ግን ቸል ብለው አንዱ ወደ እርሻው፥ ሌላውም ወደ ንግዱ ሄደ፤ የቀሩትም ባሮቹን ይዘው አንገላቱአቸው ገደሉአቸውም፡፡ ንጉሡም ተቆጣ፥ ጭፍሮቹንም ልኮ እነዚያን ገዳዮች አጠፋ፤ ከተማቸውንም አቃጠለ፡፡ በዚያን ጊዜ ባሮቹን፦ ሰርጉስ ተዘጋጅቶአል ነገር ግን የታደሙት የማይገባቸው ሆኑ፤ እንግዲህ ወደ መንገድ መተላለፊያ ሄዳችሁ ያገኛችሁትን ሁሉ ወደ ሰርጉ ጥሩ አለ፡፡ እነዚያም ባሮች ወደ መንገድ ወጥተው ያገኙትን ሁሉ ክፉዎችንም በጎዎችንም ሰበሰቡ፤ የሰርጉንም ቤት ተቀማጮች ሞሉት፡፡

ንጉሡም የተቀመጡትን ለማየት በገባ ጊዜ በዚያ የሰርግ ልብስ ያልለበሰ አንድ ሰው አየና፦ ወዳጄ ሆይ፥ የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ? አለው እርሱም ዝም አለ፡፡ በዚያን ጊዜ ንጉሡ አገልጋዮቹን፦ እጁንና እግሩን አስራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል አለ፡፡ የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና፡፡" (ማቴ. 22፥1-14)

### 9.1. ንጉሡ

በዚህ ክፍል መንግሥተ ሰማያት ራሷን በንጉሥ መሰለች፡፡ ንጉሡም የመንግሥትን ሥራ ሚሰራ ወይንም በክብሩ ተቀምጦ ሳይሆን ለየት ያለ



የግል ሥራ እየሠራ ነው፡፡ ይኸውም የራሱን ልጅ በመዳር ላይ ይገኛል፡፡ መንግሥተ ሰማያት በዚህ ክፍል በንጉሥ ሰርግ ስለተመሰለች ብዙ ምስጢራትን ይዛለች፡፡ የልጁ ሰርግ በመሆኑ ንጉሡ የተለየ ኃይሉን፣ ገንዘቡንና ሁሉን በዚህ ጉዳይ አስቀምጧል፡፡ ንጉሥ በመሆኑ ሠርጉ ከሃገሩ ሕዝብ በሙሉ የተለየ ነው፡፡ በንጉሡ በኩል ሁሉ በመኖሩ የተስተካከለ ሰርግ ነው፡፡ ሰርግ ደግሞ አንድ ቀን ብቻ የሚደረግ በዓል በመሆኑ ልዩ ትኩረትን ይሻል፡፡ የንግሥና በዓላት፣ የዓመት በዓላት፣ የክብር በዓላትና ሌሎች ዓይነት ድግሶች በሙሉ በተለያዩ ጊዜ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሰርግ ግን አንድ ጊዜ ተደርጎ የሚያልፍ ነው፡፡ ንጉሡ የልጁን መውደድ የሚገልጽበት ጊዜ ነው፡፡

"ንጉሥ አርጤክስስ የከበረውንም የመንግሥቱን ሀብት፥ የታላቁንም የግርማዊነቱን ክብር መቶ ሰማንያ ቀን ያህል አሳያቸው፡፡ ይህም ቀን በተፈጸመ ጊዜ በሱሳ ግንብ ውስጥ ለተገኙት ሕዝብ ሁሉ ከታላቁ እስከ ታናሹ ድረስ ንጉሡ በንጉሡ ቤት አታክልት ውስጥ ባለው አደባባይ ሰባት ቀን ግብዣ አደረገ፡፡ ... ንጉሡም እንደ ሰው ሁሉ ፈቃድ ያደርጉ ዘንድ ለቤቱ አዛዦች ሁሉ አዝዞ ነበርና መጠጡ እንደ ወግ አልነበረም" (አስ. 1፥4-9) ይህ ዓይነት ግብዣ እንኳ የከበረ ነው፡፡ አባት ደግሞ ትልቁ ሀብቱ ልጁ ነው፡፡ ከልጅነት የሚበልጥ ክብርም የለም፡፡

ልጁ ሰርግ ተደገሰለት ማለት ከዚያን ቀን ጀምሮ ልጁ ከቤት ወጣ ማለት ነው፡፡ አባቱንና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር የሚጣበቅበት ክብረ በዓል ነው፡፡ በመሆኑም ንጉሡ የልጁን የመጨረሻ ስንብት የሚያደርግበት ቀን ነው፡፡ አገር የሚደሰትበት ቀን ነው፡፡ በመሆኑም መንግሥተ ሰማያት የተመሰለችው ለልጁ ሰርግ ያደረገን ንጉሥ ነው፡፡ በጣም የምትናፈቅ ከንጉሡ እስከ ዝቅተኛው ኅብረተሰብ ድረስ ሊጠብቃትና ሊያከብሯት የሚገባው ዓይነት ነች፡፡ የንጉሡ የሰርግ ዝግጅት በመሆኑ ሁሉ ሰው ከንጉሡ በረከትን ለመቀበል የሚዘጋጅበት ነው፡፡ ንጉሡ የተለያየ ጊዜ

ከአካባቢው ሊርቅ ይችላል፤ ይህ ንጉሥ ግን በሙሉ ልቡ በቤት ይኖራል። የልጁ ሰርግ ቀን በመሆኑ በአካባቢው በዋንኛነት ይገኛል።

በመንግሥተ ሰማያት የተመሰለው ንጉሥ የወትሮውን አለባበስ ሳይሆን የከበረውን ልብሱን ለብሶ የሚገኝበት ቀን ነው። ንጉሡ ከልጁ ጋር የሚከበርበት ቀን ነው። ለልጁ የመጨረሻውን ስጦታ የሚያደግርበት በመሆኑ የልጁ ልብ በዋንኛነት በንጉሡ እርኗል። ንጉሡ የራሱን ልጅ ለመዳር በመጨነቁ፤ አዛገሮቹ፣ ባለሙዋሎቹ፣ አማካሪዎቹ በሙሉ በዚህ ሰርግ ይገኛሉ። የመንግሥታት ሥራ በሙሉ በአንድ ነገር ላይ ትኩረት ያደረገ ተግባር ይሆናል። ሁሉ ስለ ሰርጉ መሳካት የሚያስብበት ነው። ባሪያዎቹም ሰርጉን በተመለከተ ይሯሯጣሉ። በመሆኑም መንግሥተ ሰማያት በዚህ ንጉሥ በመመሰሏ የትኩረት አቅጣጫዋ አንድ ነው። በውስጧ የተገኘውም ሕዝብ ትኩረቱ አንድ ነው። ንጉሡን ሰርገኛውንና የታደሙትን ለማስደሰት ሰርጉ እንዲያምር ነው።

በዚህን በንጉሥ ቀን ሕዝቡም ከወትሮው ለየት ያለ ነገር ይጠበቅበታል። ቢቻል በገንዘቡ ሁሉ የሰርግ ልብስ ማዘጋጀት። ካልተቻለ ያለውን ልብስ አጥቦ፣ አመቻችቶ ሰውነትን በውሃ ታጥቦ መጠንቀቅን ይጠይቃል። በዚህ ግብዣ የታደመ በሙሉ ንጉሡን፣ ልጁንና ሰርጉን ስለሚመለከት የመጨረሻ ትኩረት ይጠይቃል። የተዝረከረከ ሰው መታየት የለበትም።

## 9.2. የታደሙት ሰዎች

በታደሙት ሰዎች ምክንያት ንጉሡ፣ ልጁ፣ ባሪያዎቹም ተደናገጡ። ትልቅ ችግር ተፈጠረ። ሙሽራው ወይንም ሙሽሪት የጠፉ ያኸል ሰርግ ቤቱ ተደናገጠ። ንጉሡ በእጅጉ አዘነ። <u>ስለ መንግሥተ ሰማያት ስናስብ በዚህ መንግሥት የተቆጣን፣ ያዘነን ንጉሥ እንመለከታን።</u> ያልጠበቀው ጉዳይ ገጠመው። በድግስ ቤቱ ውስጥ ችግር እንዳይኖር ሁሉን በጥንቃቄ



አድርጓል። የበሬው፣ የኮርማው፣ የፍሪዳውና የሌሎች ሥራዎች በወጉ ተፈፅመዋል። የታደሙትንም ያውቃል። የታደሙትንም በስማቸውና በአድራሻቸው ስለሚያውቅ በባሪያዎቹ አማካኝነት ስፍራቸው ድረስ በመሄድ ተጠሩ።

ንጉሡ የመጨረሻ ትኩረት ሰጥቶ የዋለበት ቀን ይህ ቀን ነው። ተራው ሕዝብ የናቀውም በዚሁ ቀን ነው። የንጉሡ የመጨረሻው ቁጣ በዚህ ቀን ነው። ወደ ንጉሡ ሰርግ መጀመሪያ በላካቸው ባሪያዎች የመጣው መልስ በደፈናው "አንመጣም" የሚል ነው። ከታዳሚው የሚጠበቀው ራስን አሳምሮ መገኘት ብቻ ነበር። ንጉሡ የታዳሚው ልብ ስላልገባው በድጋሚ የሰርጉን ሁኔታ በማብራራት እንዲነግሩ አዘዘ። "እነሆ ድግሴን አዘጋጀሁ፣ ኮርማዎቼና የሰቡት ከብቶቼ ታርደዋል ሁሉም ተዘጋጅቷል፤ ወደ ሰርጉ ኑ በሉአቸው አለ።" ታዳሚ እንዲመጣ ተደጋጋሚ ጥሪ ተደረገ። የንጉሡን ልጅ ሰርግ በነፃ ለመብላት ሁሉ ቸል አለበት። ንጉሡን፣ ልጁንና ሰርጉን ቸል አሉ።

የእግዚአብሔር መንግሥት በዚህ ንጉሥ በመመሰሏ በሰርግ ቀን የተከዘን ንጉሥ ትመስላለች የሚለውን ይተካል። ይህም ብቻ ሣይሆን የታደሙትን ለመጥራት የተላኩት ባሪያዎች በታዳሚዎቹ ተገደሉ። ሰዎችን ወደ ሰርግ በመጥራታቸው ጠሪዎቹ (ባሪያዎቹ) ተገደሉ። ምንም በማያውቁት ምክንያት ባሪያዎቹ ተገደሉ። ወደ ንጉሥ ሰርግ ኑ በማለት የተጠሩት ባሪያዎች ተገደሉ። ንጉሡ በመናቁ ባሪያዎች ተገደሉ። ንጉሡን የመግደል ያክል ሴራ ደረሰበት።

የቀረበ ማዕድ እያለ ወደ ንግድና እርሻ ተሰማሩ። የሰርግ ቀን በአብዛኛው የእረፍት ቀን ነው። እነዚህ ግን በዚህ ቀን ወደ ንግድና እርሻ ተሰማሩ። ከንጉሡ ሰርግ የራሳቸው ንግድና እርሻ በለጠባቸው።

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ያተኮረው በእስራኤል ቤት ነው። የእስራኤል ቤት የታደሙ ሲሆኑ ወደዚህ ሰርግ ለመምጣት እምቢ (ቸል) አሉ። የንጉሡ ጭንቀት አልገባቸውም። ተላላኪ (ነቢያት) እስከመግደል ደረሱ።

## 9.3. የተቃጠለ ከተማ

መንግሥተ ሰማያትን ስንመለከት የተቃጠለ ከተማንም እንመለከታለን። ንጉሡ ባለሙዋሎቹን አንድ ትዕዛዝ አዘዟል። የታዳሚዎቹ ከተማ እንዲቃጠል። በዚሁ መሠረት ከታደሙት ውስጥ የተላኩባቸውን ሰዎች ተገደሉ በሙሉ ዕጣ ፈንታቸው ከተማቸውና እራሳቸውም ጭምር ጠፉ፣ ተቃጠሉም። ንጉሡ ድግስ አዘጋጅቶላቸው እንዲደሰቱ በተወሰነበት ቀን ታላቅ የእሳት ቃጠሎ ደረሰባቸው። በዚህ ቀን እንግዲህ በሁሉ ዘንድ ሐዘን ነው። የመንግሥተ ሰማይ ምሣሌ የሆነው ንጉሥ በከፍተኛ ኃፍረትና ጸጸት በዚህ ቀን ዋለ። ሙሽራው ኩምሽሽ ብሎና አዝኖ በዙፋኑ ተቀምጧል። የንጉሡ ወዳጆችና ልጆች በደረሰው ጉዳይ በማዘን ወደ ቤት ገብተው በሀዘን ያለቅሳሉ። ቤቱ በሙሉ ጉድ ሆንን በማለት እጅግ አዘኑ። በታዳሚዎቹ መንደር የተነሣው የእሳት ቃጠሎ የሚያበርደው በመጥፋቱ ከፍተኛ ሃዘን በዚህ ስፍራ አለ። ንጉሡ ያዘዘው እሳት በመሆኑ አይጠፋም። ታዳሚዎቹን ሲጠሩ የተገደሉ በመሆኑ አንድ ሰው መንግሥተ ሰማያትን ለማየት ሲጣጣር ይህን ክስተት ይመለከታል። ያዝናል፣ ያለቅሳል። ብዙውን ጊዜ የመንግሥተ ሰማያት ምስጢር የገባቸው በዓይናቸው ሽፋሽፍት የእንባ ዘላዎች ይኖራሉ። ለምን እንደሚያለቅሱ ሳይገባቸው ያለቅሳሉ።

የሰርጉ ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን ሲመለከቱ ያዝናሉ። ሰርገኛው ክርስቶስ ያለበትን ሀዘን ሲመለከቱ ያዝናሉ፣ ያለቅሳሉ። የነቢያትን መገደልና መደብደብ ሲመለከቱ ያለቅሣሉ። ታዳሚው በሰርግ በመቅረታቸውና ከተማቸው በመቃጠሉ ያዝናሉ። የእስራኤል ገሰቀልናን



ሲመለከቱ ያዝናሉ። በሄሮድስ፣ በኔሮ የጠፋውን ከተማ ሲመለከቱ ያለቅሳሉ።

እንዲዚህ ሰርግ በዓለም ታሪክ አሳዛኝ ክስተት የለም። እንደዚህ ሰርግ አጋጣሚ የሚያስደነግጥ የለም። ነገር ግን የመንግሥተ ሰማያት ምሣሌ የሆነው ንጉሥ ተሰቃየ። ልቡ አዘነ። ተጸጸተ። "እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ።" (ዘፍጥ. 6፥6) ይህ በኖኅ ዘመን ነበር። የአሁንም ዘመን የኖኅ ዘመን እንደሆነ ጌታ ኢየሱስ አስተምሯል።

## 9.4. ክፉዎችም በጎዎችም የተመገቡት ሰርግ

ከተማው ከተቃጠለና የንጉሡ ቁጣ ከበረደ በኋላ የንጉሡ ትእዛዝ የሚደንቅ ነበር። ንጉሡ የተቆጣ በመሆኑና በታዳሚዎቹ ስላዘነ ሁሉ የሚጠብቀው አንድ ነገር ነበር። ይኸውም የተዘጋጀውን ሰርግ አስቀሞ መብሉን ወደ ውጭ ይደፋዋል የሚል ፍራቻ ነበር። ንጉሡ ግን እጅግ አስተዋይ በመሆኑ የሚያደርገውን አወቀ። በመንገድ ያሉ ሁሉ እንዲመገቡት ሆነ። ቤቱን ለመንገደኛ በሙሉ ከፈተ። ከአሁን በኋላ የታደመ ያልታደመ የሚል ሁኔታ ቀረ። የንጉሡን ሰርግ የማይገባቸው በሙሉ በሉት። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን እያመሰገኑ መብሉን በሉት። አጋጣሚ በመንገድ ላይ በመቆማቸው የዚህ ግዕድ ተካፋይ ሆኑ።

ሰውን ከሰው መለየት ቀረ። የሰርጉ መብል ላይ ክፉ ሰዎች እንኳ ተቀላቀሉ።

የእግዚአብሔር መንግሥት ማዕድ ሁሉ ተመገበው። ክፉውም በጎውም ተመገበው። የተመጋቢዎቹ ድርሻ ግን ደስ እያላቸው የንጉሡን ጭንቀት እንዲያስተው እያስደሰቱ መመገብ ይኖርባቸዋል።

ከእስራኤል ውጭ የምንገኝ የእግዚአብሔር መንግሥት ማዕድ ተካፋዮች የሆንን እኛ እግዚአብሔርን በማክበር መመገብ ይኖርብናል። እኛም

እንደገና በእግዚአብሔር ማዕድ ላይ ብንቀልድ ከመንገድ ተሰብስበው የንጉሡን ማዕድ ላይ እንደገና መቀለድ ነው። የንጉሡን ማዕድ የማይገባቸው ሰዎች እየተመገቡ በንጉሡ ማዕድ ችላ ቢሉ ከታዳሚዎቹ የከፋ ይሆናል። በመሆኑም በመንቀጥቀጥና በመፍራት እግዚአብሔርን በማክበር የማዕዱ ተካፋዮች መሆን ይኖርብናል። ሳንታደም እንዲሁ ከመንገድ ተሰብስበን የመንግሥትን ማዕድ እየበላን መሆኑን መዘንጋት እጅግ አሳዛኝ ይሆናል። "እግዚአብሔር እንደ ተፈጥሩት ለነበሩት ቅርንጫፎች የራራላቸው ካልሆነ ለአንተ ደግሞ (ለበረሃ ወይራ) አይራራልህምና።" (ሮሜ 11፥21)

ሌላ ወጪ ለማድረግ ቢታገል በርግጥም ይህ ሰው በከፊል ሽጦ የመጣ ነው። ከዚህ መዝገብ እድል ፈንታ የለውም። "ጴጥሮስም፦ ሐናንያ ሆይ፥ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ? ሳትሸጠው የአንተ አልነበረምን? ከሸጥኸውስ በኋላ በሥልጣንህ አልነበረምን? ይህን ነገር ስለ ምን በልብህ አሰብህ? እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም አለው። ሐናንያም ይህን ቃል ሰምቶ ወድቆ ሞተም፤" (የሐዋ. 5፥3-5)

ሐናንያና ሰጲራ ከነጴጥሮስ ጋር ኅብረትን ለማድረግ ፈለጉ። እነ ጴጥሮስ ያላቸውን ሁሉ ሽጠው ጌታን የተከተሉና የእርሻውን መዝገብ የገዙ ናቸው። የነዚህ ሐዋርያት ኅብረት የክርስቶስ ትምህርቶች በሙሉ ፍሬው የተንፀረገገበት ነበር። እነጴጥሮስን መተባበር ማለት በእነርሱ መንገድ መጓዝ ነበር። ሐናንያና ሰጲራም እርሻቸውን ሸጡ በከፊሉ የእርሻውን መዝገብ መግዛት በከፊሉ ከእርሻቸው ሽያጭ ማስቀረት በሚል ሃሳብ ሰይጣን ልቦናቸውን ደፈነ። የሰይጣን ዓላማ ሰው በሁለንተናው የእግዚአብሔርን መዝገብ መግዛት እንዳይችል ልብን ይከፍላል።



የእግዚአብሔርን መንግሥት መርህ መከተል ከፈለግን በቀጥታ የመንግሥት ልጆች መሆን ይኖርብናል። በእግዚአብሔር እርሻ ላይ እድል ፈንታ የሚኖረው የእግዚአብሔር መዝገብ ይሆናል። የኛ የሆነ ነገር በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ድርሻ የለውም። የኛ ድርሻ ሽጦ መግዛት ነው። ያለንን ሁሉ በመሸጣችን ከእንግዲህ በእግዚአብሔር በሆነ ነገር ብቻ የእግዚአብሔርን እርሻ እንገዛ "ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና" (ዮሐ. 15፥5)

- ማሚ የሚባል የጌሬራ ሰው ዳዊት በባዶ እግሩ ወደ ደብረ ዘይት ሲወጣ ትቢያ እየነሰነሰ ዳዊትን የደም ሰው እያለ ሲሰድበው ወዘተ::

ንጉሥ ዳዊት በዚህ ዘመን ቢኖርና ይህን የብሉይን መጽሐፍ ቢያነብ ምን ያህል እንደሚሸማቀቅ እገምታለሁ:: እንግዲህ ንጉሥ ነገሥት ዳዊትን የጌታ መንግሥት ስትፈትሸው ይህ ሁሉ ከተገኘበትና ዓለም በሚያነበው መጽሐፍ ገድሉ ብቻ ሳይሆን ውድቀቱ ከተብራራ እኔና አንተ ከበረሃ የመጣን ወይራ (ሮሜ 11 ይነበብ) መንግሥተ ሰማያት ፍተሻ ስታደርግ በውኑ ዕዳችንን ድፍንፍን አድርጋ ጉዳዩ በኔና ባንተ ይቅር በማለት እሽሩሩ ትለን ይሆን? በፍጹም አይመስለኝም::

እልፍ መክሊት ዕዳ የነበረበት ሰው ምሕረትን ጠየቀ ጌታውም ሁሉንም ተወለት:: ሙሉ ዕዳ ሰረዛ ተደረገለት:: ጥፋተኛ ነኝ፣ ዘርፌአለሁ፣ የአንተ ፍተሻና ብይን ተገቢ ነው የእኔ ዕጣ ደግሞ ገብቶኛል ለሚልና ወድቆ ለሚሰግድ ደግሞም ሁሉን እከፍላለሁ ለሚል ይህ ንጉሥ ይራራል:: ይህ ንጉሥ የሚያዝን እንጂ ጨካኝ አይደለም:: ለቀቀውም ዕዳውንም ተወለት:: ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

## 10.4. ከምሕረት በኋላ

ባለ እልፍ መክሊት ዕዳ የተለቀቀውና የተማረው ሰው ቀጣዩ ሁኔታ መከታተል ተገቢ ነው:: እንደተለቀቀና እንደተማረ ይህ ሰው ምን አደረገ?

- ከባለቤቱና ከልጆቹ ጋር ሆኖ የደረሰበትን ችግርና የገጠመውን ክብር አንስቶ ታላቅ ምስጋና ያደርግ ይሆን?
- የንጉሡን ውለታና ምሕረት እየዞረ ይሰብክ ይሆን?
- እርሱ እንደተማረ ሌሎችን መማር ጀምሮ ይሆን?

እነዚህንና ይህን የመሠሉትን በጎ ተግባር ሳይሆን ሌላ የጭካኔ ጭካኔ ውስጥ ራሱን ዘፍቆ ተገኘ:: ይህ ባሪያ ከጌታው ዘንድ እልፍ መክሊት ዕዳ



ወስዶ ከእርሱ ለሚያንሱት ለሌሎች ያበድር ነበር:: ወዲያውኑ ሙሉ ምሕረት እንደተቀበለ የራሱን ገንዘብ ያሰባስብ ጀመረ:: መንግሥተ ሰማያት ባሮቹን ሊቆጣጠር እንደጀመረና እርሱ እንደተገኘ ይህ ሰው የራሱን ገንዘብ መቆጣጠር ጀመረ::

መጽሐፍ የዚህን የተማረን ሰው ታሪክ ሲዘክር "ነገር ግን ያ ባሪያ ወጥቶ ከባልንጀሮቹ ከባሮቹ መቶ ዲናር ዕዳ ያለበትን አንዱን አገኘ፥ ዕዳህን ክፍለኝ ብሎ ያዘና አነቀው:: ስለዚህ ባልንጀራው ባሪያ ወድቆ፥ ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው:: እርሱም አልወደደም፥ ግን ሄዶ ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ በወኅኒ አኖረው::" (ማቴ. 18፥28-30)

እግዚአብሔር እኛን የሰው ልጆችን እንዲህ ነው የሚያውቀን:: እርሱ እልፍ መክሊት ምሮን እኛ ግን 100 መክሊት አይደለም መቶ ዲናር መማር አቃተን:: ይህ የተማረ ባሪያ 100 ዲናር ለባልንጀራው እንኳን ገንዘቡን ከየት አምጥቶ ነው ብለን በጥንቃቄ ብንፈትሽ ከጌታው ከሰረቀው እልፍ መክሊት ዕዳ ውስጥ ነው የሚሆነው:: ሰርቆ ከሰረቀው ቆንጥሮ አበድሮ የሰረቀውን እልፍ መክሊት ተትቶለት እርሱ ግን ጠላቱን ሳይሆን ባልንጀራውን አነቀው:: ሄዶ ማነቁ እንዳለ ሆኖ 100 ዲናር የተበደረው ባልንጀራ የለመነው አለማመን እልፍ መክሊት እንደተበደረው ዓይነት ቃና አለው:: <u>ታገሠኝ ሁሉን እከፍልሃለሁ</u>:: ይህ እልፍ መክሊት የተተወለት ባሪያ አገሩን ይጋብዛል ተብሎ ሲጠበቅ ባልንጀራውን ፈልጎ አነቀው:: እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ እልፍ መክሊት ዕዳ የነበረበት ሰው ባልንጀራውን ማነቁ ሳይበቃው በወኅኒ ጥሎ እስክትከፍለኝ አትወጣም ማለቱ ነው:: ሰውየው 100 ዲናር ለመክፈል የ100 ቀናት ሥራ ይበቃዋል:: በእስራኤል ባህል እንደ የወይን አትክልተኛ በጠዋት ተቀጥሮ ማታ አንድ ዲናር እንደ ተከፈለው ይታወቃል:: በዚሁ ስሌት እንኳ ብንወስድ ይህ ባሪያ 100 ዲናሩን በዓመት ከፍሎ ይጨርሳል:: ሠርቶ

እንዳይከፍል እንኳ በወኀኒ ጣለው። በዚህ ዘመን ብዙ ወንድሞቻችን በወኀኒ የሚገኙት እኛ ያበደርናቸው 100 ዲናር ስላልከፈሉ ነው።

### 10.5. አንተ ክፉ ባሪያ

የዚህ ክፉ ባሪያ ማንነት አስቀድሞ በጌታው ባሮች ዘንድ አዘንና ሁከትን ፈጠረ። "ባልንጀሮቹ የሆኑ ባሮችም ያደረገውን አይተው እጅግ አዘኑ፥ መጥተውም የሆነውን ሁሉ ለጌታቸው ገለጡ" (ማቴ. 18፥31) ከንጉሡ የተጠላ ክፉ ባሪያ የሚታወቀው አስቀድሞ በጌታው ባሮች ነው።

ይህን ሁሉ ያልጠበቀው ጌታችን ነው እንጂ ሌላ አይደለም። ይህን ዓይነት ባሪያ ምሕረት ማግኘት አልነበረበትም ጓደኞችንን አንቆ ወኀኒ ጣለብን በማለት በቀጥታ ጉዳዩን ለጌታቸው ገለጡት።

ይህ ክፉ ባሪያ ለሁለተኛ ጊዜ ጌታው ፊት ቀረበ። "አንተ ክፉ ባሪያ፥ ስለ ለመንኸኝ ያን ዕዳ ሁሉ ተውሁልህ፤ እኔ እንደ ማርሁህ ባልንጀራህ የሆነውን ያን ባሪያ ልትምረው ለአንተስ አይገባህምን? አለው። ጌታውም ተቈጥና ዕዳውን ሁሉ እስኪከፍለው ድረስ ለሚሣቅዩት አሳልፎ ሰጠው።" (ማቴ. 18፥32-34)

የንጉሡን ምሕረት ያቃለለ ይህ ክፉ ባሪያ መጨረሻው ከፋበት። እኔ ማርኩህ አንተስ ባልንጀራህን ለምን አልማርከም የሚል ጥያቄ ቀረበለት ውጤቱም "አንተ ክፉ ባሪያ" አስባለው።

ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ስናስብ የተቈጣ ንጉሥን እንመለከታለን። የማረውን ሕዝብ መልሶ ክፈለኝ ሲል እንመለከታለን። ክፉ ባሪያዎች ምሕረትን ሰለናቁ የቀድሞው ኃጢአታቸው ሲታሰብባቸው እንመለከታለን። የተማረ ሰው እንደ ገና ተጠርቶ ወኀኒና ወደ ሚሣቅዩት ሰው ተጣለ።



## 11. ሩቅ አገር የሄደ መኰንን

"እነርሱም ይህን ሲሰሙ፥ ወደ ኢየሩሳሌም መቅረቡ ስለ ሆነ የእግዚአብሔርም መንግሥት ፈጥኖ ሊገለጥ እንዳለው ስለ መሰላቸው ምሳሌ ጭምር ተናገረ። ስለዚህም እንዲህ አላቸው፦ አንድ መኰንን ለራሱ መንግሥትን ይዞ ሊመለስ ወደ ሩቅ አገር ሄደ። አሥር ባሪያዎችንም (His Servants) ጠርቶ አሥር ምናን ሰጣቸውና፦ እስክመጣ ድረስ ነግዱ አላቸው።" (ሉቃ. 19፥11-13)

### 11.1. ሩቅ አገር

የዚህ ሰው ማዕረግ መኰንን ነው አሁን የሚኖረው ግን በዚሁ በተባለው አገር ነው። የዚህ ሰው መንግሥት የምትገኘው ሩቅ አገር ነው። ይህ ሰው መንግሥት አለው መንግሥቱን ሩቅ አገር አኑሮ ራሱ መጣ። አሁን ባለበት መንግሥት ውስጥ ግን ሌሎች አላፊዎች አሉ። የዚህ ሰው ታላቅነት የሚታየው የከበረ መንግሥቱን አስቀምጦ በሌላ አገር መንግሥት ያን ያክል መቀመጥ መቻሉ ነው ምንም እንኳ መኰንኑ መንግሥቱ ሩቅ አገር ቢሆን በእጁ የራሱ መንግሥት ምናን አለው። የእርሱም ምናን በዚህኛውም መንግሥት ቢሆን ሊነገድበትና ሊተርፍ የሚችል ነው። የእርሱ ምናን በሌላ መንግሥታትም ስር ሆኖ ሊያተርፍ ይችላል።

ይህ መኰንን የራሱ ባሪያዎች አሉት ምናኑም እንዲያተርፉለት የተወላቸው ለራሱ ባሪያዎች ነው። የራሱ ባሪያዎች በታማኝነት ራሳቸውን ችለው እንዲነግዱ ከፊታቸው ዞር በማለት ሩቅ አገር ሄደ። አሁን እነዚህ ባሪያዎች የሚጠበቅባቸው ትልቁ ኃብታቸው ታማኝነት ነው። መኰንኑ በአጠገባቸው ስለማያዩት እንደፈቃዳቸው ሊኖሩ ይችላሉ። የሚጠበቅባቸው ሌላው ትልቁ ጉዳይ ምናኑ እንዲያተርፍ ብዙ እንቅስቃሴ ማድረግ ነው

የንግዱ ዘመን መኩንኑ እስኪመለስ ነው። መቼ እንደሚመለስ አልተነገራቸውም የተጣለባቸው አደራ ግን እንዲነግዱ ብቻ ነው።

ይህን ምሳሌ የተናገረው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ሲመላለስ ነበር። በዚህን ወቅት ወደ ኢየሩሳሌም እያቀና ሕዝብ ሁሉ በታላቅ ክብር የእርሱን ንግሥና ስርዓት በመጠባበቅ ባሉበት ወቅት ነበር። ወደ ኢየሩሳሌም ሲጠጋ የመናገሻ ከተማ የደረሰ መስሎአቸው ሁሉ የክብረ በዓሉን ቀን ይጠባበቃሉ። ሁሉ ሆ! በማለት ለማንገሥ ከእርሱም ክብርን ተቀብለው አብረው ለመክበር ነበር። የዕረፍት ጊዜ ነው ብለው ሲጠብቁ እርሱ ግን ይህችን ኢየሩሳሌም ሳይሆን ሌላ ሩቅ አገር እንደሚሄድ በምሳሌ ጭምር ተናገረ። የክርስቶስ የንግሥናው ከተማ ኢየሩሳሌም አይደለችም በሩቅ አገር ያለችው ከልጆቿ ጋር በነፃነት የምትኖረው አዲሲቷን ኢየሩሳሌምን ነው። በተጨማሪም ወደ ኢየሩሳሌም ባቀናበት ወቅትም የንግሥናው ሰዓት አልደረሰም ይልቅም ጊዜው ገና እንደነበር አስታወቃቸው። አሁን ባሪያዎች የምትከበሩበት ሰዓት ሳይሆን የምትነግዱበትና ምናን የምትቀበሉበት ጊዜ ነው። እስከ ዛሬ ምናኑ በእኔ እጅ ቆይቷል አሁን ወደ ሩቅ አገር ስለምሄድ ኃላፊነት የምትሸከሙበት ወቅት ነው፤ ይኸውም በምናን ነግዶ መኩንኑ እስኪመለስ ማትረፍ ነው።

የክርስቶስ መንግሥት ከሌላው መንግሥታት የምትለይበት ዋናው ጉዳይ የዚህ መንግሥት አድራሻ ነው። ሌላው መንግሥታት ከዚሁ ከዓለም ይገኛሉ ለምሳሌ የናቡከደነጾር መንግሥት ስትሻር ሌላ መንግሥት ከዚያው አገር ተገኘ። የፋርስና የሜዶን ሲሻር የግሪክ መንግሥት ተተካ። በሌላም መልኩ አንዱ መኩንን ሲሻር በዚያ አገር ተገገር የነበረ አንድ ሰው ይህን መንግሥት ይገዛል። የክርስቶስ መንግሥት አድራሻዋ ሩቅ አገር ነው በዚህ መንግሥት ሥር ያለውን አሰተዳደር ማንም አያውቀውም። ምን እንደሚመስል መገመት ያስቸግራል በሌላ መልኩ ይህ መንግሥት ሩቅ ነው። ሕዝቡ ኢየሱስ ወዲያው እንዲነግሥ ፈለጉ ሳይሰቀል፣ ሳይሞት፣



ሳይቀበር፣ ከሙታን በትንሣኤው ጉልበት ሳይላቀቅ በቀጥታ ንግሥናን ፈለጉለት የእርሱ መንገድ ግን እጅግ ሩቅ ነበር። ድብደባ፣ ስቃይ፣ መተፋት፣ መጣል፣ መሞት፣ መቀበር በሙሉ ሌላው ሩቅ መንገድ ሆኖ ማንም ሊገዝበት የማይችል ነው። በተጨማሪም የእግዚአብሔር መንግሥት ምሥጢሩ ሩቅ ነው። ለዚህ ዓለም የፍቅር መንግሥት ሩቅ ነው ሰላም፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋህነት፣ ቅንነት፣ ሕይወት፣ ታማኝነት... በሙሉ ሩቅ ናቸው፤ የተሰፋ ነገር ሩቅ ነው። የመረጋጋትና በፀጥታ መኖርም ሩቅ ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይዞት የሚመጣው መንግሥት የእንጀራና የመጠጥ አይደለችም። የሰላም፣ የፍቅር፣ የበጎነት፣ የታማኝነትና የእውነት ... መንግሥት ፍሬዎች ናቸው።

የእግዚአብሔር አገልጋዮችም በዚህ ዘመን የመንግሥቱን ፍሬዎች ለማግኘት አቋራጭ መንገድ የለም፤ ነገር ግን ከሩቅ አገር የሚገኝ ፍሬ በመሆኑ ዝም ተብሎ የሚታፈስ አይደለም። በእግዚአብሔር ፊት ሩጫ መሮጥ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ መቆየት፣ ወዳጅነትን ማድረግ ይጠበቃል። በክርስቶስ መንገድ የተገዙ የሩቁን አገር ፍሬ ሊያቀምሱን ይችላሉ። ከዚያም ምድር የሚመጣውን በረከት ከክርስቶስ እጅ መቀበል ያሻል። መኩንኑ ሩቅ አገር በመሄዱ እኛም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ይህን ሩቅ አገር መድረስ እንችላለን።

የዚህ ዓለም መንግሥታትና የእግዚአብሔር መንግሥት በቦታ ደረጃ እንኳ ሩቅ ናቸው። ሩቅም የተባሉት በሰው ቋንቋ ሳይሆን በክርስቶስ ቋንቋ ነው። የዚህ ዓለም መንግሥት አሠራርና አስተሳሰብ ከእግዚአብሔር መንግሥት አንፃር እጅግ ሩቅ ነው። ሁሉ ነገሩ ሩቅ ነው። የዚህ ዓለም ጥበበኞችና አስተዋዮች እንዳይጠጓቸው ሩቅ ነው።

መንግሥቱን ይዞ መጣ ፈለጉም አልፈለጉም ይህ መንግሥት ተገለጠ ባቸው::

ጌታ ኢየሱስ በራሱ አገር ሰዎች ተጠላ:: መንግሥቱንና የመንግሥቱን መኰንን ጠሉት:: እንድትነግሥብን አንወድም በማለት የእርሱን ማንነት ተቀናቀኑ:: በእንደበታቸው ብቻ ሣይሆን በምስክር እጅ እንደማይፈልጉት አረጋገጡ:: በሄሮድስና በጲላጦስ ፊት ካዱት:: በመልክተኞቻቸው አማካኝነት እንደማይፈልጉት ነገሩት:: እንዲነግሥባቸው እየጠሉ እርሱ ግን መንግሥትን ይዞ መጣ:: የእነርሱ ጥላቻ ሳይሆን የእርሱ ውሳኔ ብቻ ትፀናለች::

በሚጠሉት ሰዎች መካከል ይህ ምናን ምን ያክል እንዳተረፈ ለማወቅ ፈለግ:: በተቃዋሚዎቹ መካከል ይህን ምናን ታማኝ ለሚላቸው ለባሪያዎቹ ተወላቸው:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም የራሱ ንብረት (ጸጋ) ምን ያህል እንደሠራንበት ማወቅን ይፈልጋል:: ትንሽ በተሰጠን ነገር ምን ያህል ታማኝ መሆናችንን አስጠርቶ ይይቀናል::

የክርስቶስ ተቃዋሚ ማለት የክርስቶስን ንጉሥ መሆን ማወቅና አለማወቅ አይደለም:: ተቃዋሚ ማለት ግን ክርስቶስ በላዬ እንዲነግሥ የማይፈልግ ማለት ነው:: አንዳንዱ ክርስቶስን ያደንቁታል:: ትምህርቱ፣ ኑሮው፣ ጻድቅነቱንና ንጉሥ መሆኑን ያምናሉ ያውቃሉም ነገር ግን በላያቸው እንዲነግሥ ካልወደዱ ጠሉት ማለት ነው:: ንጉሥን መጥላት ንግሥናውን መጥላት ነው::

የዚህ አገር ሕዝብ የዚህን መኰንን የጠሉበት መንስኤው አልተገለጠም:: አገር በሙሉ የጠላው መኰንን ነው:: ያለመንግሥት በተመላለሰበት ወቅት ያውቁት ስለነበር የእርሱን መንገሥ እልወደዱም:: መንግሥት ይዞ እንደሚመጣ ግን ያውቃሉ:: የራሱ መንግሥት እንዳለው በውል አውቀዋል:: የእርሱን መንግሥትም ሆነ የእርሱን ንግሥና



አልወደዱም:: እርሱን በመጥላታቸው የእርሱንም በላያቸው መንገሥ አልወደዱትም::

የእርሱን ንግሥና እንደማይፈልጉ በቀጥታ ሳይሆን በመልክተኞች ገለጡለት:: መልክተኛ መላክ ማለት ሕዝቡ ሁሉ በአንድነት አድመውበታል:: ሕዝቡ ተስማምቶ ስለነበር በተናጠል አልሄዱም:: ይልቅም ሁሉ በአንድ ሆነው የተለያዩ መልክተኞች ላኩበት:: ኢትዮጵያ አንድ ባሕል አላት በተለይም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ:: አንዱ ክርስቶስን ብቻ አምኖ ከኖረ ከአደረ፣ ከማኅበር፣ ከቀብር እንዲወገድ ማኅበረሰቡ ይስማማል::

እኔ ጌታን ከመቀበሌ በፊት የእግዚአብሔርን የመኖር ሕልውና ... አላውቅም ነበር:: የምንም ሃይማኖት ተከታይ ለመሆንም ያን ያህል ስንቀሳቀስ ራሴን አላገኘሁም ነበር:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በአዳኝነቱና በሙሉ ጌትነቱ ተቀብዬ መኖር ስጀምር ግን ያሳድዱን ጀምር:: በአጭር ቃል የመንግሥቱ ንጉሥ የማይወድዱት በመሆኑ እኔን ሳይሆን ሩቅ አገር የሄደውን መኰንንን ጠሉት:: ምክንያቱም ይህን ጌታ በላዬ ሳላነግሥ ይወድዱኝ የነበሩ በዚያን ጊዜ ወደ ጥላቻ መጡ:: በዚህም ለኔ መዳን መሆኑን አረጋገጥሁ::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የተናገረው በጉጉት የእርሱን መንግሥት መገለጥ ይጠብቁ ለነበሩ ሲሆን ይህም ወደ ኢየሩሳሌም በቀረበ ጊዜ ነበር:: ሕዝቡ የሚወደው በሚመስልበት ቀን የአገሩ ሰዎች ይጠሉት ነበረና በማለት ያስተምራል:: "የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም::" (ዮሐ. 1፥11) ዮሐንስ የጻፈው አልተቀበሉትም በማለት ሲሆን ጌታ ኢየሱስ ግን ይጠሉት ነበረና በማለት የሕዝቡን ልብ በአንድ ቃል አስቀመጠው:: አለመቀበልና መጠላት በመጠኑም ቢሆን ይለያያሉ:: አለመቀበል ከችሎታ ማነስና ከተዛማጅ ጉዳዮችም ሊመነጭ ይችላል:: ይጠሉት ነበረና ማለት ግን የጨለመና እጅግ የከፋ ነው:: ጌታ ኢየሱስ በሚኖርበት ቤት ወንድሞቹ ሳያምኑበት ሲቀሩ ለነዚህ ግልፅ ነገር ተናገራቸው::

"ዓለም እናንተን ሊጠላ አይቻለውም ፤ እኔ ግን ሥራው ክፉ መሆኑን እመሰክርበታለሁና እኔን ይጠላኛል።" (ዮሐ. 7፥7)

የዚህ አገርም ሕዝብ ይህንን መኰንን ሊጠላ እንጂ ሊወድ አልተቻለውም። በመካከላቸው ሲኖር ይህ ክፉ ነው በማለት ስለሚያሳውቃቸው ይጠሉታል። ዓለም እውነትን አታውቅም። መሪዎቿም እውነትን አያውቁም። አገረ ገዢ ጲላጦስ እውነት ማድረግ ሳይሆን እውነትን አያውቃትም። የማያውቀውን ደግሞ አያደርግም። "እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለው። ጲላጦስም፦ እውነት ምንድር ነው? አለው።" (ዮሐ. 18፥37-38)

የአገሩ ሕዝብ ኢየሱስን የጠላው በውስጥ ልቡ ብቻ ሳይሆን ልክ እንደ አድማ ነበር። ሁሉ መጥላታቸውን ለራሱ ነገሩት። ይኸውም በአንድ መልክተኛ ሳይሆን በተለያዩ መልክተኞች ነበር። የእግዚአብሔርን መንግሥት ይዞ ከሚመጣው ከኢየሱስ ይልቅ በጭቆናና በግፍ የሚገዛቸውን የሮማን መንግሥትን መረጡ። ከኢየሱስ ጌትነት ይልቅ የጨካኙን ቄሣርን ፈለጉ። ከአገራቸው ሰው ይልቅ የበአዳንን የግዛት ዘንግ ፈለጉ።

"ከዚህ በኋላ ጲላጦስ ሊፈታው ፈለገ፤ ነገር ግን አይሁድ፦ ይህንስ ብትፈታው የቄሣር ወዳጅ አይደለህም፤ ራሱን ንጉሥ የሚያደርግ ሁሉ የቄሣር ተቃዋሚ ነው እያሉ ጮኹ። ... ጲላጦስም፦ ንጉሣችሁን ልስቀለውን? አላቸው። የካህናት አለቆችም፦ ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም ብለው መለሱለት።" (ዮሐ. 9፥12-15)

ጲላጦስ እንኳ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ መሆኑን አወቀ። ከወንበዴዎች ጋር ታስሮ የመጣን አንድ ልጅ እግር የአይሁድ ንጉሥ እንደሆነ አወቀ። የካህናት አለቆች ግን ኢየሱስን ከልባቸው ይጠሉት ነበርና የቄሣርን ንግሥና ክፋት አልታያቸው አለ። እስራኤልን የሚያስጨንቀውን ቄሣር ከኢየሱስ ጋር አስተያይተው ቄሣር ተሻላቸው። ከአገሩ ሰዎች መልክተኞች



ውስጥ የኢየሱስን መንገሥ እንደማይፈልጉ የላኳቸው ዋናዎቹ የካህናት አለቆች ናቸው። ኢየሱስን በላያችን እንዲነግሥ አንወድም በማለት በጲላጦስ ፊት ካዱት። ይህን ኢየሱስን ከፈታኸው ከወዳጃችን ቄሣር ጋር ትጣላለህ በማለት በግብዝነት ማንነታቸውን ሸጡ። ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም። እግዚአብሔርም ንጉሣቸው አይደለም ማለት ነው። በአንደበታቸውም ጭምር የቄሣርን ንግሥና ተቀበሉት። "እኔን የሚጠላ አባቴን ደግሞ ይጠላል።" ዮሐ. 15፥23) በሕይወቱ የሚደንቀኝ ይህ ነው። ኢየሱስ አንድን ሰው ከስሶ አያውቅም። መታወቂያ ፊልሳ መንግሥት አካል አልመጣ፣ ቤት ንብረት ኃብት አላከማቸ። ነገር ግን በጥልቀት ይጠሉታል። ምን አደረጋቸው?

## 11.4. መንግሥት ይዞ መመለስ

"መንግሥትም ይዞ በተመለሰ ጊዜ፥ ገንዘብ የሰጣቸውን እነዚህን ባሪያዎች ነግደው ምን ያህል እንዳተረፉ ያውቅ ዘንድ እንዲጠሩለት አዘዘ። የፊተኛውም ደርሶ፦ ጌታ ሆይ፥ ምናንህ አሥር ምናን አተረፈ አለው። እርሱም፦ መልካም፥ አንተ በጎ ባርያ፥ በጥቂት የታመንህ ስለ ሆንህ በአሥር ከተሞች ላይ ሥልጣን ይሁንልህ አለው። ሁለተኛውም መጥቶ፦ ጌታ ሆይ፦ ምናንህ አምስት ምናን አተረፈ አለው። ይህም ደግሞ፦ አንተም በአምስት ከተሞች ላይ ሁን አለው።" (ሉቃ. 19፥15-19)

የአገሩ ሕዝብ ቢጠሉትም፣ መልክተኞችም በመላክ እንዳይነግሥባቸው ቢናገሩም፣ እርሱ ያለው አልቀረም። መንግሥት ይዞ መጣ ክፉቅ አገር መጣ ዓለም ወደደችም ጠላችም የእግዚአብሔር መንግሥት ይመጣል፤ በክብርም ይገለጣል። ሌላውን በሙሉ ሽሮ ብቻዋን የምትገዛበት መንግሥት ክርስቶስ ይዟት የመጣ መንግሥት ነች። አሁን በሚሥጢር የምትሠራው በገሃድ ብቻዋን ትገለጣለች።

መንግሥት ይዞ ሲመለስ ብዙ ክስተቶች እንደተፈፀሙ በዚህ ምሳሌ አልተነገረም:: ስለመንግሥቱ አቀባበል አልተገለጠም:: ነገር ግን መንግሥት ይዞ ሲመጣ የመንግሥቱ ጌታ ያ ወደ ሩቅ አገር የሄደው መኰንን ነው፣ እርሱ እራሱ መጣ:: ሲመጣ የጠየቀው ጉዳይ ቢኖር አደራ ሰጥቶ የሄደው ገንዘብ ጉዳይ ነው፤ ትርምስ የለም፤ ሌላ ጉዳዮችም የሉም:: ብዙ ሰዎችንም አልፈለገም:: ከአገር ሕዝብ መካከል የአሥሩ ባሪያዎቹን የንግድ ውጤት ለመስማት ፈለገ:: ይህን ለመስማት የሚፈልገው ደግሞ ሌሎች አይደሉም ወይንም በመልከተኛም አይደለም ከራሳቸው አንደበት ለመስማት አሥሩ ባሪያዎችን አስጠራ:: አሥሩም ባሪያዎች ተጠርተው መጡ እንጂ በንጉሥ አካባቢ አልነበሩም:: ንጉሡም እርሱን እንዲጠብቁት ሳይሆን ዋነኛ ፍላጎቱ በምናኑ እንዲነግዱና እንዲያተርፉ ነው:: ንጉሡ መንግሥትን ይዞ ሲመጣ በመጀመሪያ የፈለገው ነገር የአገሩን ሕዝብ ኑሮ፣ የባሮቹን ደኅንነት፣ የአቀባበሉን ድምቀት አልነበረም:: የባሮቹን የንግድ ታማኝነት ነበር::

የፊተኛው መልስ መኰንኑን አስደሰተው:: መኰንኑ የሰጠው ጥቂት ነገር ነው አንድ ምናን ነው:: ይህችው ምን ያህል እንዳተረፈ ማወቅ ነበር ይህ የፊተኛው በራሱ አንደበት አሥር እንዳተረፈ ነገረው:: መኰንኑ ሲሄድ ነግድ አለው ባሪያው ለተመለሰው መኰንን አተረፈ አለው:: ጥያቄውና መልሱ የሚገጥሙ ነበሩ:: ዝብርቅርቅ መልስ የለም:: ማመካኘትና ሰበብ የለም መልሱ በቀጥር የሚገለፅ ነበር:: የመኰንኑም ፍላጎት ባሮቹ ምናኑ ምን ያህል እንዳተረፉ በቁጥር እንዲገልጡለት ነበር:: "አሥር አተረፈ" ይህ መልስ መኰንኑን አረካው:: መኰንኑን በጠሉት አገር አሥር ማትረፍ ታማኝነትንና የዓላማ ፅናትን ይጠይቃል:: ይህ ባሪያ ብዙ ምክንያት ሊያቀርብ ይችላል ከምክንያቶቹ አንዱ ጌታ ሆይ ሕዝቡ አንተን ስለጠሉ ምናኑን ጠሉት ማለት ይችል ነበር:: ንጉሡ ይህን አውቆ እንዲነግዱ ያዘዘው እርሱ ስለሆነ ምክንያት አይቀበልም::



ይህ መኰንን መንግሥት ይዞ ሲመለስ ከመንግሥቱ ጋር አስተዳዳሪዎችን ይዞ አልመጣም:: የመንግሥቱ አለቃ የሆነው መኰንን አለ:: በግዛቱ የሚያስተዳድሩና የሚገዙ ግን የሚገኙት ከባሪያዎቹ መካከል ነው:: በዚህ ባለበት ዘመን የተረፈው ምናን መንግሥት ሲመጣ የግዛትን መጠን ይወስናል:: የተሰጠው ምናን ሳይሆን በተረፈው ምናን ልክ የሚገዙትም ከተማ ይወስናል:: የሚመጣውን መንግሥት ምን ይመስላል? በዚያ መንግሥት የሚኖረኝ ኃላፊነት ምን ይሆናል? በዚያ መንግሥት የስንት ከተማ አስተዳዳሪ እሆናለሁ? ብሎ መንግሥቱን መጠባበቅ የዋህነት ነው:: የሚመጣው የሚወስነው አሁን በእጅህ ባለው ምናን ይኸውም በትርፍነት የያዝከው ምናን ነው:: የፊተኛው ባሪያ መጥቶ አሥር ምናን አተረፈ ሲለው ዋናው የመኰንኑ መልስ አሥር ከተሞችን ግዛ አለው የሁለተኛውም እንዲሁ:: እንግዲህ ይህ ባሪያ አሥር ምናን በእጁ መኖሩን የገለጠለት እራሱ ባሪያው ነው:: በባሪያው እጅ ያሉ ምናኖች ለሚመጣው መንግሥት የከተሞች መክፈቻ "ቁልፍ" ነው:: አንድ ምናን አንድ ከተማን ይከፍታል:: ሁለት ምናን ሁለት ከተሞችን ይከፍታል በመሆኑም የሚመጣውን መንግሥት ከመጠበቅ በተሰጠው ምናም ማትረፍ እጅግ ብልህነት ነው:: አሥር ምናን ያተረፈው ባሪያ በመጀመሪያ ወደ መኰንኑ ቀርቦ መናገሩ ይህ ባሪያ የመንግሥቱን መገለጥ በቅድሚያ ይጠባበቅ ነበር: አንድም ያላተረፈው መጨረሻ መጣ በመሆኑም መንግሥትን መጠበቅ ማለት በተሰጠው ሥራ ላይ ተግቶ መጠበቅ ነው::

እጅግ የሚያሳዝነው ግን በዚህ መንግሥት ብዙ ከተሞች እያሉ ገዢዎች መታጣታቸው ነው:: አሥር ያተረፈው ሲመጣ መኰንኑ ወዲያውም አሥር ከተሞች አለው:: አምስትም ያተረፈውን በአምስት ከተሞች በማለት የመኰንኑን የመንግሥት ከተሞች ስፋት እናስተውላለን:: በጥቂቱ ታምኖ በብዙ መንገሥ እንዴት ክብር ነው:: "መንግሥትም ግዛትም ከሰማይም ሁሉ በታች ያሉ የመንግሥታት ታላቅነት ለልዑል

ቅዱሳን ሕዝብ ይሰጣል፤ መንግሥቱ የዘላለም መንግሥት ነው፥ ግዛቶችም ሁሉ ይገዙለታል ይታዘዙለትማል።" (ዳን. 7፥27) ይህ መኰንን ብዙ ከተሞች ቢኖሩትም ምናን ላላተረፋት ለመስጠት ምንም ፈቃደኛ አይደለም።

## 11.5. በጨርቅ የተጠቀለለ ምናን

"ሌላውም መጥቶ፦ ጌታ ሆይ፥ በጨርቅ ጠቅልዬ የጠበቅኋት ምናንህ እነሆ፤ ፈርቼሃለሁና፥ ጨካኝ ሰው ስለ ሆንህ፤ ያላኖርኸውን ትወስዳለህ ያልዘራኸውንም ታጭዳለህ አለው። እርሱም፦ አንተ ክፉ ባሪያ፥ አፍህ በተናገረው እፈርድብሃለሁ። እኔ ያላኖርሁትን የምወስድና ያልዘራሁትን የማጭድ ጨካኝ ሰው እንደ ሆንሁ አወቅህ ምን ነው ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ያልሰጠኸው? እኔም መጥቼ ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር አለው። በዚያም ቆመው የነበሩትን፦ ምናኑን ውሰዱበት አሥሩ ምናን ላለውም ስጡት አላቸው። ... እላችኋለሁ፥ ላለው ሁሉ ይሰጠዋል፥ ከሌለው ግን ያው ያለው ስንኳ ይወሰድበታል።" (ሉቃ. 19፥20-26)

ይህ ባሪያ በሁሉ መሥፈርት ውድቅ የሆነ ነገር ገጠመው፥ በመጀመሪያ ምናኑን በመደበቁ ከንግድ ውጭ ሆነ። በሁለተኛ ደረጃ መኰንኑን በተቃራኒ አቅጣጫ ተረዳው። ጨካኝ ሰው አደረገው የአገሩ ሰዎች እንኳ ያላሉትንና ያላሰቡትን ቃል ተናገረ። የአገሩ ሕዝብ ይጠሉታል እንጂ ጨካኝ ነህ ያለው አልነበረም። የገዛ ባሪያው ግን ጌታውን ጨካኝ ነህ አለው። በሦስተኛ ደረጃ ለብዙ ዘመን በእጁ የቆየችው ምናን ለባልንጀራው ተሰጠበት።

በዚህ ባሪያ መስፈርት ጨካኝ ማለት ያላኖረውን የሚወስድ ያልዘራውን የሚያጭድ ነው። መኰንኑ በመፍራቱ የማይሆን አመለካከትን ያዘ። ጌታውን የሚፈራው እንደ ጌትነቱ ሳይሆን እንደ ጨካኝ ንጉሥ ነው።



ጌታውን በተቃራኒው በመረዳቱ እድሉም ተቃራኒ ሆነበት። የተሰጠውን አደራ በራሱ አሳብ ደባልቆ ሳያተርፍ ቀረ። በጨርቅ ተጠቀለለ።

ያላኖረውን የሚወስድ ያልዘራውን የሚያጭድ መሆኑን መረዳቱ እንዳለ ሆኖ ሌላ አማራጭ መውሰድ ይችል ነበር። ይህ ገንዘብ ሳይነግድበት እንዲሁ ለለዋጮች (Bank) ቢያስቀምጠው እንኳ ያተርፍ ነበር። ሰውየው መሥራት ካልሆነለት በለዋጮች እጅ ቢያኖረው መልካም ይሆን ነበር።

አንዱ ምናን አሁንም ቢሆን ለባለ አሥሩ ተሰጠች። ይህ ፍርድ በአካባቢው የቆሙትን እንኳ ሳይቀር አስደነገጠ። መኰንኑ ይህን ይፈርዳል ብሎ የጠበቀው የለም። አሥር ላለው እንጂ ለባለ አምስቱ እንኳ አልተሰጠም።

ብዙ ባሪያዎችን ከታማኝነት ያስወጣው ዋናው መስፈርት የጌታቸውን ማንነት ባለመረዳታቸው ነው። ጌታቸውን የሚረዱበትን እውቀት ስለሌላቸው ክፍርድ በታች ይወድቃሉ። መነገድ እየቻሉ ጌታቸውን ጨካኝ ነው በማለት ሽባ ሆነው ይቀመጣሉ። መሥራት እየቻሉ ሳይነግዱ ይውላሉ።

ሌሎች እንዲነግዱበት ማድረግ እንኳ የባሪያው መብት ነበር። ምንም ጌታው ለአሥሩ ባሪያዎች አደራን ቢሰጥ ባሪያው መሥራት ካቃተው ገንዘቡን ለሌላ መስጠት ተገቢ ነው። ከመቋጠር ለለዋጮች መስጠት። ይህ ባሪያ በክፉዎች ተርታ ተመደበ። ጌታውን ጨካኝ በማለቱ እራሱ ክፉ ባሪያ ተባለ።

## 11.6. ጠላቶቼን አምጡልኝ ... እረዱአቸው

"ነገር ግን እነዚያን በላያቸው ልነግሥ ያልወደዱትን ጠላቶቼን ወደዚህ አምጡአቸው በፊቴም እረዱአቸው። ይህንም ከተናገረ በኋላ፥ ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጣ ይቀድማቸው ነበር።" (ሉቃ. 19፥27-28) አስቀድሞ የአሥሩን ባሪያዎችን ጉዳይ ጨረሰ። የገንዘቡን አለማትረፍ ተመለከተ።

# 12. መልካም ዕንቁ የሚሻ ነጋዴ

"ደግሞ መንግሥተ ሰማያት መልካምን ዕንቁ የሚሻ ነጋዴን ትመስላለች ዋጋዋም እጅግ የበዛ አንዲት ዕንቁ በአገኘ ጊዜ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ገዛት።" (ማቴ. 13፥45-46)

## 12.1. የዕንቁ ንግድ

መንግሥተ ሰማያት በተለያዩ ምሳሌዎች ትመሰላለች። እንደ እርሻ፣ መዝገብ፣ ሰናፍጭ ቅንጣት፣ በባሕር እንደተጣለ መረብ ወዘተ ... አሁን ደግሞ ሕይወት ካለው መካከል ሰውን መስላ ተገለጠች። ከሰው ውስጥም ነጋዴን ከነጋዴም የዕንቁ ነጋዴን ተመስላ ተገለጠች።

የዚህ ነጋዴ ሥራው መልካም ዕንቁን መፈለግና ማፈላለግ ነው። ከአገር አቋርጦ ሌላ አገር ይዞራል። ልቡና አእምሮውም በሙሉ ለዚህ ተግባር በማዋሉ በነፍሱ ዕንቁ ትልቁን ስፍራ ይይዛል። ሰውን ሲያገኝ መነጋገር የሚፈልገው የዕንቁን ጉዳይ ነው። ወሬ ሲሰማ የዚህን ጉዳይ በጥሞና ይሰማል፣ የነጋዴን ዓይነት ያውቃል፣ የዕንቁን ገበያና ፍላጎት ያውቃል ከበርቴዎችንም ያውቃቸዋል።

የአንድ አገርም እድገት የሚለካው ባላት ዕንቁ መጠን ነው። ገንዘቧን በእንቁ ትቀይራለች። የገንዘብ ዋጋ ሲዋዥቅ ዕንቁ ግን ሁል ጊዜ እየከበረ ይመጣል። አንድ አገር አንድ ዓይነት ዕንቁ በብዛት ስታመርት ሌላዋ ደግሞ ሌላ ዓይነቱን ታመርታለች፤ ለገበያም ያውሉታል። በመሆኑም የዕንቁ ገበያ አገር አቋራጭ ንግድ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ አገሮች በዕንቁና በከበረ ድንጋይ የሚነግዱ እንዳሉ የተለያዩ ነቢያት ተናግረዋል። የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 18 ስለ ባቢሎን ሲናገር የነጋዴዎችን የዕንቁ ንግድ እናገኛለን።



የዕንቁን ንግድ ልዩ ከሚያደርገው ነገሮች አንዳንዶቹ፦

1ኛ. ከፍተኛ የገንዘብ ልውውጥ ይደረግባቸዋል በመሆኑም ትርፉ ከፍተኛ በመሆኑ ነጋዴዎቹን ያበለፅጋል በሌላም መልኩ ተራ ነጋዴ በዚህ ንግድ መሳተፍ አይሆንለትም።

2ኛ. በትንሽ ቦታ ከፍተኛ ዋጋ ያለውን ዕንቁ መጫን ይቻላል። ነጋዴው ሲጓጓዝ አብሮ ከዕቃው ጋር መጓዝ ይችላል። በአንድ ጉዞ ከፍተኛ ዋጋ ያለውን ማምጣት በመቻሉ ተዛማች ወጪዎች አይበዙበትም። ለምሳሌ የዕንቁው ዋጋ 10 ሚሊዮን ብር ቢሆን ይህን ዕቃ ለማስጫን ለነጋዴው መጫፈሪያ፣ ምግብ፣ መኝታ ደግሞ 100 ሺህ ብር ቢገመት ተዛማጅ ወጪ አንድ በመቶ አካባቢ ይሆናል።

3ኛ. ግንኙነቱ ከከበርቴዎች ጋር ነው።

4ኛ. ዓለምን ማዞር የሚችል ከፍተኛ ንግድ ነው።

መንግሥተ ሰማያትም መልካም ዕንቁ የሚሻ ነጋዴን በመምሰሏ በተራ ጉዳዮች አትውልም ሁልጊዜ የመንግሥተ ሰማያት ምኞት በከበረ ዕንቁ ንግድ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ነው። የመንግሥተ ሰማይ ሰዎችም መለያቸው የከበረ ነገር ፍለጋ በመዋላቸው ነው። በርካሽ ጉዳይ አይውሉም። ዕንቁ ፍለጋ ቢሰማሩም ዕንቁን የመምረጥ ችሎታቸው በእጅጉ የተመሠከረላቸው ናቸው። በዕይታ ቢያመልጥ በክብደት እያመልጥም ከሆነ ነገር ጋር ሲጋጭ የሚሰጠው ድምፅ፤ አንዳንድ ጊዜም ከሆነ ነገር ጋር ሲታሽ የሚለዋወጠው መልክ ዕንቁን ከዕንቁ ይለያል። በሌላ መልኩም ይህን ዕንቁ ሊይዙ የሚችሉ ሰዎችን ተመልክቶ ዕንቁውን ማወቅ ይቻላል።

የመንግሥተ ሰማያት የዕንቁ ንግድ ዓይነት በመመሰልዋ ትርጉሙ ትልቅ ነው። በተድበሰበሰ ነገር መርካት አይኖርም። ሁልጊዜ ለደንበኞቿ የተሻለን ዕንቁ ለማቅረብ ስለምትጣጣር የተሻለ ፍለጋ ዓይነተኛ ዓላማዋ ነው። አንድ ዕንቁ ሲታይ ወዲያው መስፈርቱ ይህ ዓይነት ዕንቁ ከዚህ

ሰማያትም ሰው በሙሉ ትልቅ ዕንቁ የሚገኘው ሁሉን በመክፈል መሆኑን ልቦናው ያውቃል:: ትልቁን ዕንቁ በእጁ ከመግባቱ ቀደም ብሎ ወደ መሸጥ ተግባር ይመለሳል::

ይህ ነጋዴ ከሰዎች ዘንድ አንድ ነገር ይገጥመዋል:: ይኸውም ሞኝ ይባላል:: ከሰረ (Bankrupted) የከበረው ንግድ ስላላዋጣው ዕንቁውን ሁሉ ሸጠ:: ንብረቱን በሙሉ ሸጠ እንዲያውም ሁሉም በዓይኑ ቁራኛ እስኪጠብቁት ድረስ ሥራውን ይሠራል:: ማለትም ይህን ሁሉ የሚሸጠው አገር ለቅቆ ለመጥፋት ያሰበ ስለሚመስላቸው ዕዳም ካለበት ሁሉ እንዲመልስ ይጠይቁታል:: ለሰው ሁሉ ይልቅም ለቤተሰቦቹ አበደ እስኪሉት ድረስ ያለውን ይሸጣል:: ይህ ነጋዴ ያገኘው ዕንቁ ከሁሉ የበለጠ በመሆኑ ትልቅ ዕንቁ አገኘሁ በማለት መለከት አይነፋም:: ይህን ካደረገ ሁሉ ይወጻደሩትና መግዛት ይሳነዋል:: በመሆኑም ልቡን ለራሱ ብቻ ይጠብቃል:: እዚህ ላይ ትልቅ ሚና የሚሠራው ምሥጢር የመጠበቅ ችሎታው ይሆናል::

ይህች ዕንቁ አንድ ልዩ ውበትና ችሎታ አላት ይኸውም ከሌሎች ዕንቁዎች ጋር አብራ እንዳትደረደር ሌሎቹን በሙሉ አሽጣለች:: የዕንቁ መደርደሪያውም በመሸጡ አዲሱ ዕንቁ መቀመጫ የላትም:: ምን ላይ ትቀመጥ? የት ቦታ ትቀመጥ? በመሆኑም ትልቁ ዕንቁ መቀመጫ አጣ?

ዛሬም በነፍሳቸው ትልቅ ዕንቁ ያላቸው ሰዎች መደርደሪያ የላቸውም:: ከአዲሱ ዕንቁ በቀር ሌላ ንብረት የላቸውም:: እጅግ የሚያደናግጥ ነው:: ተራዎቹ ዕንቁዎች የከበረ መቀመጫ ሲያገኙ አዲሱ ዕንቁ ግን መቀመጫ የለውም:: የሚንከራተት፣ በሌቦች ዘወትር የምትቃኝ፣ የሁሉ ልብ ያረፈባት ነች::

በኤልሳዕ ዘመን አንዲት የነቢይ ሚስት የነበረች ባልቴት ነበረች ልጆቿም በባርነት እንዲገዙ ባለዕዳዎች ወሰኑባት:: ሁሉን ሸጠች ነገር ግን ይህ ነው የማይባል ዕቃ ቀራት ይኸው ባዶ ማድጋ ብቻ:: ይህም ነጋዴ ይህችን ዕንቁ ሲሸጥ ምናልባት የሚቀረው ባዶ ሸክላ ነው:: ይህን የከበረ



ዕንቁ የሚያስቀምጠው በዚሁ ሸክላ ዕቃ ብቻ ነው:: "ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን፤" (2ኛ ቆሮ. 4፥7)

ወደ እግዚአብሔር ስትቀርቡ ያላችሁ ነገር በሙሉ እየወደመ ሲመጣ መንግሥተ ሰማይ በእናንተው ሥራውን ጀምሯል:: ያለውን በመሸጥ የከበረን ዕንቁ ለመግዛ እየተጣደፈች መሆኗን እንዘንጋ:: ቶሎ ቶሎ የሚወድምባቸው የከበረችውን ዕንቁ ቶሎ በእጃ ለማስገባት የታቀደ ነው:: ከማልቀስ ይልቅ ደስታን ከብዙ ዕንቁዎች ይልቅ የመንግሥተ ሰማይ አንድ ዕንቁ ይሻለናል:: ጌታ ሆይ በእኔ ጉስቁልና አንተ ምን ታገኛለህ? በማለት ከጌታ ጋር ከምንከራከር ቶሎ ብለህ የኔን ጨርስና ዕንቁ ቤቷ ትግባ እንበለው:: ስንት የከበረ ዕንቁ በነፍሳቸው ያሉ ሰዎች በሚታይ ነገር ግን ባዶዎች አሉ? ስንት የከበረ የእግዚአብሔር ዕንቁ ያላቸው ሰዎች በዚህ ምድር ተቅበዘበዙ? የሚሰበኩበት መድረክ የላቸውም፣ የመሳፈሪያ ገንዘብ የሌላቸው ስንት ናቸው? በዓለም በሚታይ ዕንቁ ራቁታቸውን ሆነው የእግዚአብሔር ዕንቁ ግን በነፍሳቸው የታጨቀ ስንት ናቸው?

የእግዚአብሔር ነገር አንድ ነው:: "የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው፤ ማርያምም መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም አላት::" (ሉቃ. 10፥42) ጌታ ኢየሱስ የተናገረው አንድ ነገር ግልፅ ነው:: የእግዚአብሔርን ቃል ነው:: ነገር ግን የእግዚአብሔርም ቃል ቢሆን ከኢየሱስ ክርስቶስ እንደበት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚፈሰው ዕንቁ ነው:: እግዚአብሔር አብ የተናገረው ልጁን ስሙት ነው:: ጌታ ኢየሱስ ያለው ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ይነግራችኋል ነው:: ማርያምም የተናገረችው ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አንደበት የሚወጣውን የእግዚአብሔርን ቃል ነው:: "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው::" (ማቴ. 4፥4) በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን የእግዚአብሔን ቃል በማንበብ ብቻ የእግዚአብሔር ቃል ከእግዚአብሔር አፍ አይወጣም:: ነገር ግን መንፈስ

ቅዱስን ለማድመጥና ለመዝነት ነፍሳችንን ካስዝን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈሱ ከመጽሐፍ ቃል ይልክልናል:: ሕይወትን ይዘራል፣ መንፈሳችን፣ ነፍሳችንና ሥጋችን ሀሴት ያደርጋል ፍጥረትም ይናገራል::

የመንግሥተ ሰማይ ነጋዴ ሁሉን ፈልጎ መልካምን ዕንቁ በማግኘቱ አረፈ:: ክርስቲያንም ሁሉን ይፈልጋል በመጨረሻ በእግዚአብሔር ቃል ጥላ ሥር ያርፋል:: መብሉም፣ መጠጡም፣ ጨዋታውም፣ ውሎውም፣ ፍቅሩም፣ ፈቃዱም፣ ነፍሱም፣ መንፈሱም ሥጋውም ሁለመናውም በእግዚአብሔር ቃል ጥላ ሥር ይተዳደራል:: በብዙ ጭንቀት ሳይሆን በመመለስና በማረፍ ሰላም ይሆንለታል:: ታስቦ የተወለደው በእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ማረፊያው አባቱ ይሆናል ይኸውም የእግዚአብሔር ቃል ይሆናል:: እንደ ጌታ ኢየሱስ የመናገር ችሎታ ይኖረዋል:: "ይህም ሲሆን ሳለ ደቀ መዛሙርቱ፦ መምህር ሆይ፥ ብላ ብለው ለመኑት:: እርሱ ግን፦ እናንተ የማታውቁት የምበላው መብል ለእኔ አለኝ አላቸው:: ... የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውን እፈጽም ዘንድ ነው::" (ዮሐ. 4፥31-34)

ቅዱስ ጳውሎስ ይህችን አንድ መዝገብ ለማግኘት ያለውን ሁሉ ሸጠ:: "ስለ እናንተ እንደ ተሰጠኝ እንደ እግዚአብሔር መጋቢነት የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሜ እንድሰብክ እኔ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆንሁ፤ ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ ምሥጢር ነው፥ አሁን ግን ለቅዱሳን ተገልጦአል፤ ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው የዚህ ምሥጢር ክብር ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ ሊያስታውቅ ወደደ፥ ምሥጢሩም የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው::" (ቈላ. 1፥25-27) ይህንን ምሥጢርና ይህን በሌላ መልእክት ስለራሱ ሲናገር "አዎን፥ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ



ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቈጥራለሁ ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ፥ ... እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፥ በመከራውም እንድካፈል፥ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፥ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ::" (ፊልጵ. 3፥8-11) ይህን አሳብ ከተናገረ በኋላ እንኳ የዕንቁውን ፍለጋ ተያያዘው:: "አሁን እንዳገኘሁ ወይም ፍጹም እንደ ሆንሁ አይደለም፥ ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዝለሁ ብዬ እፈጥናለሁ:: ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቈጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ:: እንግዲህ ፍጹማን የሆንን ሁላችን ይህን እናስብ፤ ..." (3፥12-15)

# 13. አሥሩ ቈነጃጅት

## 13.1. መብራትና ዘይት

"በዚያን ጊዜ መንግሥተ ሰማያት መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን ሊቀበሉ የወጡ አሥር ቈነጃጅትን ትመስላለች። ከእነርሱም አምስቱ ሰነፎች አምስቱም ልባሞች ነበሩ። ሰነፎቹ መብራታቸውን ይዘው ከእነርሱ ጋር ዘይት አልያዙምና፤ ልባሞቹ ግን ከመብራታቸው ጋር በማሰሮአቸው ዘይት ያዙ።" (ማቴ. 25፥1-4)

በዚህ ምሳሌያዊ ንግግር ከአሥሩ ግማሹ ልባም ግማሹ ሰነፎች ናቸው። የልባምነትና የስንፍናው መስፈርት ግን አንድ ጉዳይ ነው። ለመብራቱ የሚሆን ዘይት የመኖርና ያለመኖር ነው። ዘይት ያለው ልባም ሲሆን የሌለው ደግሞ ሰነፍ ነው። ዘይቱ የሌላቸው ድሆች ሳይሆን የተባሉት ሰነፎች ናቸው። ሁሉ ዘይት መያዝ ሲችል ከስንፍና የተነሣ ዘይት ባለመያዛቸው ሰነፎች ተባሉ።

ሁሉም ቈነጃጅት ናቸው ሁሉ ሙሽራውን ለመቀበል የሚያስችል የተፈጥሮ ማንነት ይዘዋል። የውጭ ሰውነታቸውን አይቶ አንድስ እንኳ አይበቃም የሚል የለም። ሐዋርያው ጳውሎስ እናንተን እንደ ንጽሀት ድንግል ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁ በማለት ቅዱሳንን እንደ ቈነጃጅት ያስቀምጣቸዋል። ቁጥራቸውም ሙሉ ነው ያውም አሥር ናቸው።

ሁሉም መብራታቸውን ይዘዋል። መብራት አንድ ጊዜ ተገዝቶ የሚያልቅና የማይለወጥ በመሆኑ ሁሉ በዚህ አይወቀሱም። መብራት ሳይኖረው ሙሽራውን እጠብቃለሁ ቢል በአሥሩ ቈነጃጅት መዘበቻ ይሆናል ከሰነፎቹ እንኳ ያነሰ ነው። መብራት በእግዚአብሔር ቃል ይታወቃል። "ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው።" (መዝ. (119) ፥105) የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉን ይዟል። ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ያውቃል መዳን በሌላ በማንም እንዳልሆነ ያውቃል። ጌታ ኢየሱስ



የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ መሆኑን ያውቃል ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስን ዘይት አልያዘም። በተፈጥሮ አእምሮ ሁሉን ያቀናብራል፣ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን ይዟል። ሁሉ ክርስትናውን ያውቃል፣ ያስቀድሳል፣ ቆራቢ አባል ይሆናል፣ ይጾማል፣ ይጸልያል፣ አሥራት በኩራት ሰንበት የሚባሉትን በሙሉ ከልጅነቱ ጀምሮ ይጠብቃል።

የሁሉም ዓላማ አንድ ነው የዓላማ ጽናትም አላቸው። ሁሉም ሙሽራው ይመጣል በማለት ይጠብቃሉ። ከነዚህ መካከል አንድም ዘባች የለም። "በመጨረሻው ዘመን እንደ ራሳቸው ምኞት የሚመላለሱ ዘባቾች በመዘበት እንዲመጡ ይህን በፊት እወቁ፤ እነርሱም፦ የመምጣቱ የተስፋ ቃል ወዴት ነው? አባቶች ከሞቱበት ጊዜ፥ ከፍጥረት መጀመሪያ ይዞ ሁሉ እንዳለ ይኖራልና ይላሉ።" (2ኛ ጴጥ. 3፥3-4) ዘባች ማለት የሙሽራ መምጣትን የማያምኑ ሲሆኑ ሁሉ ነገር እንዳለ ይኖራል የሚል እምነት አላቸው። የመምጣቱን ተስፋ በተፈጥሮ ክስተት ንቀውታል። ብዙ ማስረጃን በማቅረብ ሙሽራውን መቀበል እንደማያስፈልግ ያምናሉ። በመሆኑም እነዚህ ከአሥሩ ውጭ ናቸው። ከልባምም ሆነ ከሰነፍ የማይመደቡ ዘባቾች ናቸው። አሥሩ ቈነጃጅት ግን አንድ ራእይ አላቸው ይኸውም "ማራናታ" ነው።

ሰነፎቹንና ልባሞቹን የለያቸው አላቂ የሚመስለው ዘይት ነው። ዘይት መብራት ከበራበት እየነደደ ይቀንሳል በመሆኑም ሁልጊዜ መሞላትን ይጠይቃል። ትልቁ ጥንቃቄ የዘይቱን ብዛት (Gauge) ተመልክቶ ከሚገኝበት መግዛትነው ።

ሰነፎቹ ዘይት አልያዙም ያልያዙበት ምክንያት ዘይት መግዣ ገንዘብ አጥሮአቸው አይደለም ምክንያቱም ሙሽራው ሲመጣ በነበረበት ሁካታ ወቅት ልባሞቹ እንዲሞሉላቸው ሲጠይቁ ወደ ውጭ ሂዱና ግዙ ተባሉ። በዚህን ጊዜ መግዣ ገንዘብ የለንም በማለት ማስረጃ አላቀረቡም። "ሊገዙም በሄዱ ጊዜ (ሰነፎቹ) ሙሽራው መጣ፥" (ቁ. 9) እንግዲህ ውጭ ሊገዙ

እንግዲህ ከአሁን ጀምሮ ዘይታችንን እያነደድን መጨረስ የለብንም። ዘይት ከሌላ ስፍራ ሳይሆን ከመንፈስ ቅዱስ እንጠይቅ። ከመብራታችን ጋር ማሰሮ እናዘጋጅ። በማሰሮም የቃሉን ታቦት የመታዘዝንና የቅድስናን ዘይት ሞልተን እንዘጋጅ። ሙሽራውም ቢዘገይ፣ እኛም እንቅልፍ እንቅልፍ ቢለን፣ ሙሽራው ይመጣል። ማንኛውም የተወለደ ሰው እንደሚሞት ሁሉ ወደ አብ ያረገው ሙሽራው ዳግም ይመጣል። የሰነፎች የልመና ጥሪ ያቆማል ሰነፍ ከልባም ይለያል። በቃል ጥበብ ሳይሆን ቃል ውስጥ ባለው ዘይት አንዱ ከሌላው ይለያል።

## 13.4. ቀንና ሰዓትን ማወቅ

“በኋላም ደግሞ የቀሩቱ ቈነጃጅት መጡና፥ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ፥ ክፈትልን አሉ። እርሱ ግን መልሶ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ አላውቃችሁም አለ። ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አታውቁምና እንግዲህ ንቁ።” (ማቴ. 25፥11-13)

ከዚህ በፊት በደጁ ቆሞ ያንኳኳ የነበረ ጌታ ዛሬ ደግሞ የተንኳኳባቸው ማንኳኳትን ጀመሩ። እርሱ ሲያንኳኳ እንቢ አሉ እነርሱ ራሳቸው ቢያንኳኩ እንኳ አልከፈት አላቸው። እንዲያውም እነርሱ ጌታ ጌታ ይሉታል እርሱ ደግሞ እናንተን አላውቃችሁም አላቸው። እናንተ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ ትሉኛላችሁ እንጂ እኔ አላውቃችሁም። ዘይት የሌለው ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ! ቢልም በጌታ ዘንድ አይታወቅም። ያለ ዘይት (ያለመንፈስ ቅዱስ ቅባት) የተደረገ ጌታ ሆይ በሙሉ ከሥጋ ነው። ከክፉ ነው እንዳይባል ክፉ ክርስቶስን ጌታ ነው አይልም።

እንግዲህ ጌታ በአንዱ ሌሊት ይመጣል። በመሆኑም ለሁሉ መልስ ንቁ ነው። የነቃ ተጠቀመ። መንቃት ማለት ሁለት ጉዳዮችን ያካተተ ተግባር ነው። አንደኛ እንቅልፍን ማሸነፍ ሲሆን ሁለተኛው ከመብራት ጋር ዘይትን በማሰሮ መያዝ ነው።



ስለዚህ ቃል አንዳንድ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ በመስጠት ጠበብቶች ገጥመውኛል። ጌታ ዘይት ሙሉ አለ እንጂ ስለ መንፈስ ቅዱስ መቼ ተናገረ። ቈነጃጅት የሚለው ማንን ነው? በማለት ሌላ ትርጉም ልንሰጥ አይገባንም ይላሉ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረንና የተሰፋ ቃል የገባልን ከመንፈስ ቅዱስ መሞላት ውጭ ምን አለ? የተስፋው መንፈስ፣ የአምላካችን መንፈስ፣ አጽናኙ መንፈስ፣ ዓለምን የሚወቅስ መንፈስ፣ ብርሃንና ሁሉን የምናውቅበትን መንፈስ ከአርያም፣ ከጸባኦት የምንጠብቀውና የምንኖርበት እርሱ ብቻ ነው። ነፍስን፣ መንፈስን በጸጋ የሚሞላ፣ ብርሃን የምንጎናጸፍበት፣ መንፈስና ሙሽራው “ና” ይላሉ የተባለበት ውህደት የተደረገው ከእርሱ ጋር ብቻ ነው። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በሐዋርያት ሥራ ጌታን ሲቀበል ደስ እያለው ወደ አገሩ ሄደ የተባለው ይኸው መንፈስ ብቻ ነው።

ይልቅም እኩለ ሌሊት የሆነበት ሌላው ምክንያት የብርሃን አድማስ በሙሉ ጭልም ባለበት አማካኝ ሰዓት ላይ ሙሉ ብርሃን የሆነው ጌታ ሲመጣ ብርሃኑን እንዲያደምቅለት ነው።

ሁሉ ነገር ከጨለመ በኋላ የሰው ልጅ ከሰማይ እንደሚገለጥ ቅዱስ ማቴዎስ ሲገልጥ “ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥” (ማቴ. 24፥29-30) እንግዲህ የሰው ልጅ ምልክት ከሰማይ ሲታይ በምድር ያለው አቀባበልን ይህ ወንጌል ሲያብራራ “በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል።” (ማቴ. 24፥30)

ሁሉ ለጠላት ጠቃሚ ነው። ማሳውን ቢኮትኩትና ቢጠብቅ እንክርዳድ ይበቅላል። ከዚህ በኋላ ሰዎቹ ቢነቁ ምንም ማድረግ አይችሉም።

የእግዚአብሔር መንግሥት ጠላት አለው ጠላቱም በሁለት ይከፈላል። ሰይጣንና ክፉ ሰዎች ናቸው። ሰይጣንን መጥላትና መቃወም ሲገባን ክፉ ሰዎችን ግን መውደድና መጸለይ አለብን። መጽሐፍም "ጠላቶቻችሁን ውደዱ" ተብሎ እንደተጻፈልን ሁሉ ይህን እናደርጋለን። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በተመላለሰበት ወቅት ዋነኛ ጠላቱ ሰይጣን ሳይሆን ፈሪሳውያንና ሰዎች ነበሩ። ሰይጣን ስለክርስቶስ ሲናገር "ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ማን እንደሆንክ አውቃለሁ" ብሎ ሲናገር በክርስቶስ መስቀል የነበሩ ፈሪሳውያን ጠላቶቹ ግን "የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ አላልክም እንግዲህ ከወደድህ ያውርድህ" አሉት ። ሰይጣን ኢየሱስን ቅዱስ ሲለው ፈሪሳውያን ግን በብዔል ዜቡል ሰይጣንን ያወጣል በማለት የክርስቶስን መንፈስ ሰደቡ። የጲላጦስ ሚስት ክርስቶስን በሕልም በማየት ለባለቤትዋ "ጲላጦስ በዚህ ቅዱስ ሰው አንድ ነገር እንዳታደርግ" በማለት ተናገረች። እስራኤል ግን ከክርስቶስ አገር አጥፊውን በርባንን ወደደ። ቢሆንም ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ (ሰዎችን)

"መኝታ" ዋነኛ የጠላት መሣሪያ ሆኖ የጌታው ሰዎች መተኛታቸውን ጠብቆ የሚዘራው እንክርዳድ ነው። ለጠላት መጠቀሚያ መኝታ ከሆነ አንድ ሰው ማማ አቋቁሞ የጠላትን ተግባር ከተከታተለ ሁልጊዜ ውጤታማ ይሆናል ።

በጌቴሴማኒ ጌታ ኢየሱስ ከሰይጣን፣ ከሞትና ከጨለማ ሠራዊት ጋር ሲታገል በደቀ መዛሙርቱ ላይ ከባድ እንቅልፍ ወደቀ። ሁሉ ቢተኙ እንኳ ስምዖን ጴጥሮስ ለአንድ ሰዓት እንኳ ይተጋ ዘንድ ተጠየቀ "ስምዖን ተኝተሃልን" ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ በማለት ይማልዳል። በእርግጥም ሁሉም ተኙ ሰይጣንም ዘርን ዘርቶ ሄደ። ስምዖን ጴጥሮስ



የሊቀካህናቱን ባርያ ጆሮ ቆረጠ፣ ሁሉም ትተውት ሸሹ። እርሱ የንቃ ጌታ ብቻ በስፍራው ከአባቱ ጋር ቆመ።

"ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና ነቅታችሁ ተቃወሙ" በእርሻው እንክርዳድ ምሳሌ የተኙት "ሰዎቹ" እንጂ አንድ ሰው ብቻ አይደለም ።

በማቴዎስ 25 ላይ ስለ አሥርቱ ቈነጃጅት በገለፀበት ቃል ላይ አሥሩም ተኙ ይላል። ሙሽራው በመጣ ጊዜ በእንቅልፍ ልባቸው ዘይት ብቻ በመያዛቸው ወደ ሰርጉ አዳራሽ ገቡ።

አንድ ክርስቲያን ወንድም በአንድ ወቅት ሲናገር "ለኢያሱ ታላቅ ፍርሃትና በኋላም ድል ያደረገው ዮርዳኖስን ነው። ለነቢዩ ሙሴ በፈርዖን ሠራዊት ፊት ሆኖ እጅግ ተጨንቆ ሲጮህ ኤርትራ ባሕር እንደተከፈለ ለዚህም ዘመን ክርስቲያን ደግሞ ታላቁ ዮርዳኖስና ኤርትራ ባሕር የሆነው የእንቅልፍ በሽታ (Sleeping sickness) ነው።" ሌባ በየትኛው ሰዓት እንደሚመጣ አታውቁምና ንቁ።

ነቢዩ ኤልያስን የሚያህል ታላቅ ነቢይ በተራራው አናት ወጥቶ ሦስት ታላቅ የነቢያትና የነገሥታትን ቅባት ይዞ ሲወርድ ባለበት ወቅት ከክትክታው ዛፍ በታች መጽሐፍ ተጋደመ ይላል። አንተም በፊት ለፊትህ ክብርና ቅባት ጌታ ካዋለህ እንቅልፍ ያይላል።

### 14.5. የመከር ጊዜና አጫጆች

ገበሬው የመከር ጊዜ ሳይደርስ ስንዴው ጎን የበቀለውን እንክርዳድ እንዲነካ አይፈቅድም። በእንክርዳድ ላይ ፍርድ የሚፈፀመው በመከር ወቅት ይሆናል። የመከሩ ጌታ በያንዳንዱ እንክርዳድ ላይ በተናጠል ቅጣትን አልወሰነም። ይልቅም እንክርዳድ በነዶ በነዶ ታስሮ ለእሳት እንዲዘጋጅ የመከር ጊዜ አጫጆችን አዟቸዋል።

እንክርዳዱ ያን ሁሉ ዘመን በማሳው ላይ እንዳልቆየና እንደተመቸው ሁሉ በአንድ ላይ ታስሮ ወደ እሳት የሚጋዝበት መኸር ወቅት አለው። ጠላት በሌሊት ቢዘራም፣ ሰዎቹ ቢተኙም፣ በማሳው ቢከርምም፣ የጌታውን ባሮች ቢያስቆጣም ለሁሉ ዘመን አለው። "ለሁሉ ዘመን አለው፥ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው ለመትከል ጊዜ አለው የተተከለውን ለመንቀል ጊዜ አለው።" (መክ. 3፥1-2)

በእስራኤል ነገሥታት ታሪክም ይህ የእንክርዳድና የስንዴው ተክል ተገልጧል። (የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ወይን ቦታ እርሱ የእስራኤል ቤት ነው። የደስታውም አትክልት የይሁዳ ሰዎች ናቸው) (ኢሳ. 5-7) በነዚህ በእስራኤልና በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ስንፈትሽ ብዙ ስንዴና የእንክርዳድ ዘር እናያለን። እንደነ አክዓብ፣ ኢዮርብአም፣ አካዝ የመሣሰሉት ለበዓልና ቀልጠው ለተሠሩ አማልክት ሲሰግዱ የሐሰት ነቢያትን ሲሰበስቡና እርሻን ሲያረክሱ ተገኙ። እንደነ ንጉሥ ዳዊት ኢዮሳፍጥ፣ ዓሳ፣ ኢዮአታም፣ ኢዮስያስ የመሣሰሉ ደግሞ በይሁዳና በእስራኤል ዘንድ ቅን ነገር ተገኝባቸው የስንዴ ምሳሌ ነበሩ።

እግዚአብሔር ለስንዴውና ለእንክርዳድ ቀን ቀጥሯል። አንዱ ወደ ጎተራ አንዱ ወደ እሳት ይጣል ዘንድ ለአጫጆች ትእዛዝ ይሰጣል።

ቅዱስ ጳውሎስ የመከሩን ጊዜ "ያ ቀን" ይለዋል ። "ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን በብርም በከበረ ድንጋይም በእንጨትም በሣርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ፥ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፤ በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፥ የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል።" (1ኛ ቆሮ. 3፥12-13)

የእግዚአብሔር ፍርድ በዚያን ቀን የሚከናወን ከሆነ እኛ ነገሮችን በፍርድ ለማጠናቀቅ በየጊዜው ለምን እንደምንነሣ አይገባኝም። ይህ ሰው ከቤተ ክርስቲያን ካልተወገደ በቀር ቤተ ክርስቲያኒቷ ምንም ፍሬ ማፍራት አትችልም በማለት እንክርዳዱን ለመልቀም እንነሳለን።



ይህ እንክርዳድ የተባለን ሰው ለመንቀል ብንነሳ ከሥሩ ብዙ መልካም ሰዎች ይኖሩታል። በመሆኑም መልካሞቹ አብረው ይነቀላሉ። ብዙ የታመኑ ክርስቲያኖች በአጭበርባሪና በዓለማዊ ክርስቲየን መሥሪያ ቤት ተቀጥረው ይሠራሉ። ይህ ሰው ከተነቀለ ከሥሩ ያሉትም መልካም ዘርን ይጎዳል ።

ማንኛውም የእግዚአብሔርን መንግሥት የምትጠብቅ ቤተ ክርስቲያን ልታደርግ የሚገባት በማንኛውም ወቅት ለክፉ ለቅቆ አለመገዛትና አለመተኛት ነው። ነገር ግን አንድ ጊዜ ተኝታ ክፉ ዘሩን በማሳ ከዘራ በኋላ የበቀለን እንክርዳድ ለመንቀል ጾም ጸሎት ወይም ትግል ማድረግ አይገባም። ብዙ መልካም ክርስቲያኖች በጌታ ማሳ እንክርዳድ በአብዛኛው በማየታቸው ቤተ ክርስቲያንን እየለቀቁ መሄዳቸው የታወቀ ሲሆን መደረግ ያለበት ግን ራስን ሳይነቅሉ ከእንክርዳድ ጋር አብሮ መዝለቅ በዚያን ቀን በጉ ከፍየሉ ' ይለያል። የእንክርዳድ እድል ፈንታ በአጫጆች እጅ (በመላእክት) ወደ ዘላለም እሳት የጌታም መልካም ዘሮች ወደ ዘላለም ጎተራ ይገባሉ። ጉባኤውም በዚህ ይፈታል።

# 15. በመንግሥትህ አስበኝ

"ከተሰቀሉት ከክፉ አድራጊዎቹም አንዱ፦ አንተስ ክርስቶስ አይደለህምን? ራስህንም እኛንም አድን ብሎ ሰደበው። ሁለተኛው ግን መልሶ፦ አንተ እንደዚህ ባለ ፍርድ ሳለህ እግዚአብሔርን ከቶ አትፈራውምን? ስለ አደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው፤ ይህ ግን ምንም ክፉት አላደረገም ብሎ ገሥጸው። ኢየሱስንም፦ ጌታ ሆይ፥ <u>በመንግሥትህ</u> በመጣህ ጊዜ አስበኝ አለው። ኢየሱስም እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።" (ሉቃ. 23፥39-43)

## 15.1. በሁለት ወንበዴዎች መካከል

በዚህ ቀን ሦስት ሰዎች ተሰቀሉ። ከእግዚአብሔር አብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመለኮት ዙፋን ይቀመጥ የነበረ የእግዚአብሔር ልጅ በዚህን ጊዜ ግን ከወንበዴዎች መካከል ገባ።

ከተሰቀሉት መካከል በመካከል መሰቀሉ ከሁለቱ ይልቅ ኢየሱስን ዓለም ዋነኛ አድርጋ ወሰደችው። ኢየሱስ በመካከል በመግባቱ እውነተኛውን ወንበዴ ንስሐ ከሚገባው ለየ። አንዱ ክፉዎች ጎን ሲቆም ሌላኛው ከበጎዎች ጎን ቆመ። ሰው እንደሚያይ እግዚአብሔር አያይም። ክፉ ተብለው ከተቆጠሩት መካከል አንዱ በጽድቅ ጎን ቆመ። ሦስቱን እንዲሰቀሉ የፈረዱ ሰዎች ሁሉን በክፉ ሲመድቡ ከተሰቀሉት መካከል ግን አንደኛው በጻድቃን መንገድ አቀና እንግዲህ ሰው የሚሰቅላቸው ከኢየሱስ ግራና ቀኝ ከቆሙት አንደኛው በጽድቅ ጎዳና ተገኝ።

ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል በሁለት ወንበዴዎች መካከል መሰቀሉ ዛሬም ኃጢአተኛ ከሚባሉት መካከል ቆሞ የግራና ቀኙን ማድመጥ



ይችላል። አንዱ የተሰቀለበት ዓመጽ እያለ እንደገና በመስቀል ላይ ኃጢአቱን ይጨምራል ኢየሱስንም ይሰድባል በመሆኑም ቁጭቱን በሙሉ በኢየሱስ ላይ ያከማቻል። ሁለተኛው ግን ያለ አማላጅ በቀጥታ የእግዚአብሔርን ልጅ በመማጸን በጽድቅ መንገድ ተገኘ።

## 15.2. በመንግሥት በመጣህ ጊዜ አስበኝ

ይህ ሁለተኛ ወንበዴ እጅግ የሚደንቅ ማንነት ያለው በመሆኑ በዚህ ፍርድ ሥር ወድቆ እጅግ የተረጋጋ አእምሮ ነበረው። የተፈጸመው ፍርድ በእርሱና በባልንጀራው ላይ ትክክል እንደሆነ ያውቃል። የእርሱን በደል ብቻ ሳይሆን የባልንጀራውንም ጭምር ያውቃል። ከሁሉ ያሳዘነው በመካከል የተሰቀለው ሰው ጉዳይ ነበር። ይህ እንደ እርሱ በመስቀሉ እንደ ወንበዴ ተቆጥሯል። በተለይም ሌላው ክርስቶስን ሲሰድብ አዘነ። ሌላው ተሳዳቢው ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ያውቃል፤ ነገር ግን ይሳደባል፤ በኃጢአት ላይ ኃጢአትን ይጨምራል። ሁለተኛው ግን የመጀመሪያውን ይገስጸዋል በዚህ ፍርድ ሥር ወድቆም ሳለ የመገሰጽ ጉልበቱ አልወደቀም።

ኢየሱስ በዚህን ሰዓት ከሁለቱ ወንበዴዎች ይልቅ በከፍተኛ ስቃይ ይገኛል። በመጀመሪያ ሰውነቱ የደከመ፣ በመከራና በጭንቀት በመኖሩ ኃይሉ እንደገል የደረቀ፤ ልቡም እንደሰም የቀለጠ፤ አጥንቶቹም የተለያዩ፣ የዓለምን ኃጢአት ተሸክሞ በራሳቸው በደል ከተሰቀሉት ጋር አብሮ ተደምሯል። ዓለም እውነተኛውን አዳኝ ከወንበዴዎች መካከል በማኖር ለማደናገር ሞከረች። የተሰቀለ ሁሉ ክርስቶስ አይደለም ማለትም ክርስቶስ በተሰቀለ ቀን የተሰቀለ ሁሉ ክርስቶስ አይደለም። በዓይን ሲታይ ሦስቱም አንድ ዓይነት ናቸው በእግዚአብሔር እይታ ሲታይ ክርስቶስ ብቻውን የእግዚአብሔር ልጅ ነው።

በዚህ በመስቀል ቀን የኢየሱስ መከራ ደግሞ ሌሎች ጉዳዮችን አስከትሏል አገርንና ከተማን ካወከ ከበርባን ይልቅ ኢየሱስ ይሰቀል!

ይሰቀል! በማለት በትንሹም በትልቁም ተነግሯል። ካህናት፣ ጸፎት፣ ፈሪሳዊ፣ ሰዱቃዊ እስራኤል ሁሉ ይሰቀል በማለት አብዝተው የጮኹበት ሰው ክርስቶስ ነው ብሎ ማመን አዳጋች ነው። ሁለተኛው ወንበዴ ግን ይህን አመነ። ምንም ሕዝቡ ሁሉ በተቃራኒ ቢቆሙበት፣ ምንም ወደ ሞት ቢሄድ፣ ምንም ወንበዴ ቢመስል ይህ ሰው የራሱ መንግሥት አለው በማለት አመነ። የኢየሱስ መንግሥት ሌላ እንደሆነ ያወቃል። ኢየሱስ "መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም" በማለት አስተምሯል ይህ ሁለተኛ ወንበዴም ይህንም አውቋል። ሐዋርያት ሲበታተኑ ይህ ሰው ግን በመስቀል ሆኖ ሳለ ስለ ክርስቶስ መንግሥት ይናገራል።

በመንግሥትህ አስበኝ ተብሎ የሚለመን እግዚአብሔርና ልጁ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። መልአክትንም ቢሆን፣ ሐዋርያትንም ቢሆን፣ ነቢያትንም ቢሆን ይህን ዓይነት ጥያቄ ወደ እነርሱ ሊመጣ አይቻልም ኢየሱስን ግን መጠየቅ ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱ መንግሥት ያለው ሲሆን በዚህ መንግሥት ሥር የሚተዳደር ሳይሆን አስተዳዳሪና ንጉሥ ነው። ይህ ዛሬ እርቃኑን ከእኔ ጋር የተሰቀለው ሰው መንግሥት አለው።

## 15.3. እግዚአብሔርን መፍራት

ይህ ወንበዴ በመስቀል ቆሞ የእግዚአብሔር ልጅ ከአጠገቡ እንደተሰቀለ አወቀ። አንዱ ሌላውን በዚህ መሰቀል ሥር ሆኖ እግዚአብሔርን መፍራት ያስተምራል። ወንበዴዎች እግዚአብሔርን መፍራት ተማሩ። ወንበዴ ወንበዴን ገሰጸ። ጻድቃን እግዚአብሔርን መፍራት በምቹ ጊዜ ሲሳናቸው፤ ወንበዴው በመስቀል እግዚአብሔርን መፍራት አስተማረ።

"የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው።" (ምሣ. 1፥7) እግዚአብሔርን የሚፈራ ደግሞ ከበነ ነገር ሁሉ እንደማይጎል መጽሐፍ ይነግረናል። ሁለተኛው ወንበዴ አገርን በድኋል እርሱም ይህ ፍርድ



እንደሚገባው አምኗል። ዓለም ተገቢውን ቅጣት ቀጥታዋለች። እግዚአብሔር ግን እርሱን በመፍራቱ ለዚህ ሰው ያስቀመጠለት ትልቅ በረከት ነው። የእግዚአብሔርን ልጅ በአጠገቡ አቆመለት። ኢየሱስ ዝም ብሎ ይሞታል። ይህ ወንበዴ ግን ይመሰክርለታል።

እግዚአብሔርን መፍራት ከሞት የበረታ ነው። ይህ ወንበዴ የመስቀል ሞት ላይ ቆሞ እግዚአብሔርን መፍራት ያስተምራል። ምንም በሞት ደጅ ቢቆምም እግዚአብሔርን መፍራት እንዳለበት ለራሱም ለሌላውም ያስተምራል።

በዚህ ዘመን በትንሽ መከራ ጉልበት ሰላም ሲጠፋ እግዚአብሔርን መፍራት አብሮ ይወድቃል። ይህ ሰው ግን እግዚአብሔርን መፍራት ከሞትም እንደሚበልጥ አወቀ። የማይነቃነቅ እምነት ይህ ነው።

## 15.4. ዳግም ምጽአት

አሁንም የሚደንቅ ቃል ከወንበዴው አፍ ወደቀ። በመንግሥትህ ሳይሆን ያለው "በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ" በማለት ዳግም ምጽአትን ገለጸ። ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱ መንግሥት እንዳለው አወቀ። ይህን መንግሥት ይዞ የሚመጣው ይህ ክርስቶስ እንደ ሆነ ተናገረ መንግሥትን ይዞ ለመምጣት በዚህ መስቀል እያለፈ እንደ ሆነ ተረዳ።

የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በዚህን ሰሞን ይናገሩ የነበሩትን ብናስተውል "በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በሥራና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ስለ ኢየሱስ፤ እርሱንም የካህናት አለቆችና መኳንንቶቻችን ለሞት ፍርድ እንዴት አሳልፈው እንደ ሰጡትና እንደ ሰቀሉት ነው። እኛ ግን እስራኤልን እንዲቤዥ ያለው እርሱ እንደ ሆነ ተስፋ አድርገን ነበር፤ ደግሞም ከዚህ ሁሉ ጋር ይህ ከሆነ ዛሬ ሦስተኛው ቀን ነው።" (ሉቃ. 24፥19-21)

ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ፥ እናንተም አልወደዳችሁም። እነሆ፥ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል።" (ሉቃ. 13፥34)

ይህ ሁለተኛ ወንበዴ ግን በክርስቶስ ውስጥ ገብቶ ከእግዚአብሔር ሰይፍ፣ ከነበልባሉና ከሚገለባበጠው ሰይፍ አመለጠ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ አስመለጠው። ሰውየው የሚመጣውን መንግሥት ሲጠብቅ ኢየሱስ ግን ይዞት ገባ። ኢየሱስ ውስጥ መግባት ማለት ገነት ውስጥ መግባት ነው። ወደ ገነት የሚገባው ከኢየሱስ ጋር ነው እንጂ በመልክተኛ አልነበረም።

ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትኖራለህ አለው። ይህ ቃል ብዙ ሰዎች ይጨነቁበታል። በዚያን ቀን ኢየሱስ ወደ ሲኦል ወረደ እንጂ እንዴት ገነት ገባ ይባላል? ሌላው ደግሞ እውነት እልሃለው ዛሬ ስለሚል ጌታ በዚህ በመከራ ቀን እንኳ እውነትን ለመናገር ወደ ኋላ አይልም ይላሉ። ትልቁና ዋናው ጉዳይ ግን ኢየሱስ የዚህን ሰው ነፍስ ተሸክሞ በዚህ ሰይፍ ውስጥ እያለፈ ነው ከዚያን ቀን ጀምሮ ይህ ሰው ምንም ሰይፍ አያገኘውም። ኢየሱስ በዚህ ሰይፍ ውስጥ እያለፈ ነው በመቃብር በሰይፍ እያለፈ ነው ከሦስት ቀን በኋላም በድል ተነሣ ሰይፍ አበቃ፤ ገነት ተከፈተ። በመሆኑም ከዚያን ቀን ጀምሮ ሰውየው ኢየሱስ ውስጥ ገባ ኢየሱስ ግን በሰይፍ አለፈ። ኢየሱስ ራቁቱን ነው ይህ ወንበዴ ደግሞ ጌታን በመንግሥት በመጣህ ጊዜ አስበኝ ጌታ ሆይ በማለት በራቁትነቱ አላፈረበትም። ሰውየውም ራቁቱን በኃጢአት ምክንያት ተሰቅሏል። ጌታ ኢየሱስም የዚህን ሰው ራቁትነት ሳይሆን ንስሐውን አከበረ። አዳምና ሔዋንም በራቁትነት በነበሩ ጊዜ እንዳልተፋፈሩ ጌታና ወንበዴውም በዛን ቀን የገነትን ያለመተፋፈር ማንነት ውስጥ ተገኙ።

ንጉሥ ዳዊት የእግዚአብሔር ልብ ያረፈበት ሰው ነበር። ኢየሱስም የዳዊት ዘርና ሥር ነው። አንድ ጊዜ እግዚአብሔር እስራኤልን ሊቀጣ ወደደ ንጉሥ ዳዊትንም የቅጣቱን ዓይነት ምረጥ አለው። "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የምትወደውን ምረጥ፤ የሦስት ዓመት ራብ፥ ወይም ሦስት



ወር የጠላቶችህ ሰይፍ እንዲያገኝህ ከጠላቶችህ መሰደድን፥ ወይም ሦስት ቀን የእግዚአብሔር ሰይፍ ቸነፈርም በምድር ላይ መሆንን፥ የእግዚአብሔርም መልአክ በእስራኤል ምድር ሁሉ ማጥፋትን ምረጥ፤ ... ዳዊትም ጋድን፦ እጅግ ተጨንቄያለሁ፤ ምሕረቱ ብዙ ነውና በእግዚአብሔር እጅ ልውደቅ፤ በሰው እጅ ግን አልውደቅ አለው።" (1ኛ ዜና 21፥11-13)

ዳዊት ከሦስቱ የቱን እንደሚመርጥ ችግር ሆነበት። ሦስቱም ተመጣጣኝ ነበሩ። ለምሳሌ ሦስት ወር የከፉ ሰይፍና ሦስት ቀን በመላእክት እጅ ያሉ ሰይፎች ውጤታቸው ተመሳሳይ ነው። ዳዊት ግን በእግዚአብሔር ታላቅ ምሕረት በመታመን የእግዚአብሔርን ሦስት ቀን ሰይፍ መረጠ ይህም ሰይፍ በመላእክት እጅ ገባ።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም በእግዚአብሔር ምሕረት በእግዚአብሔር ሰይፍ ሥር ወደቀ። ይህ ሰይፍ ሲመጣ ዳዊት እጅግ እንደ ተጨነቀ ኢየሱስም እጅግ ተጨነቀ። "ጴጥሮስንና ያዕቆብን ዮሐንስንም ከእርሱ ጋር ወሰደ፤ ሊደነግጥም ሊተክዝም ጀመረና፦ ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች በዚህ ቈዩ ትጉም አላቸው።" (ማር. 14፥33-34)

በዚህ ምክንያት ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ሞተ፤ ሦስት ቀንና ሌሊት በምድርና በመወርወሪያዋ ተዘጋ። በእግዚአብሔር ክብር በእግዚአብሔር ዙፋን ይቀመጥ የነበረ ንጉሥ በምድር ልብ ከከፉዎች ጋር ታገለ። በኛ ምክንያት የእግዚአብሔር ሰይፍ አለፈበት እኛም ከጠላት ሰይፍ ከራብና ከእግዚአብሔር ሰይፍ አመለጥን። የሕይወት ዛፍ ጋር ደረስን እጅ ዘርግቶ የሕይወት ዛፍ እንድንበላ እድል አገኘን። አራቱን የገነትን ወንዞች ጠማን ወርቅና የከበረ ድንጋይ ያለበትን የፊሶንን ወንዝ በረከት ተካፈልን። መጠበቅና ማበጀት ተግባራችን ሆነ።

ኢየሱስም በመንፈስ ድሆች ለሆኑ ብፁአን ናቸው ብሎናል። ብፅዕት ማርያምም በሉቃስ የመጀመሪያው ምዕራፍ ለትሁታን ጸጋ እንደሚሰጥና ባለጠጎችን ባዶአቸውን እንደለቀቀ ተናገረች። በአጭር ቃል ብዙ ትሁታንን ልንደርስና ካሉበት አዘቅት ማውጣት ሲቻል አውቆ ከጠመመ ጋር ጊዜን መፍጀት ተገቢ አይመስለኝም። በኢየሩሳሌም የነገሠ የሰባኪው የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ሲናገር "ጠማማ ይቀና ዘንድ አይችልም፤" (መክ. 1፥15)

ለምድር ሰዎች አሳብ ሲል የራሱን አይቀይርም። የእርሱ ፈቃድ በሰማይ በመሆኑ ምድራውያን ማድረግ የሚችሉት ፈቃዱን ማወቅ ብቻ ነው። ፈቃዱን ከተረዱለት የእግዚአብሔርን ማንነት ማወቅ ይቻላል። በምድር መስፈርት ሲመዘን ግን ሰማይ ከምድር እንደሚርቅ ነው።

ጠቢበኞች በምድር ሞልተው የዚህን ዓለም ሞኝ ነገር መምረጡ ደግሞም ያልሆነውን መምረጡ ይደንቃል። እነ ገማልያልን የመሰለ የሕግ መምሕራን እያሉ ዓሣ አስጋሪው የነበረው ጴጥሮስ የመንግሥት ሰማያትን ቁልፍ ሰጠው።

ኢየሱስ ክርስቶስ አንድያ ልጁ ሆኖ ሳለ በምድር ሲመላለስ እግዚአብሔር የቀሰፈው፣ የተቸገረ፣ የሕማም ሰው መስሎ ተገለጠ። ብዙ ምኩራቦች፣ መገልገያ መሣሪያዎች እያሉ ኢየሱስ አንድም ነገር ሳይሠራ በተሠሩት ነገሮች ገብቶ የአባቱን ሥራ ጨረሰ። ዓለም በሙሉ ፈጣሪን እናውቃለን እያሉ ሳሉ ኢየሱስ ግን ዓለም ላይ ተመላልሶ በደንብ ካስተወለ በኋላ ስለ ዓለም የእግዚአብሔርን እውቀት ኃይል ሲገልጥ "ጻድቅ አባት ሆይ፥ ዓለም አላወቀህም እኔ ግን አወቅሁህ እነዚህም አንተ እንደ ላክኸኝ አወቁ፤" (ዮሐ. 17፥25) ከዓለም ሕዝብ በእስራኤል ምድር ይኖሩ የነበሩ በጣት የሚቆጠሩ ደቀ መዛሙርቱ ብቻ አንድ እውቀት ነበራቸው ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የተላከ መሲህ እንደሆነ እንጂ ሌላ እውቀት አልነበራቸውም። እግዚአብሔርን ከፈቃዱ ጋር የሚያውቀው የለም።



የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚታወቀው መንግሥቱ ከመጣች በኋላ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ካልመጣች በስተቀር ፈቃዱን የሚያውቅ የለም።

እንደ ክርስትና እምነት ቀላል እምነት የለም። ውሉ ከጠፋ ደግሞ እንደ ክርስትና እምነት ውስብስብ የለም። የክርስትናን እምነት ቀላል የሚያደርጉት፦

◊ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ የሚፈፀም በመሆኑ
◊ የእግዚአብሔር ልጅ ለሰው ልጆች ሞቶ ፣ ደሙን አፍስሶ ተቀብሮ ከሙታን በመለየቱ። በመሆኑም ሁሉን የሠራ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኑ።
◊ ጉዞው የጽድቅ በመሆኑ የአእምሮ ወቀሳ ስለሌለው
◊ መጨረሻው በግልፅ የተቀመጠ በመሆኑ
◊ በሰው ሁሉ ፊት እኩል በመሆኑ
◊ በበረከት፣ በጥበብ፣ በእውቀት የተሞላ በመሆኑ
◊ ፍቅር ላይ የተመሠረተ በመሆኑ

የክርስትና እምነት ውስብስብ የሚያደርገው፦

◊ ከሰው አሳብ ፈፅሞ የሚቃረን በመሆኑ ሰማይ ከምድር እንደሚርቅ እንዲሁ የራቀ በመሆኑ ሁሉም ወደ ራሱ ፈቃድ መነተት ስለሚፈልግ
◊ በፈጣሪ መመራት እንጂ በራስ መመራትን ስለማይፈቅድ
◊ ክፉ መናፍስት ስለሚዋጋው
◊ ዓለምና ሥጋ ተቃራኒው ስለሆነች

በአጭሩ የክርስትናን እምነት ፈር የሚያስይዝ በሰማይ ያለውን እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። በሰማይ የተፈጸመው ፈቃድ በምድር እንዲደገም መለመን ይሆናል። ፈቃዱን አወቅን ማለት ሁሉ ቀለለ ማለት ነው። የፈቃዱ ቁልፎች ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልፀዋል። አሁን

የዕለት እንጀራ ሲባል ግን ለሁሉ አንድ ዓይነት ይሆናል ማለትን አያካትትም። በየዕለቱ ለአንድ አገር ሕዝብና ለሌላው በባህሉ በእንጀቱ መሸከም ልክ፣ በክብሩ መጠን ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ ለንጉሥ ሰሎሞን የዕለት ምግቡ መጽሐፍ ሲናገር "ለሰሎሞንም ለቀን ለቀኑ ቀለብ የሚሆን ሠላሳ ኮር መልካም ዱቄትና ስድሳ ኮር መናኛ ዱቄት፥ ከዋላና ከሚዳቋ ከበረሃ ፍየልና ከሰቡ ወፎች በቀር አሥር ፍሪዳዎች ሀያም የተሰማሩ በሬዎች አንድ መቶም በጎች ነበረ።" (1ኛ ነገሥ. 4፥22-23) ይህን ሁሉ እርሱ ይበላዋል ብሎ የሚያስብ አይኖርም ነገር ግን ይህ የዕለት ማዕድ ገበታው ላይ ይዘረጋል እርሱና በእርሱ ጊቢ የሚኖሩ የሚቀለቡት ነው። የሰሎሞን አባት ዳዊት አንድ ጠቦት በአንበሳ ተወስደብኝ በማለት ከአንበሳ ጋር ተጋድሎ ያደርግ ነበር። ልጁ ሰሎሞን ግን በየዕለቱ መቶ በግ በገበታው ታርዶ ይቀርባል በአጭሩ ይህን የዕለት መብል የመደበ እግዚአብሔር ነው። ሌላው ደግሞ እኔና ልጄ በልተን እንድንሞት ይህችን እንጨት እየለቀምን ነው የምትልም ሴት በነቢዩ ኤልያስ ዘመን ተገኘች። የሰማይን መስኮት መክፈትና መዝጋት የሚችል የበረከት ቁልፍ የነበረው ነቢይ ኤልያስ ቁራሽ እንጀራና ጥቂት ጽዋ ውሃ ለመነ ተብሎም ተጽፎአል። እንግዲህ የዕለት እንጀራችንን ዓይነትና መጠን ወስኖ ጌታ እግዚአብሔር ይሰጠን ዘንድ እንለምን። እየተመገብን አቅንተን የሌላውን እንመልከት።

## 16.7. ይቅርታ

"እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፤" (ማቴ.6፥12)

"ኃጢአታችንንም ይቅር በለን፥ እኛ ደግሞ የበደሉንን ሁሉ ይቅር ብለናልና፤" (ሉቃስ 11፥4)



"ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፥ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና፤ ለሰዎች ግን ይቅር ባትሉ፥ አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።" (ማቴ. 6፥14-15)

"ይህንንም ብሎ እፍ አለባቸውና፥ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው።" (ዮሐ. 20፥22-23)

የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ከሌላው የሚለየው ይቅርታ ማድረግ በመቻላቸው ነው። የሁሉ ነገር ትልቁ ጉልበት ይቅርታ ነው። የታላላቆችን ወገብ ጅማት የፈታው ይቅርታ ማድረግ ባለመቻል ነው። የመንፈሳዊ ጉልበት መለኪያው ይቅርታ ነው። መንፈስን እፍ ብሎ እንዲቀበሉ ያደረጋቸው እንኳ ከዚህ ጉዳይ ነጻ አይደሉም በመሆኑም ይህ ትምህርት በኢየሱስ በኩል መንፈስን የተቀበሉ በሙሉ መማር የሚገባቸው ነው።

### 16.7.1. እኛም ደግሞ

ይህ ሐረግ ግሩም ሲሆን የእግዚአብሔር መንግሥት ቁልፍ ነው። እኛ አድርገናል አንተ አድርግልን። የኛን ኃላፊነት ተወጥተናል፤ የአንተን በኛ ላይ ተወጣ። እኛ ታማኝ ሆነናል፤ አንተም ታመንን። እኛ ለድሆች እጅ ዘርግተናልና፤ አንተም ደግሞ ለኛ ዘርጋልን። እኛ ቃል አስተምረናል እኛን ደግሞ አስተምር። እኛ አንድ እርምጃ ሄደናል፤ አንተ ደግሞ በአንተ እርምጃ ተራመድልን። እግዚአብሔር ምንጊዜም ሥራውን የሚተገብረው የሰዎችን እርምጃ ተመልክቶ ነው። ሥራውን የሚሠራው የሰዎችን ሥራ አይቶ ነው። ይቅርታን በተመለከተም ይህ ነው። ሉቃስ ሲጽፍ "ይቅር ብለናል" የሚል ሲሆን ማቴዎስ ደግሞ "ይቅር እንደምንል"። የሉቃስ አባባል ወደ አንተ ሰው ለጸሎት ከመቅረቡ በፊት ይቅርታን አድርጎ ሰውየው ጨርሶ መቅረብ አለበት ነው። ማቴዎስ ደግሞ ሰው ሁሉ ጊዜ በመበዳደል ስለሚኖር የደቀ መዛሙርት ተግባር ሁልጊዜ ይቅርታ የተሞላ

ውስጥ ሰይጣን ገባ መግባቱ ችግር የለውም ችግሩ ግን በሰው ነፍስ ኃጢአት ገባ። ኃጢአትም በሞት ላይ ነገሠ ሰይጣንም፣ ኃጢአትም፣ ሰውም ከገነት ተባረሩ ባዶ ጊቢ ተጠበቀ። ኪሩቤል ሰይፍ ይዞ ሰው የሌለበትን ገነት ጥበቃ ተያያዘው። እግዚአብሔር ዘንድ ይኖር የነበረ ኪሩቤል መኖሪያው ምድር ሆነ በእግዚአብሔር ክብር ይኖር የነበረ ኪሩቤል የጥበቃን ሥራ ተያያዘ።

ከፈተና መዳን ማለት፡-

1. ሰይጣን የሚመጣበትን ዓላማ በግልፅ ማወቅ
   ለመግደል - ለማጥፋትና ለመስረቅ
2. ሰይጣንን ከሌሎች መለየት
3. የእግዚአብሔር ቃል የማይሻር መሆኑን ማወቅ
   እግዚአብሔር ከነገረን ሌላውን መተው
4. የእግዚአብሔርን ቃል ማስተዋል፣ መጠበቅ

16.8.2 የኢየሱስ ፈተና

"ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያቢሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው። አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ። ፈታኝም ቀርቦ፡- የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆን በል አለው። እርሱም መልሶ፡- ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው።" (ማቴ. 4፥1-4)

ከዚህ ቀን በፊት ሰይጣን የሰማው አንድ መልእክት (Information) አለ። ይኸውም በአደባባይ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ነበር። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የተነገረው በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ ሲጠመቅ ነበር። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ የእግዚአብሔር



ትልቁ ስጦታ እርሱን መስማት ነው። ኢየሱስን መስማት እግዚአብሔርን መስማት ማለት ነው።

ፈሪሳውያን፣ ጻፍት፣ ሰዱቃውያን እስራኤል በተሰበሰቡበት መድረክ እግዚአብሔር ለኢየሱስ መሰከረ። ምልክት ለሚወድ ትውልድ እግዚአብሔር ከሰማይ መሰከረ። የካህኑ የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ ለኢየሱስ መሰከረ። እነዚህ ሕዝቦች ይህን መቀበል ሲሳናቸው ሰይጣን እውነቱን አወቀ። በመሆኑም በምድረ በዳ ሲፈትነው "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ..." በማለት ነበር። ፈተናው በሥልጣኑ መጠን ነበር። ሰይጣን በአካል ተገኝቶ የመጨረሻውን ፈተና ኢየሱስን ፈተነ።

የመጀመሪያው ፈተና

የፈተናው መግቢያ እንጀራ ነበር። የሁሉ ፈተና መነሻ እንጀራ ነው። ይሁዳ ከኢየሱስና ከሐዋርያት ጉባኤ የተለየው ሰይጣንም የገባበት አንድ ጉርሻ እንጀራ ከበላ ወዲያ ነበር። ዔሳው ብኩርናውን የሸጠው ለአንድ መብል ነበር። አዳምና ሔዋን የተፈተኑት በመብል ነው "ብላ አትብላ" በሚል ነበር ። ከሰውነት ክፍል በአምላክነት ራሱን መድቦ የሚገኝ ሆድ ነው። "ሆዳቸው አምላካቸው ..." (ፊልጵ. 3፥19) ምላስ በብልቶቻችን መካከል ዓመፀኛ እንደሆነች ሁሉ ሆድ ደግሞ በብልቶቻችን መካከል እንደ አምላክ ራሱን ሰይሞ ቆሟል።

ሌላም ተጨማሪ የመጽሐፍ ክፍሎች ይህን አሳብ ያግዛሉ፡-

- የቤቴሉ ነቢይ የተገደለው በመብል ነበር። አትብላ ተባለ በላ። በዚህ ምክንያት አንበሳ መጣ አንበሳ ነቢዩን ገድሎ አህያው ከአንበሳ ጋር ቆመ ። አህያው በአንበሳው ፊት ሞገስን ሲያገኝ ነቢዩ ተገደለ። (1ኛ ነገሥ. 13) ሰይጣንም እንደሚያገሳ አንበሳ በመብል ዙሪያ ይዞራል።

የኢየሱስ መልስ ግን አሁንም ትክክለኛውን የእግዚአብሔርን ቃል በመምዘዝ ነበር። "ተብሎ ደግሞ ተጽፎአል።" የፈለገ እምነት ቢሆን ይህ እምነት እግዚአብሔርን የሚፈታተን እምነት መሆን የለበትም። ከቤተ መቅደስ ጫፍ ራስን በመወርወር ሳይሆን ሰዎች ወይንም ክፉ ሲወረውርህ ነው ይኸውም በመንገድህ ሳለህ ነው። በእግዚአብሔር መንገድ ቆመህ ሌላው ቢወረውርህ ይህ ቃል ቦታውን ይዟል። በዚህ የእግዚአብሔር ቃል ከእምነትም በላይ ነው። እምናለሁ ራሴን እወረውራለሁ ሳይሆን የእምነትን ጌታ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በዚህ ጉዳይ ምን ይላል ማለት ነው።

ሦስተኛ ፈተና

"ደግሞ ዲያቢሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው፥ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውን አሳይቶ፦ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው። ያን ጊዜ ኢየሱስ፦ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው። ያን ጊዜ ዲያብሎስ ተወው፥ እነሆም፥ መላእክት ቀርበው ያገለግሉት ነበር።" (ማቴ. 4፥8-11)

መላእክት ቀርበው ማገልገላቸውን መመልከት እንችላለን። ከዚህ ፈተና በፊት የመላእክትን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ የቀረበ ፈተና ነበር። እግዚአብሔር መላእክትን ይልክልህ ዘንድ ራስህን ወርውር አለው። ኢየሱስም ይህ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ የሆነ የመላእክት እርዳታ ነው በማለት መለሰለት ይህን ፈተና በማለፉ መላእክት ለአገልግሎቱ ተላኩለት። እግዚአብሔርን ባለመፈታተኑ በእግዚአብሔር ፊት ፈተናውን አለፈ። ጌታ ኢየሱስ ከክፉው ጋር እጅግ ረጅም ተራራ ላይ ወጣ ይህ ተራራ የዓለምን መንግሥታት የሚያሳይ ተራራ ነበር። መንግሥታትን ብቻ ሣይሆን ክብራቸውንም አሳየው። ጌታ ኢየሱስ ለሰው ልጆች ይህን ያህል ተራራ ወጣ። ከዮርዳኖስ ወንዝ የዓለም መንግሥታት የሚታዩበት ተራራ ላይ ወጣ።



በዳንኤል መጽሐፍ አንድ ድንጋይ እጅ ሳይነካት ከተራራ እንደምትወርድና የዓለምን መንግሥታት እንደምትፈጅ አሳይቶናል። አሁን ደግሞ ከነዚህ መንግሥታት ክብር ለመቀበል በዲያብሎስ እግር እንዲወድቅ ተመኘለት። "ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?" የመጀመሪያዎቹ ሁለት ፈተናዎች ለሰይጣን ቃል መገዛት ሲሆን የሦስተኛው ግን የከፋ ነው። የዓለም መንግሥታትና ክብራቸውን ለማግኘት ሰዎች በሰይጣን እግር እንደሚደፉ ሁሉ ይህን ወደ እግዚአብሔር ልጅ አዞረው። ዛሬስ የዓለምን መንግሥት ክብር ሳይሆን ተራ ቁሳቁስና ክብር ለማግኘት ሰይጣን ሳይጠይቃቸው ካልሰገድንልህ በማለት እነርሱ ከርሱ ዘንድ የሚሄዱት ህልቆ መሳፍርት ናቸው።

ከሁሉ ፈተናዎች በዚህን ወቅት ኢየሱስ በጣም አዘነ። በመሆኑም ሂድ አንተ ሰይጣን የሚል ቃል ተናገረ። (ክርስቲያን ሂድ በኢየሱስ ስም አንተ ሰይጣን እንደምንለው ነው) ወደ ረጅም ተራራ መውጣት ማለት እጅግ ጥንቃቄን ይጠይቃል ወድቆ መስገድ ማለት ማምለክ ነው። ማምለክ ደግሞ የተባለው እግዚአብሔርን ብቻ ነው። ቅዱሳን የተለያዩ መንግሥታትን ማየት ሲጀምሩ የዚያን ጊዜ ትልቅ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

ጌታ ኢየሱስና ሰይጣን የተለያዩት በተራራ ነው። በመሆኑም በእግዚአብሔር ፈቃድ ይህ ግንበኞች የናቁት የማዕዘን ድንጋይ ከተራራ የሚወርድበት ዘመን ይመጣል። በዚህን ጊዜ ዓለምና ነገሥታቶችም በሙሉ ይፈጫሉ፣ ይደቅቃሉ፣ ለሰማይ ነፋሳትም ይበተናሉ። ጌታ ኢየሱስ የዓለምን ክብርና መንግሥታት ውበት ሳይሆን ልቡ የገባው ማፍረስና ማድቀቅ ነበር።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም መንግሥታት ወደዱም ጠሉም ትንሹ ከተራራ የወረደው ድንጋይ ተራራ እንዳከለ እርሱም (ጌታ) የዓለምን ክብር በሙሉ አጠቃልሎ ይቀበላል ሁሉም በግምባራቸው ይደፉለታል።

# 17. ሕፃናትና የእግዚአብሔር መንግሥት

"እንዲዳስሳቸውም ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱም ያመጡአቸውን ገሥጹአቸው። ኢየሱስ ግን አይቶ ተቈጣና፥ ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉ አትከልክሉአቸው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና። እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አላቸው። አቀፋቸውም እጁንም ጭኖ ባረካቸው።" (ማር. 10፥13-16)

## 17.1. በወንጌል ተደጋጋሚ ጥቅስ

ሕፃናትና የእግዚአብሔር መንግሥት በተመለከተ በማቴዎስ፣ በማርቆስና በሉቃስ ወንጌላት ተጠቅሶአል አንዳንድ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በአራቱም ወንጌላት ተጠቅሰዋል። ለምሳሌ መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ ራሱን ይካድ የሚል ትምህርት በአራቱም ወንጌላት ከስድስት ጊዜ በላይ ተጠቅሰዋል።

የኢየሱስ ከድንግል ማርያም መፀነሱን የሚጠቅሱ ቅዱስ ማቴዎስና ሉቃስ ናቸው። የሞቱንና ቀብሩን ግን አራቱም ወንጌላት በግልፅ አስቀምጠዋል። የትንሣኤውን በሰፊው ተብራርቶ በአራቱም ወንጌላት ተጠቅሰዋል። በመሆኑም ወንጌል በተደጋጋሚ የሚናገረውን ልብ ማለት ለተግባራዊነቱም መሰለፍ ዓይነተኛ ተግባራችን ሊሆን ይገባል።

## 17.2. የኢየሱስ ቁጣ

ሕፃናትን በተመለከተ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የተለያየ ግንዛቤ ነበራቸው። በሕፃናት ጉዳይ የነበራቸው አሳብ ፍፁም ከኢየሱስ ጋር የሚቃረን ሲሆን ሕፃናቶች ከተነኩ ኢየሱስ ይቆጣል። የኢየሱስ ቁጣ ደግሞ ሕፃናት ከበረከት እንዳይጎድሉ ነበር። ይህም ብቻ ሣይሆን የመንግሥተ



ሰማይ ባሕሪና የሕፃናት ባሕሪይ አንድ በመሆኑ ኢየሱስ ይህን ጉዳይ አስተምሮ አለፈ ።

ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን የሚያከብሩ መስሎአቸው ሕፃናትን ይዘው የመጡትን ገሥፁ እነዚህ ደቀ መዛሙርት ደግሞ ቁጣና ግሣጼ ከኢየሱስ እንደበት ገጠማቸው። እግዚአብሔርን ለማክበር እግዚአብሔርን ማስቆጣት ሆነባቸው። የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የእግዚአብሔርን መንግሥት አሳብ ሳይገባቸው ሕፃናትን አራቁ። ሕፃናት መቀበል ማለት ኢየሱስን መቀበል ማለት ነው። ኢየሱስ የሕፃናት ወዳጅ ነው። ሕፃናት ወደ እርሱ የሚመጡበት በንፁህ ልብ ነው ይህን ልብ ደግሞ ኢየሱሰ ይወደዋል ይህን ሕፃን መገፍተር ኢየሱስን ያስቆጣል።

## 17.3. ሕፃናት

ሕፃናት ዩተወደዱበት ዋናው ምክንያት የመቀበል ችሎታቸው ሲሆን አባታቸውን ወይንም እናታቸውን ይቀበላሉ። የወላጆችን ፍቅር እንዳለ ይቀበላሉ። አባታቸው አንድ ነገር ከተናገረ ሁሉ እንዲሆን ያምናሉ ፍፁም ጥርጣሬና ግብዝነት የሌለው እምነት በወላጆቻቸው አላቸው ወላጅ የሰጣቸውንም ይቀበላሉ። ከሁሉ የሚበልጠው ወላጃቸው ነው ወላጅ በአጠገብ ቆሞ በሌላ እጅ መቆየት አይፈልጉም። በሞግዚት እጅ ውለው እናታቸው ወደ ቤት ከገባች ወዲያው በመሮጥ ወደ እናታቸው ይሄዳሉ። ስለዚህ አይደል ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ሕግና ጸጋ ሲናገር ሕግ ሞግዚታችን ሆና ወደ ጸጋ አቀረበችን።

መንግሥተ ሰማይም አንድ ባሕርይ አላት። ሕፃን እናቱን እንደሚቀበል መንግሥተ ሰማይም እንደ እናት ልጆችዋ በሙሉ እምነት እንዲቀበሉአት ትሻለች። መንግሥተ ሰማይ ብቻዋን ለልጆችም እናት በመሆንዋ የምታቀርበውን በሙሉ መቀበል ከፍተኛ ኃላፊነትን ይጠይቃል ጥርጥርን፣ ግብዝነትን፣ ማወዳደርን አትፈልግም። ሁሉ እርሷን በሙሉ ፈቃድ

እንዲቀበሏት ትሻለች። ንፁህ ልብን፣ ይቅርታን፣ ራስን ማዋረድን ትጠይቃለች።

የሕፃናት ባሕርይ ብዙ ነው። ትልቁ ግን ራስን ማዋረድ መቻላቸውም ነው። "እንግዲህ እንደዚህ ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ፥ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው።" (ማቴ. 18፥4) ይቅርታን በተመለከተ ሕፃን ራሱን ያዋርዳል አንድ ሰው ሕፃንን ቀጥቶ ሕፃኑ እንባው ሳይደርቅ መታረቅ ይቻላል። እንባው ዓይኑ ላይ እያለ ወደ ቀድሞው ፍቅሩ ይመለሳል። ሰባት ጊዜ ሰባ ይቅርታ ሊያደርግ የሚችል ሕፃን ብቻ ነው። በደልን የማይቆጥር ሕፃን ብቻ ነው። ሕፃን ወላጆች የሚሰጡትን ስጦታ ለመቀበል ራሱን ያዋርዳል ራሱን ዝቅ ያደርጋል። አንድ ዳቦ ቢወረወርለት መሬት ተንከባሎ ያነሣል የተሰጠውን ስጦታ ለመቀበል እስከ መጨረሻ ራሱን ያዋርዳል። የተሰጠውን መብል ለመብላት በመሬት ይቀመጣል ለሕፃን ዋነኛው ነገር የተሰጠውን ያከብራል ያደንቃል።

የእግዚአብሔርን መንግሥት ከሌላ መንግሥታት ጋር ማወዳደር፣ የመንግሥትን ስጦታ ከሌላ ስጦታዎች ጋር ማነፃፀር ፈፅሞ አይቻልም። ሕፃን ልጅ እናቱን የሚያፈቅረው ወይንም የሚቀበለው የእናትየዋን ማንነት ተመርኩዞ አይደለም። አጭር፣ ረጅም፣ ቀይ፣ ጥቁር፣ ደሀ፣ ሀብታም ወዘተ ውድድር ውስጥ አይገቡም። እናቱ በመሆንዋ ብቻ ከዓለም ሴቶች በሙሉ ለዚህ ሕፃን ትበልጥበታለች። የእናቱ ድምፅ ብቻ የሚሰማበት ልዩ ጆሮ አለው። ሕዝብ በተከማቸበት ስፍራ እናቱን ካገኘ ሁሉን አቋርጦ ሂዶ በእናቱ ጉያ ይገባል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ስጦታዎቹን ከሌሎች ጋር ማወዳደር አይቻልም። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመንግሥተ ሰማይ ንጉሥ ነው። ይህን ጌታ እንደ እናት፣ አባት፣ እህትና ወንድም በብቸኝነት እንድንመለከት የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ነው። ድምፁን ከሌሎች መለየት ይገባል። ሕፃን የእናቱን ድምፅ እንደሚቀበል እኛም የጌታን ድምፅ ልንቀበል ይገባል።



ለምሣሌ ሕዝቡን ሁሉ ሰበሰበ ሦስት ቀን ያህል አስተማረ ሁሉ ዳቦና ዓሣ በሉ የሚል ቃል ያልሰማ ይኖራል ብዬ አልገምትም እስኪ በዚህ ዘመን ያለውን ሕዝብ እንመልከት ማነው ወንበር በሌለበት ሣር ላይ ያን ያህል ተቀምጦ የሚሰማ? ምግቡ ዓሣና ዳቦ ብቻ ወደሚሆንበት ስፍራ ሂዶ የሚመገብ ወይንም ከአሀያና ከአሀያይቱ ውርንጫ ኋላ ኋላ እየሮጡ ወደ መቅደስ ሆሳዕና እያለ የሚገባ?

የጌታ ስጦታ በዝማሬ ሲገለጥ ሕዝቡ ምን ያስጮኸዋል ይባላል። ቀስ ብሎ ሲዘምር ምን የፈዘዘ ዝማሬ ነው ይባላል። እንግዲህ እንደ ሕፃናት ካልተመለስን ብንፆም፣ ብንጸልይና ብንመሠክር የእግዚአብሔር መንግሥት የኛ አትሆንም። ሕፃን ልጅ ማንንም አይተችም የራሱንና የጓደኞቹን ፍቅር ይዞ ያድጋል።

ከሕፃናት ባሕርይ የማይወደዱም አሉ ራስ ወዳድነትን በሰፊው እንመለከታለን። ሕፃን ሌላ ልጅ ሲወለድ ቅር ይለዋል። ፍቅሩን ስለሚሻሙበት ለሕፃኑ ትልቅ ትግል ነው። ሌላው ሁሉን ዕቃ ሰብስቦ የእኔ ነው ማለት አለ። በተጨማሪም የተመለከቱትን ነገሮች በሙሉ አሁን እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ። በመጀመሪያ እነርሱ መንካትና መቅመስን ይፈልጋሉ።

ሌላ ብዙ መልካም ባሕርያት አሉአቸው። ይህም መንግሥተ ሰማያት ከሰዎች ማግኘት የምትፈልገው ዓይነት ነው። ሕፃን ለነገ አይጨነቅም። ነገ አባታቸው ያመጣላቸዋል ሲጨዋወቱ፣ ሲጣሉ፣ ሲዋደዱ አንዱ ከአንዱ አይለዩም። የተጣሉበትና የሚስማሙበት ጉዳይ የታወቀ ሲሆን መልሰው ኅብረትን ያደርጋሉ። የሕፃንነት ወቅት አልፎ ወደ ወጣትነት ሲሸጋገሩ ሁሉ ቀስ በቀስ ይቀየራል።

ነበር:: የተገለጠውም የእግዚአብሔር ፈቃድ ሲሆን ይኸውም ለሕፃናት ነው:: አብ ወልድን ወልድም አብን ያውቃል:: አንዱ አንዱን ይገልጣል:: የሚገልጠውም ለሕፃናት ነው::

የክርስቶስ ደስታ የሰው ልጅ አብን ሲያውቅ ነው:: አብን ለማወቅ ክርስቶስን ማወቅ ነው:: ክርስቶስ ደግሞ አብን ይገልጣል ይኸውም በሕፃንነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የተዘጋጁትን ነው::

ደቀ መዛሙርቱ በደስታ ተመለሱ:: በደስታ ተመልሰውም የሆነውን ጉዳይ በሙሉ ለኢየሱስ ነገሩት:: ኢየሱስም በዚህ ሳይሆን ስማችሁ በመንግሥተ ሰማያት በመጻፉ ደስ ይበላችሁ በማለት የደስታ መስመርን አመለከተ:: እነዚህ ደቀ መዛሙርት ጥበበኞችም አስተዋዮችም ሳይሆኑ ሕፃናት ነበሩ:: መንፈሳዊውን ዓለም እንደ ሕፃናት የተቀበሉ ነበሩ:: የልባቸውን ፈቃድ ለዚህ መንግሥት አስገዙ:: እነርሱ ደስ አላቸው ጌታም ሐሤት አደረገ:: የደቀ መዛሙርት እንደ ሕፃናት መሆን ኢየሱስን በደስታ አዘለለው::

"ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን" በማለት በየዕለቱ እንጸልያለን:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ደግሞ መገለጥ ነው:: መገለጥ ማለት አብ ወልድን ወልድም አብን ሲገልጥ ነው:: የቤተልሔም እረኞች መገለጥም ይህንኑ ያብራራል:: "እንግዲህ እስከ ቤተ ልሔም ድረስ እንሂድ እግዚአብሔርም የገለጠልንን ይህን የሆነውን ነገር እንይ ተባባሉ:: ፈጥነውም መጡ ማርያምንና ዮሴፍን ሕፃኑንም በግርግም ተኝቶ አገኙ:: አይተውም ስለዚህ ሕፃን የተነገረላቸውን ነገር ገለጡ:: የሰሙትም ሁሉ እረኞች በነገሩአቸው ነገር አደነቁ፤" (ሉቃ. 2፥15-18) መገለጥ ለእረኞች ሆነ:: እረኞቹ ያሳዩ የነበሩት መታዘዝ እንደ ሕፃናት ነበር:: የፈሪሳውያን፣ የጠቢባን፣ የጸፍትና፣ የሰዱቃውያን በነበሩበት ምድር የክርስቶስ መወለድ ለእረኞች ተገለጠ::



በመጽሐፍት ቃል የዘላለም ሕይወት አለን ብለው ያመኑትን አልፎ የእግዚአብሔር መልአክት በሜዳ ያድሩ ዘንድ ተጠጉ:: የእረኞቹ ንግግር አንድ ነበር እግዚአብሔር የገለጠልንን ይህን የሆነውን ነገር እንይ በማለት እርምጃ ወሰዱ:: ዮሴፍ ማርያምና ሕፃኑን አገኙ:: የተናገሩት ግን ስለ ሦስቱ ሳይሆን ስለ ሕፃኑ ነበር:: የሰሙትም የተደነቁት በሕፃኑ ኢየሱስ ነበር::

የእግዚአብሔር ፈቃድ ኢየሱስን መገለጥ ነው:: መገለጥ ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ባለበት ሁኔታ መመልከት ነው:: የእግዚአብሔር እውቀት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን ለሕፃናት ገለጠ ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆነ:: ፈቃድህ በምድር ትሁን ብለን መጸለይ ከተፈለገ እንደ ሕፃን ለእግዚአብሔር መገዛት ነው:: እረኞች፣ ደጅ ያደሩ በአንድ ልብ የሆኑትን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ደጅ ቀረቡ:: የእግዚአብሔር ትልቁ ስጦታ መገለጥ ሲሆን ስምዖን ጴጥሮስን ብጹዕ ነህ ያሰኘው አብ ለጴጥሮስ ወልድን ስለ ገለጸለት ነው:: የኢየሱስን ማንነት በማወቁ የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ ተሰጠው::

ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ። በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፥ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፥ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ።" (2ኛ ቆሮ. 11፥23-27) አጠቃላይ የሐዋርያትን ኑሮ ይኸው የምናከብረው ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጠው "ለዓለምና ለመላእክትም ለሰዎች መጫወቻ ሆነናልና፤ እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያቱን ሞት እንደ ተፈረደባቸው ሰዎች ከሁሉ ይልቅ የኋለኞች እንዳደረገን ይመስለኛልና። ... እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፥ እንጠማለን፥ እንራቆታለን፥ እንጐሰማለን፥ እንከራተታለን፥ በገዛ እጃችን እየሠራን እንደክማለን፤ ሲሰድቡን እንመርቃለን፥ ሲያሳድዱን እንታገሣለን፥ ክፉ ሲናገሩን እንማልዳለን፤ እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጉድፍ ሆነናል።" (1ኛ ቆሮ. 4፥9-13) ሐዋርያት አንዳንዱ ደርብ ካለው ሕንፃ ተወረወሩ፣ በመጋዝ ተሰነጠቁ፣ በፈላ ዘይት ተጨመሩ፣ በመንገድ ተጎተቱ፣ በሰይፍ ስለት አለፉ፣ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ የሚሉ መጽሐፍት አያሌ ናቸው ታሪካቸውም የታወቀ ነው። ይህን ሁሉ ሰምተን እነርሱ የሚገቡበት ስፍራ እኛም እንኳን ደህና መጣችሁ ከተባልን ይደንቀኛል። ወይንም እነርሱን ተመልክቼ የራሴን ሕይወት (የዚህ መጽሐፍ ደራሲ) ስቃኝ አንበሳ ፊት የቆመች ስስ የሆንሁ እንደሆነ እገምታለሁ ። በአንድ ነገር ግን አምናለሁ። ሁላችን በክርስቶስ መሥዋዕት በእምነት እንደጸደቅን በሥራዬ ግን በአያሌው የከሰስኩ መሆኔን አስቀድሜ አውቄዋለሁ። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን በምሕረትና በጥንቃቄ ዋጋ ለመክፈል ጌታን እለምናለሁ። ጽድቁና ዋጋ መክፈሉ እንደ ሰማይ ቢርቅም ከኃጢአት ለመሸሽ እንኳ እየሞከርኩ ቢያንስ ጽድቁ ከፈራሳዊ ካልበለጠ መንግሥተ ሰማይ በሩ እንዳይዘጋ የነርሱ የጽድቅ ሙቀት መለኪያ እየያዝኩኝ ዘወትር በብብቴ አኖራለሁ። አይ በዚህ ዘመን (በአዲስ ኪዳን) ከእኛ የሚጠበቅ ሥራና ዋጋ መክፈል የቀረ መሆኑን የምታስብ ካለህ እጅግ የዋህ ነህ። ምክንያቱም ቅዱስ ጳወሎስ የአዲስ ኪዳን ሰው



ስመጥር ከተማ ተወልዶ ያደገ ዕብራዊ ለሕግ ቀናኢ የአብርሃም ዘር ነበር። በዚህ ማጣፊያው እንዳያጥረን ራሳችንን እንሸንግል።

ሀ. ጃንደረቦች

"ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ። ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው አላቸው።" (ማቴ. 19፥12)

ወንድ የእግዚአብሔር ክብር ምሳሌ እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ለእግዚአብሔር መንግሥት ክብር ራሳቸውን የሰለቡ መኖራቸውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አመለከተ። ማንም ሊቀበለው የማይደፍረው እንደ ሆነ ስለገባው ሊቀበል የሚችል ይቀበለው በማለት ዘጋው።

ለእግዚአብሔር መንግሥት የራሱን አካል በቢላዋ አሳለፈ በአካሉ ላይ ጨከነ። ወንድነቱን ሻረ ተራ ጃንደረባ ለመሆን ፈቀደ። የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚጋፋውን አካሉን ቆርጦ ጣለው። ዘር የሚተካበትን አካል ከራሱ ለየው ትዳሩን ተወ ልጆች መውለድን አቆመ ወደ ሴት መመልከት አቆመ ማንነቱን ሻረ። የእግዚአብሔርን መንግሥት ክብር በዚህ ሁኔታ ተመለከተ። ራስን ማጥፋት ያን ያህል አስቸጋሪ አይደለም። ምክንያቱም ማንም እንደ ሞተ ይሞታል ነገር ግን በሕይወቱ እየኖረ ይህን መሥዋዕትነት ከፈለ። ከእግዚአብሔር መንግሥት ይልቅ የሚበረታ አለመኖሩን አስታወቀ።

ለ. ቅዱስ ጳውሎስ

ለመንግሥተ ሰማያት ክብርና ግርማዊነት ለመግለጥ ዋጋ ከከፈሉ ቅዱሳን መካከል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአዲስ ኪዳን ከተገለጡ ሰዎች መካከል ሐዋርያው ጳውሎስ ተጠቃሽ ነው። እንዳንዴ ስለ አሁን ዘመን ክርስትና አኗኗርና የቅዱስ ጳውሎስን የሕይወት ገጠመኝ ስገነዘብ ሁሉ

መንግሥት ግባ የሚሉ ናቸው:: መዳናችሁን ፈጽሙ ያለ ቅዱስ ጳውሎስ መዳን እንዲሁ የሚዘነጋ ጉዳይ ይሆንን? በተሰሎንቄ ምዕራፍ አንድ ላይ አስደናቂ የመመረጥ ቃል ተናገረ:: "የእምነታችሁ ሥራ የፍቅራችሁንም ድካም የተስፋችሁን መጽናት በአምላካችንና በአባታችን ፊት ሳናቋርጥ እያሰብን፥ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በሁላችሁ ምክንያት እናመሰግናለን፤ በእግዚአብሔር የምትወደዱ ወንድሞች ሆይ፥ እንደ ተመረጣችሁ አውቀናልና::" (1ኛ ተሰ. 1፥2-4) ዓለምን ክጃለሁ፣ ሰይጣንን ክጃለሁ፣ ሥጋን ክጃለሁ በማለቱ ብቻ አንድ ሰው እንደ ተመረጠ ከገመትን የተሰሎንቄ ምዕመናም ያን ያህል በክርስቶስ የመዳናቸውን ፍሬ ተመልክቶ እንደ ተመረጣችሁ አውቀናል ለማለት ተነሣ::



## 19. መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም

"ጲላጦስም መልሶ፦ እኔ አይሁዳዊ ነኝን? ወገኖችህና የካህናት አለቆች ለእኔ አሳልፈው ሰጡህ፤ ምን አድርገሃል? አለው:: ኢየሱስም መልሶ፦ መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴ ከዚህ ዓለም ብትሆን፥ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም አለው::" (ዮሐ. 18፥35-36)

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ሲመላለስ ስለ አባቱ መንግሥት ተረድቶና አውቆ ይኖር ነበር:: ክብር አገኘ፣ ዝቅ አደረጉት፣ ተስፋ ሰጡት ወይም ተስፋ ነሱት ሁሉን ጉዳይ ከመንግሥቱ ጉዳይ አንጻር ይመለከተዋል:: ይህንንም አውቆ ሰይጣን የሰው ልጆች ልብ ውስጥ የዚህ ዓለም ክብር እንዳለ ስለተረዳ ሁሉን የሚያታልለውና የሚያሞኘው በዚህ ሲሆን ይህን ተንኮል ይዞ ኢየሱስ ጋር መጣ:: "ዲያብሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው፥ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ፦ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው:: ያን ጊዜ ኢየሱስ፦ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምላክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው:: ያን ጊዜ ዲያብሎስ ተወው፥ መላእክት ቀርበው ያገለግሉት ነበር::" (ማቴ. 4፥8-11) ሉቃስ ደግሞ የዓለምን መንግሥታትና ክብራቸውን ዲያብሎስ ለጌታ ኢየሱስ እንዳሳየው ይገልጣል:: የዓለም መንግሥታትና ክብራቸው ሁሉ በሰይጣን ቁጥጥር ስር ባይውል ኢየሱስ ለሰይጣን "ለአንተ ይህን ማን ሰጠህ" በማለት አክሎ ይመልስለት ነበር:: የዚህ ዓለም ገዢ በመሆኑ ሁሉን ተወለት::

የዲያብሎስ ፈተና ብዙ ፈርጅ አለው:: የሚፈተነው ሰው ክብርና ንጽሕና ይወስናል:: እንደ ኢየሱስ ዓይነቱን የዓለምን መንግሥታትና ክብር ሁሉ እሰጥሃለሁ በማለት ለማባባልና ለማግባባት ሞከረ:: ሌላውን ደግሞ

ሰይጣን መንግሥት ቁርባን ይዘው ለሚቀርቡ ነው:: ለነዚህ ሰዎች ወደድንም ጠላንም ጌታ እስኪመጣ በፍጹም ይቅርታና ጩኸት ካልተመለሱ በስተቀር የዘላለም ጥፋትና ቅጣት አለ:: ለሰይጣንና ለመላእክቱ የተዘጋጀ የዘላለም ቅጣት ይኸውም የዘለለም የእሳት ባሕር ነው:: እግዚአብሔር ፍቅር ከሆነ ይህን ለምን ያዘጋጃል የሚል ጥያቄ ያለው ሰው አስቀድሞ እግዚአብሔር ፍቅር ብቻ ሳይሆን ማንነቱ የተዋቀረውን በቀልን የተሞላ ጻድቅም ነው:: በግም እንበሳም ነው:: ከበግም የተረጸ ከአንበሳም ድል የነሳ ነው:: ሙሉ የዘላለም በረከትን ሽልማትን የያዘ ብቻ ሳይሆን ሙሉ ቅጣትንና ቁጣን የተሞላ ነው::



## 20. ዘመኑ ተፈፀመ

"ዮሐንስም አልፎ ከተሰጠ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌልን እየሰበከና፦ ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ።" (ማር. 1፥14-15)

"ነቢያት ሁሉና ሕጉ እስከ ዮሐንስ ድረስ ትንቢት ተናገሩ፤" (ማቴ. 11፥13)

የነቢያትና የሕጉ ፍጻሜ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የእርሱ መገለጥ ነው:: የነቢያትም ሆነ የሕጉ ዓላማ ጌታ ኢየሱስን ለሰዎች ማመልከት ሲሆን የትንቢቱ ተስፋ የጌታ መገለጥ ነበር:: በተለያየ መልኩ በመጽሐፍት ስለ ጌታ ኢየሱስ ተናገሩ በመጨረሻም ከሴት የተወለደው የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ::

ጌታ በመገለጡም ነቢያትና ሕጉ አረፉ፤ የተናገሩለት ቃል ሥጋ ለብሶ ተገለጠ:: የዚህ ጌታ ስብከት ደግሞ ዘመኑ ተፈጸመ ነበር:: የተባለው ዘመን ተፈጸመ በወንጌል እመኑ የእግዚአብሔር መንግሥት ተካፋዮች ሁኑ:: በተስፋ የኖራችሁበት ዘመን በዚህ ወንጌል ተካተተ፤ መንግሥተ ሰማያት የመኖሩ ተስፋ ተጀመረ:: የትንቢቱ ዘመን ተፈጸመ፤ ቃል መጸሰስ ተጀመረ::

የእግዚአብሔር መንግሥት እየገፋች ደረሰች ሁሉ ሰው ወደዚህ መንግሥት በረከት ለመግባት እጅ እንዲሰጥ ተጠየቀ:: እጅ መስጠት ማለት ለዚህ መንግሥት ተገዙ፣ በፊት የኖራችሁበት ዘመን የቆሸሸ በመሆኑ ንሐሃ ግቡ:: የመንግሥቱ ንጉሥ ለማዳን ተገለጠ የእግዚአብሔር መንግሥትም መረቧን ዘረጋች:: "እንግዲህ ለንስሐ የሚገባውን ፍሬ አድርጉ፤ በልባችሁም፦ አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ፤" (ማቴ. 3፥8-9)

ነቢዩ ኢጋቦስ የአዲስ ኪዳን ነቢይ ሲሆን ይህ ነቢይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቃል። የዚህ ነቢይ ቃል ደቀ መዛሙርትን ማስጠንቀቅ ነበር። በዚህ ነቢይ ቃል ቤተ ክርስቲያን ተበረታታች የረሃብ ዘመን እንደሚመጣ ለደቀ መዛሙርት በመንፈስ አመለከተ ደቀ መዛሙርት ገንዘብ በማዋጣት ወደ ተቸገሩ ሰደዱ ይህ ማለት የእግዚአብሔርን መንግሥት በጽናት እንድትቆም አገዘ።

ቤተ ክርስቲያን ሕዝቦቿን ማስተማር የሚገባት በአብዛኛው ስለ ተስፋ ሳይሆን የተፈጸመውን ተስፋ ተካፋይ እንዲሆኑ ነው ማለትም ክርስቶስ በክብር ሲገለጥ የሚኖረው አንድ ተስፋ አለ። በሕግና በነቢያት ተገልጾ የተፈጸመ ተስፋም አለ። ይኸውም የክርስቶስ መወለድ፣ መሞት፣ በክብር መነሳት፣ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ነው። የዚህ የተፈጸመውን ተስፋ ተካፋይ ያልሆነ ወደፊት የሚፈጸመው የክብር ተስፋ ተካፋይ ይሆናል ማለት አይቻልም። "አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን በኋላም የካዱትን እንደ ገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፤" (ዕብ. 6፥4-6)

ይህ ያለንበትን ዘመን ለማወቅ ይህ ጥቅስ ገላጭ ነው። ብርሃን የበራልን ዘመን ነው ሰማያዊውን ስጦታ <u>እንድንቀምሰው</u> የተፈጸመ ዘመን ነው። ከመንፈስ ቅዱስ ተካፋይ እንድንሆን ትንቢቱ ተፈጸመ። መልካሙን የእግዚአብሔርን ቃል እንድንቀምስ የተፈቀደም ሆኖ ሊመጣ ያለውን የዓለምን ኃይል በዚህ ዘመን እንድንቀምስ የተደረገበት ጊዜ ነው። ይህን ሁሉ ከደን ዋናውን ተስፋ ብንጠብቅ የዝቅተኛውን ትምህርት ተቋም ዘለንና ንቀን ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት መተናነቅ ይሆናል።



ኢየሱስ ተፈጸመ በወንጌል እመኑ በማለት በገሊላና በአካባቢው አስተማረ ሰዎች ግን ከወይኑ አትክልት ውጭ ጣሉት። ሊያስወርሰን ሊመጣ ወራሹ ይህ ነው እንግደለው በማለት ተማማሉበት "እርሱም፦ ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ ይላቸው ጀመር።" (ሉቃ. 4፥21)

ውስጥ ከሚጥሉት ሁሉ ይልቅ ይህች ድሃ መበለት አብልጣ ጣለች፤ ሁሉ ከትርፋቸው ጥለዋልና፥ ይህች ግን ከጉድለትዋ የነበራትን ሁሉ ትዳርዋን ሁሉ ጣለች አላቸው።" (ማር. 12፥41-44)

የዚህ ታናሽ መንጋ መዝገብ በሰማይ ነው ይህ መዝገብ ቶሎ እንዲከማች ለማድረግ ያለውን ሁሉ መሸጥ ጠየቀ። የዚህ ታናሽ መንጋ መዛግብት ከሌቦችና ከብል ነጻ ሲሆን መዝገቡ አያረጅም አያልቅምም። ያለውን ተሸጦ በምጽዋት በተሰጠ ገንዘብ የሚገኝ የዘላለም መዝገብ ነው። መንግሥት ያለው መንጋ በመሆኑ የዚህ መንግሥት መዛግብት አላቸው ከትርፍ ቀቀሎ የሚገኝ መዝገብ ሳይሆን ያለውን ሸጦ ለምጽዋት የሚጸርግ መዝገብ ነው።

ይህ መዝገብ ደግሞ ለራስ የሚሆን እንጂ ለጎረቤት አይደለም። ለራሳችሁ አድርጉ "ይህ ታናሽ መንጋ በምድር መዝገብ የለውም ሁሉን በመሸጡ አንድ መዝገብ ብቻ ቀረው።"

21.4. ልብ የሚጣልበት መዝገብ

"መዝገባችሁ ባለበት ልባችሁ ደግሞ በዚህ ይሆናል።"

የልብ መኖሪያዋ በመዝገብ ነው። በሰማይ ከሆነ በሰማይ፤ በምድርም ከሆነ በምድር ነው። እግዚአብሔር የመንጋው ልብ ከሰማይ ይሆን ዘንድ መዝገቡን በሰማይ አስቀመጠ። በሰማይ በመቀመጡም ልብም በሰማይ ሆነች። በምድር ያለው የማስፈጸሚያ አካል ነው። አንድ ንብረት በሰማይ መዝገብ ለማስቀመጥ በምድር ምጽዋት ማድረግ ነው። ሁሉ መዝገብ ለመንጋው እንዲሆን በምድር የሚገኘውን በሙሉ መሸጥ ነው። የምድሩ ሲሸጥ መቀመጫውን ሰማይ ያደርጋል የምድር ትምክህት ሲሸጥ ትምክህት በሙሉ በሰማይ ይሆናል።

ሰማያዊ ልብ ያለው ሰው መዝገቡ በሰማይ ነው። በምድር ያለም በምድር ነው። በገንዘቡ የሚመካ አንድ ባለጠጋ ያቀረበው ምሳሌ ይህን



ያብራራል። "እንዲህ አደርጋለሁ፤ ጐተራዬን አፍርሼ ሌላ የሚበልጥ እሠራለሁ፥ በዚያም ፍሬዬንና በረከቴን ሁሉ አከማቻለሁ፤ ነፍሴንም፦ አንቺ ነፍሴ፥ ለብዙ ዘመን የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ፤ ዕረፊ፥ ብዪ፥ ጠጪ፥ ደስ ይበልሽ እላታለሁ አለ። እግዚአብሔር ግን፦ አንተ ሰነፍ፥ በዚች ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ሊወስዱአት ይፈልጓታል፤ ይህስ የሰበሰብኸው ለማን ይሆናል? ለራሱ ገንዘብ የሚያከማች፥ በእግዚአብሔር ዘንድም ባለ ጠጋ ያልሆነ እንዲህ ነው።" (ሉቃ. 12፥18-21)

እግዚአብሔርን መምሰል በዚህ ምድር ማትረፊያ የሆነበት ዘመን ይህ ነው። በምድር መዛግብት ማከማቸት የቻለ በእግዚአብሔር የተባረከ የተባለበት ጊዜ ይህ ነው። ያለህን ሽጥ ምጽዋትም ስጥ በሰማይ መዝገብ አከማች የሚል ትምህርት የተናቀበት ነው። ሰይጣን የሰውን ነፍስ ለመስረቅ ይመጣል የሚሰርቀውም መናፍስቱን አሰልፎ ተራ ሌብነት ማድረግ ሳይሆን እንደ ባለ ጠጋው ሰው በምድር ሀብትን እንዲያከማች በሌሊት ግን ነፍሱን እንዲወስድ ነው። የሰው ልብ በቁሳዊው ዓለም ከተጠመደ ሰይጣን በሰው ያለውን ጸጋ ነፍስን ለመስረቅ ምቹ አጋጣሚ ነው። ሰይጣን መዝገብን የሚሰርቀው መዝገቡ በምድር ከሆነ ነው። የዚህ ታናሽ መንጋ ምሥጢር ግን ልዩ ነው። አንድ ነገር ሲያጋጥማቸው ይሸጣሉ ምጽዋትም ያደርጋሉ በዚህን ጊዜ መዝገባቸውን ከሰይጣን፣ ከሌባና ከብል ይጠብቃሉ። ልባቸውም ሰማይ በመሆኑ ሌባ አይደርስበትም፣ አይመኝም።